# የ ጥ ን ቆ ለ ው
# ኢ ኮ ኖ ሚ



## የተቋማት መውደቅ እና የመናፍስቱ መነሳት

# የጥንቆላው ኢኮኖሚ

የተቋማት መውደቅ እና የመናፍስቱ መነሳት

ማቲያስ ገሠሠ

ሚያዚያ, 2018

# ማውጫ


1 ጥንቆላ በእኛ ዘመን ..................................................................................................... 1

2 ዕንቆቅልሹ: ጥንቆላን ዘመናዊነት ሳይሽረው መቅረቱ ................................................................ 10

3 ጥንቆላ እንደ ትይዩ ተቋም (Witchcraft as a Parallel Institution) .......................................... 16

4 የጥንቆላ ኢኮኖሚ አካላት (The Elements of Witchcraft Economies) .................................. 22

5 የጥንቆላ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ምንጭ .......................................................................................... 29

6 የጥንቆላው ኢኮኖሚ እራሱን የእሚያጠናክርበት ዑደት (The Self-Reinforcing Loop)............... 34

7 ተቀጥላ ዋጋ እና የዋጋ ስረዓት ማዛባት - የጥንቆላ ኢኮኖሚ ችግሮች (Costs and Distortions - Problems of Witchcraft Economy)........................................................................................ 38

8 ሊህቃን ለምን የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ማፍረስ ያቅታቸዋል........................................................... 44

9 መፍትሔው : ተቋማዊ እንጂ የባሕል አብዮት ወይንም መንፈሳዊ አይደለም .................................. 48

10 መደምደሚያ : ከአጋንንት ወደ ተቋም ግንባታ ........................................................................ 52

# መግቢያ

ለብዙዎች ጥንቆላ ጎጂ እና ባሕላዊ ዕምነት ብቻ ነው።

በእዚኽ ዘመን ግን የመደበኛ ማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት መፍረክረክ እና መዳከም ፤ በእዚኽ ዘመን ጥንቆላን ፤ ከባሕላዊ ጎጂ ዕምነት አልፎ ፤ የመደበኛ ማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ተፎካካሪ መሆን የእሚፈልግ አደረጃጀት ወደ መሆን አድጓል።

በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ መደበኛ የሆኑት የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ በአወቃቀር እና በአሠራር ድክመት ፤ መስጠት የእሚገባቸውን መደበኛ አገልግሎት በእሚገባ መስጠት ሲያቅታቸው እና በእዚኽም ዜጎች ፦ የመጠቃት እና ጥረታቸው መና የመሆን ስሜት ሲፈጠርባቸው ፤ እንደ ዘመናዊ ጥንቆላ ዓይነት ፤ በኢመደበኛ መንገድ ጥቃትን እከላከላለኹ ፣ የጥረትን ውጤት አበዛለኹ የእሚል አሠራር ፤ እራሱን ለማራባት እና ለማስፋት ምቹ አረንቋ ያገኛል።

በእዚኽም የመደበኛ ተቋማት መዳከም ታግዞ ፤ ዘመናዊ ጥንቆላ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ፤ ከጎጂ ባሕላዊ ዕምነትነት አልፎ ፤ ከአንድ ኢኮኖሚያዊ ስረዓት ጋር የእሚነጻጸር ፦ ሰፊ ኢመደበኛ ኔትዎርክ ያለው ፣ ተሳታፊዎችን በአገልግሎት ተቀባይነት እና አቅራቢነት ሥራዬ ብሎ የእሚመለምል ፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የእሚያከፋፍል ፣ የእራሱን አሠራር/ሕግ ወደ መሬት አውርዶ የእሚያስፈጽም ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያለው አደረጃጀት ሆኗል።

በእዚኽ መልኩ ድርጅታዊ ቁመናውን ለማጠናከር ፤ ከጥንቆላው ጋር አብሮ ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀትን ከማሕበራዊ ምህንድስና (Social Engineering) ጋር አብሮ ይጠቀማል።

ይኽን ዓይነት ቁመና የያዘው ጥንቆላ ፤ በኢመደበኛ ኔትዎርኩ ላሉ ሰዎች ፤ ምን አልባት ጥቅም እና አገልግሎት እየሰጠ ሊሆን ይችላል። ከጥንቆላው መረብ ውጭ ላሉ ፦ ግለሰቦች ፣ ቤተሰቦች እና ድርጅቶች በተናጠል ፤ በጠቅላላው ጥንቆላ ለተስፋፋበት ማሕበረሰብ ግን ብዙ ጉዳት የእሚያደርስ እና ድብቅ ብዙ ዋጋ የእሚያስከፍል ጥገኛ ተውሳክ ሆኗል።

የእዚኽ መጣጥፍ ዓላማም ፦ ይኽን የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፦ አመጣጥ ፣ ባሕሪ እና አሠራር ፤ በመግለጽ ክፋቱን ብቻ ማሳየት ሳይሆን መፍትኼውንም መጠቆም ነው።

በመሆኑም ፦ በእዚኽ መጣጥፍ ውስጥ ፤ የጥንቆላ መፍትኼው ፤ ዘመናዊ መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን በማጠናከር ፤ ዜጎችን ያለ ምንም ማመካኘት በእኩልነት የእሚያገለግሉ እና ከእሚሰጡትም አገልግሎት የተነሳ ዜጎች የኢኮኖሚ ደረጃቸውን በተጨባጭ ማሻሻል የእሚችሉ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲችሉ ማድረግ እንጂ ፤ መንፈሳዊ ወይንም ባሕላዊ ውጊያ ማድረግ አይደለም የእሚል የመፍትኼ አቅጣጫ ከእነ ማብራሪያው ተቀምጧል !

# 1 ጥንቆላ በእኛ ዘመን

በእዚኽ ዘመን ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላቀር ሐገራት ፤ ጥንቆላ ግዙፍ ተቋማዊ ቁመና ተላብሶ ፤ ከግል ሕይወት እስከ ማሕበራዊ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት እና ውጤቶችን በመወሰን ፤ እራሱን እንደ ትዩዩ መንግሥት ያደረገበት ደረጃ ነው ያለው።

ዕውነታው ይኽ ቢሆንም ቅሉ ፤ የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ፤ ስለ ዘመናዊ ጥንቆላ ያላቸው ግንዛቤ ሙሉ ባለመሆኑ ፤ ጉዳዩ የእሚገባውን ትኩረት አላገኘም።

ለአንድ አንዶች ጥንቆላ ማለት ፦ አንድ ጠንቋይ በአንድ ክፍል ወይንም ቤት ውስጥ ተቀምጦ ፦ በሽታ አድናለኹ ፣ ገበያ አመጣለኹ ፣ ኃብታም አደርጋለኹ ፣ ወዘተ እያለ የእሚልበት እና ይኽም በተጨባጭ በሰዎች ሕይወት ላይ የእሚኖረው ተፅዕኖ ዝቅተኛ ወይንም ምንም ነው የእሚል ነው። ይኽ ዓይነቱ አስተሳሰበ ፤ በተለይ የተማሩ እና በኃይማኖታቸው የበረቱ ሰዎች የእሚያዘወትሩት ነው።

ለሌሎች ደግሞ ፤ ጥንቆላን እንደ ትልቅ ኃይል አድርገው ስለ እሚያዩት እና ስለ ጥንቆላ ክፋት ማውራት ወይንም በአንዳች መንገድ ከጥንቆላ ጋር መጋጨት ከፍተኛ ጉዳት ያደርስብኛል ብለው በመፍራት ጉዳዩን የእሚሸሹት በመሆኑ ፤ የዘመናዊ ጥንቆላ የደረሰበትን ቢያውቁም እንኳን ወደ አደባባይ ወጥቶ ኹሉም እንዲያውቀው አያደርጉም።

እንደገና ከእነ እዚኽ ውጭ የሆኑ ሌሎች ደግሞ ጥንቆላ ትልቅ አቅም ነው ብለው ስለ እሚያምኑ ፤ ነገር ግን ፤ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ፤ ከፍተኛ ኃይማኖተኝነት ባለበት ሐገር በጥንቆላ ማመን የእሚያደርሰውን ማሕበራዊ ውግዘት ፍራቻ እንዲኹም የስኬትን ምስጢር የመደበቅ ፍላጎት ተዳምረው ፤ የጥንቆላውን ጉዳይ በምስጢር መጠበቅ የእሚፈልጉ በመሆኑ ፤ ዘመናዊ ጥንቆላ የደረሰበት ደረጃ ተሰውሮ እንዲቆይ የእራሱን አስተዋዕዖ አድርጓል።

ዕውነታው ግን ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ፣ ጥንቆላ በከፍተኛ መጠን ተደራጅቶ እና ራሱን ስውር ትይዩ መንግሥት አድርጎ ፤ ከግል ጉዳዮች አንስቶ እስከ ማሕበራዊ ጉዳዮች ፤ መደበኛውን ኃይማኖት እና መንግሥት ተክቼ ፦ በሽታ አድናለኹ ፣ ገንዘብ አዘንባለኹ ፣ የፍርድ ቤት ክርክር በቶሎ እንዲያልቅ አደርጋለኹ ፣ የተንዛዛ ጉዳይ በፍጥነት አስፈጽማለኹ ፣ የቀዘቀዘ እና የደከመ ገበያ ሞቅ አደርጋለኹ ፣ የሥራ በር እከፍታለኹ ፣ የትዳር አጋር አመጣለኹ ፣ ባላንጣን ልክ አስገባለኹ ፣ ወዘተ የእሚል ትልቅ ድርጅታዊ አቅም ያለው ተቋም ሆኖ አድጓል።

ዘመናዊ ጥንቆላ የደረሰበት ደረጃ ይኽ ከሆነ ፤ ይኽ ጥንቆላ የእሚባለው ነገር ምንድ ነው ? እንዴት ነው እሚሠራው ? ወዘተ የእሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

ምክንያቱም ፦ አንድ እንደ ባዕድ አምልኮ የእሚታይ ተራ ልማድ ፤ እራሱን የመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ትይዩ እስኪሆን ድረስ የእሚያጎለብትበት መንገድ ለብዙዎች ግልፅ አይደለም።

ስለ እዚኽ ፦ በእኛ ዘመን ጥቆላ የደረሰበትን ደረጃ ለማብራራት እንሞክር።

በደፈናው ጥንቆላ ምን ማለት ነው ብለን ለመተርጎም ከተነሳን ፤ ጥንቆላ ፦ አስማትን (ምትኃትን) ፣ መ።መጠንቆልን (የመተንበይ፣ የመገመት ፣ ወዘተ) እና እንደ ኮከብ ቆጠራ ፣ ድግምት ፣ ወዘተ ዓይነት መንገዶችን በመጠቀም ፦ ተከታይ ለማፍራት ፣ ጉዳት ለማድረስ ፣ የችግር መፍሔ ለመስጠት ፣ አንዳች ግብ ለማሳካት መመኮር ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አብሮትም የአሠራር ስረዓት ፦ በግ እንደ ማረድ ፣ ደም እንደ ማፍሰስ ፣ እንደ መራገም ወይንም ቃል ማውጣት ይኖረዋል።

በሳይንሳዊ መንገድ እንመልከተው ካልን ፤ ምንም እንኳን ጠንቋዮች በሰዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው ተፈጥሮ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ እንችላለን ፤ ስለ እዚኽ፦ ዝናብ እናዘንባለን ፣ በሽታ እናመጣለን ፣ በሽታ እንፈውሳለን ፣ ድንጋይ እናዘንባለን ፣ ወዘተ ቢሉም ፤ በእዚኽ ረገድ ጠንቋዮች ይኽን ማድረግ ስለ መቻላቻው ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የለም።

ከእዚኽ ተነስተን ፤ ጠንቋዮች በተፈጥሮ እና በቁሳዊ ነገር ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ በማድረግ ፦ ለምሳሌ ፦ በጥንቆላ ብቻ ፦ ዝናብ ማዝነብ ፣ ክብደት ማንሳት ፣ ወዘተ እንደ እማይችሉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ሰይጣን በእራሱ በቁስ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግ ይችል ይሆናል ፤ በጠንቋዮች ጥንቁልና ግን አይሆንም።

ሆኖም ፦ በሳይንስ ፓራሳይኮሎጂ (Parapsychology) የእሚባለው እና ከአምስቱ ህዋሳት ውጭ በሆነ መንገድ ፦ ቴሌፓቲ (Telepathy) ወይንም ያለ ንግግር ኃሳብን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍ ነገር ፣ ክሌርቮያንስ (Clairvoyance) የተደበቁ እና የተሰወሩ ነገሮችን ማወቅ ፣ ኢኤስፒ (ESP – Extra Sensory Perception) ፣ ወዘተ በሳይንሱ ዓለም እራሱ አፈንጋጭ ክስተቶች (Paranormal) በእሚባል በአግባቡ የተመዘገቡ እና የእሚታወቁ ናቸው።

በእርግጥ ይኽ ማለት ሳይንስ ጥንቆላን ፤ ፓራሳይኮሎጂ (Parapsychology) በእሚል እውቅና ይሰጠዋል ማለት ሳይሆን ፤ በአፈንጋጭ ክስተትነት አውቆ ፤ በሳይንሳዊ መንገድ ለመረዳት ጥረት ያደርጋል ማለት ነው።

በተለምዶ እኛ ጥንቆላ የእምንለውን እና ሳይንስ አፈንጋጭ ወይንም ፓራሳይኮሎጂ (Parapsychology) የእሚለውን ነገር ለሳይንስ አስቸጋሪ የእሚያደርገው ፤ በመስኩ ያለው ተለዋዋጭነት እና የጥራት ችግር ነው።

አንድ ጠንቋይ ፦ ኃሳብ መላክ እችላለኹ ሊል ይችላል ፤ ነገር ግን ይኽ ኃሳብ የመላክ ነገር ኹል ግዜ አይሳካለትም ፤ ኹል ግዜ አይሳካለትም ብቻ ሳይሆን ምን ሲሆን እንደ እሚሳካለት እና ምን ሲሆን እንደ

እማይሳካለት ማወቅ ያስቸግራል። በተመሳሳይም የተደበቀ ነገር አውቃለኹ ወይንም ምስጢር እገልጣለኹ ሲልም እንደ እዚያው ነው። ከእዚኽ የተነሳ ፤ ሳይንስ ጉዳዩን የእድል እና የግምት ጉዳይ ነው ብሎ እንዲያጣጥል በር ይከፍታል።

ለምሳሌ ፡- ፕሮጀክት ሰን ስትሪክ (Project Sun Streak) በእሚል (ሊንኩ ይኸ ነው SUN STREAK PROJECT 0209 SESSION NUMBER: - CRV VIEWER: 032) በ1980ዎቹ ሲአይኤ (CIA) የተባለው የአሜሪካው የስለላ ድርጅት ፤ ለአንድ የሩቅ ተመልካች (Remote Viewers) ብለው ላሉት ሰው ፤ የጂፒኤስ ኮርድኔት (GPS Coordinate) በኮድ አድርገው ሰጥተውት ፤ በእዚኽ ቦታ ምን ይገኛል ብለው ሲጠይቁት ፤ በእዚያ ቦታ ከሞላ ጎደል የሙሴ ጽላትን የእሚመስል ነገር እንደ እሚገኝ እና አከባቢው ምን እንደ እሚመስል ፤ ዶክመንቱ ላይ ልታዩ እንደ እምትችሉት በስዕል ለማስቀመጥ ሞክሯል።

ለምሳሌ ፡- ከእዚኽ በታች የዕምታዩት የኪሩቤል ስዕል ፤ ከእላይ በአስቀመጥኩት ሊንክ ሲአይኤ (CIA) ሰውየው ይታየኛል ብሎ የሳለው ነው ብሎ የለቀቀው ነው ፡-




*ስዕል 1 ፡ የሲአይኤው (CIA) የሩቅ ተመካች ታየኝ ብሎ ከሳለው ስዕል አንዱ ፤ የኪሩቤል ስዕል።*

በመጽሐፍ ቅዱሱ መሠረት ፤ ታቦቱ ምን ይመስላል ካልን ደግሞ ፤ ታቦቱ ከእዚኽ በታች ያለውን ስዕል ነው እሚመስለው ፡-



*ስዕል 2 ፡ በመጽሐፍ ቅዱሱ መሠረት የተሠራ ተታቦት ስዕል*

ምን አልባት ግርታ እንደ አይፈጠር ፤ ታቦት እና ጽላት እንደ እሚለያዩ እና ታቦት የእሚባለው ይኽ በወርቅ የተለበጠ መሸከሚያ ያለው እና ከእላይ ኪሩቤል የእሚባሉት መላዕክት የእሚሸፍኑት ሳጥን ሲሆን ፤ ጽላት ማለት ግን ፤ አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፈበት እዚኽ ታቦት/ሳጥን ውስጥ የእሚቀመጥ ኹለት ጥርብ ድንጋይ ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ፤ በእግዚአብሔር ጣት አስርቱ ትዕዛዛት የተጻፈበት የድንጋይ ጥርብ ስለ ሆነ (ዘጸዓት 24፡12 ይመልከቱ) ፤ ጽላትን በስዕል ዕናሳየው ካልን ፤ የእሚከተለውን ነው እሚመስለው፡-



*ስዕል 3 ፡ ፅላት የእሚባለው እና አስርቱ ትዕዛዛት የተጻፈበት የድንጋይ ጥርብ*

ይፋ በተደረገው የሲአይኤ(CIA) ዶክመንት ላይ እንደ ተቀመጠው ፤ ይኽ የሩቅ ተመልካች (Remote Viewer) የተባለው ሰው ፤ አሜርካ ተቀምጦ ፤ አንድ መደበኛ ያልሆነ የጂዖግራፊክ ኮርድኔት (Geographic Coordinate) ብቻ ተሰጥቶት ፤ በእዚኽ ቦታ ምን ይታያኃል ተብሎ ሲጠየቅ ፤ የተለያዩ ነገሮችን ሲያስቀምጥ ፤ ታቦቱን የእሚሸፍኑትን ኪርቤሎች ግን ፤ በአካል ያያቸው እስኪመስል ፤ ጥሩ አድርጎ አስቀምጧል።

ዶክመንቱ ላይ የተቀመጠው የእንግሊዘኛ ትዕዛዝ ይኽን የእሚል ነው ፡-

1. (S/NF/SK) MISSION: ACCESS AND DESCRIBE THE TARGET IDENTIFIED BY COORDINATE 781410/110121

ይኽን ትዕዛዝ ስንተረጉመው ፡-

- S – Secrete - ይኽ ምስጢር ተደብቆ መቆየት አለበት ፤ ካፈተለከ ችግር ሊፈጥር ይችላል።
- NF – Not for Foreign Nationals - ይኽ ዶክመንት የአሜርካ ዜግነት ለሌላቸው ለውጭ ዜጎች በፍጹም አይሰጥም ።
- SK – Special Knowledge - ልዩ የሆነ ዕውቀት መስክ።
- MISSION: ACCESS AND DESCRIBE THE TARGET IDENTIFIED BY COORDINATE 781410/110121 - ተልዕኮ ፡ በእዚኽ የቦታ አመልካች 781410/110121 የተመለከተው ቦታ ላይ የእሚገኘውን ነገር ተመልከት እና ግለጽ።

እዚኽ ጋር ፤ የቦታ አመልካች ወይንም ኮርድኔት ተብሎ 781410/110121 የተሰጠው ቁጥር ፤ መደበኛ የጂኦግራፊ ኮርድኔት ባለመሆኑ ፤ በታውን ከዶክመንቱ ተነስቶ ማወቅ አይቻልም። እንደ እሚባለውም ፤ ሙከራው የእሚደረግበት ሰው ፤ በታውን እንደ አይገምት ፤ የበታው ምስጢራዊ ኮድ እንጂ የበታው አመልካች ኮርድኔት አይደለም።

ምን አልባት ሰምታቹ እንደ እምታውቁት ግን ፤ አንድ አንድ ሰዎች ፤ ሲአይኤ (CIA) ፤ ሪሞት ቪወር (Remote Viewer) ተጠቅሞ ፤ ታቦቱ አክሱም ኢትዮጵያ ይገኛል ብሎ አረጋገጠ ተብሎ ሲዘገብ ነበር ፤ ዶክመንቱ ግን ታቦቱ መኖሩን ዓሳየ እንጂ ፤ ኢትዮጵያ ነው አላለም እንዲያውም ወደ መካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ነው የገመተው።

ሆኖም ፡- እነ እዚኽ የሩቅ ተመልካች የእሚባሉት ሰዎች ፤ አንድ አንድ ግዜ ፤ በእዚኽ በኪሩቤሉ እንደ ታየው ፤ እሚያስገርም የተሰወረ ነገር የማወቅ ብቃት ቢያሳዩም ፤ ጉዳዩ በኋላ ላይ ፤ ወደ አሜሪካው የጥናት ተቋም (American Reaser Instituion) ለግምገማ ሲላክ ፤ በእዚኽ ሪፖርት መሠረት (ይኽ የሪፖርቱ ሊንክ ነው ፡- [An Evaluation of Remote Viewing: Research and Applications](#) ) ፤ አንድ አንድ ግዜ አስገራሚ የሆነ ምስጢር የማወቅ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ቢኖሩም ፤ ይኽ የሩቅ ተመልካች የእሚባለው ነገር ፤ በአስተማማኝ መልኩ መረጃ ለመሰብሰብ እና ውሳኔ ለመወሰን ስለ እማያስችል መቋረጥ አለበት አሉ ፡-

> *"ከኹሉ በላይ ፡- በሩቅ ተመልካቾች ፤ አንድ ስውር ነገርን ዓየኹ በእሚል የእሚያቀርቡት መረጃ ድንግዝግዝ ያለ እና አሻሚ በመሆኑ ፤ በእርሱ ላይ ተመርኩዞ ውሳኔ ለመወሰን የትክክለኛነት እና የጥራት ጉድለት ያለበት ነው። ከእዚኽም በመነሳት ፡- ለመረጃ ስብሰባ የሩቅ ተመልካቾችን መጠቀም ተገቢ ነው የእሚባልበት ምክንያት የለም።"*
>
> *"Most importantly, the information provided by remote viewing is vague and ambiguous, making it difficult, if not impossible, for the technique to yield information of sufficient quality and accuracy of information for actionable intelligence. Thus, we conclude that continued use of remote viewing in intelligence gathering operations is not warranted."*

በእዚያ ላይ እንደ ተመለከተው ፤ የአሜሪካው የስለላ ድርጅት ፤ እንደ እዚኽ ዓይነት የሩቅ ተመልካች የሆኑ ሰዎችን ፤ ለስለላ ዓላማ መጠቀም ይቻል እንደ ሆን ለማወቅ ፤ በሰዎቹ ላይ ብዙ ሙከራ ካደረገ በኋላ ፤ ሰዎቹ በተለየ ኹኔታ የተደበቀ ነገር የማወቅ ነገር ቢኖራቸውም ፤ ዕውቀታቸው ብዥታ ያለበት በመሆኑ እና አንድ አንዴም የእሚሳሳቱ በመሆኑ ፤ እንደ አሠራር ልንጠቀምበት አንችልም ብሎ ትቶታል።

ሆኖም ፡- ከአስር ሙከራ አምስት ሊሆን ቢችልም እና ሲሳካም ጥራት ባይኖረውም ፤ እኛ ጠንቋይ የእምንላቸው ሰዎች ፤ የአጋንንት አሠራር ተጠቅመው ያደርጋሉ የእምንላቸውን ነገሮች ፤ ማለትም ፡-

የተሰወረ ነገር ማወቅ ፣ የወደፊት ማየት ፣ የፍርኃት እና የጥርጣሬ ኃሳብ መልቀቅ ፣ ወዘተ ዓይነት ነገር ማድረግ የአሚችሉ ሰዎች መኖራቸው ግን እርግጠኛ ነው።

ስለ እዚኽ ፦ ምንም እንኳን ጠንቋይ የአምንላቸው ሰዎች ፤ አፈንጋጭ አሠራራቸውን (Their paranormal practices) የአሚያመጡት ክፉ መናፍስትን በመጠቀም ነው ብለን ማስረገጥ ባንችልም ፤ የሰዎችን ስሜት እና ስነ ልቦና መረበሽ የአሚችሉ ፣ የተደበቀ ነገር (በከፊልም በድንብዝብዝ ቢሆንም) የአሚያውቁ ፣ ወዘተ ዓይነት ሰዎች እንደ አሉ ግን እርግጠኛ መሆን እንችላለን።

ትልቁ ነገር ግን ፤ በተለይ ከጥንቆላ ኢኮኖሚ አንጻር ፤ አንድ ጠንቋይ ነኝ የአሚል ሰው ፦ ኃሳብ ማስተላለፍ መቻሉ ፣ የተደበቀ ነገር ማወቁ ወይንም አንዳች ዓይነት ምትሐት እሰራለሁ ማለቱ ወይንም መሥራቱ አይደለም ።

የጠንቋዩ ጉዳይ ያ ብቻ ቢሆን ኖሮ ፤ ከማሕበራዊ ተፅዕኖ አንጻር ፤ አንድ መሐረብ እርግብ አደርጋለኹ ብሎ ትርዒት ከአሚያሳይ ሰው ያለፈ ምንም ፋይዳ አይኖረውም ነበር።

በእኛ ዘመን ጥንቆላን የአሚያከፋው ፤ ይኽ አፈንጋጭ ልምምድ (Paranormal Experience) በማሕበራዊ ምህንድስናና (Social Engineering) እና በኢመደበኛ ሰፊ አደረጃጀት የአሚደገፍ በመሆኑ ነው።

በእዚኽ አውድ ፤ ማሕበራዊ ምህንድስና እና ኢመደበኛ አደረጃጀት ምን ማለት እንደ ሆኑ እንመልከት፦

የዲጅታል ዘመን (Digital Age) ከመምጣቱ በፊት ፤ ማሕበራዊ ምህንድስናና (Social Engineering) የአሚለው ኃሳብ ፤ በተማከለ እና በታቀደ መልኩ አንድ ማሕበረሰብን ወደ እሚፈለገው የዕድገት እና የልቀት ደረጃ ላይ ለማምጣት የአሚወሰዱ የተለያዩ ማሕበራዊ ፖሊሲዎችን የአሚመለከት ነገር ነበር ፤ ለምሳሌ ፦ ፊውዳልምን ሽሮ ጭሰኝነትን ማስቀረት ፣ የሴቶችን መብት አክብሮ ሴቶች ከወንድ እኩል የኹሉም የማሕበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ መብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ፣ ባርነትን መሻር እና የሰው ባሪያ የለም ማለት ፣ ወዘተ።

ይኽ ትርጉም አሁንም ያልተቀየረ ቢሆንም የዲጂታል ዘመኑ (Digital Age) አዲስ ትርጉም ጨምሮበታል።

በእዚኽ በዲጅታሉ ዘመን (Digital Age) የሰዎችን ፓስዎርድ ለመስረቅ ፤ የፓስወርድ ደህንነት ማስጠበቂያ ስረዓቶቹ በእየ ግዜው እየጠነከሩ አስቸጋሪ ስለ አደረጉት ፤ ሐከሮች የሰዎችን ፓስወርድ ለመስረቅ ማሕበራዊ ምህንድስናና (Social Engineering) ይመርጣሉ።

በእዚኽ አውዱ **ማሕበራዊ ምህንድስና (Social Engineering)** ማለት ፤ የማታለያ እና የማባበያ ስልቶችን በመጠቀም ሰዎች የግል መረጃቸውን እና ሚስጢራቸውን እንዲዘረግፉ በማድረግ ያንን ለማጭበርበር ዓላማ መጠቀም ማለት ነው።

ስለ እዚኽ ፦ ፓስወርድ ለመስረቅ ፤ ለምሳሌ ፦ የሰውየውን ስም ፣ የትዳር ጓደኛውን ስም ፣ የተወለደበትን ቀን ፣ የእሚወደውን ሰው ፣ የሙዚቃ ምርጫ ፣ ወዘተ በማወቅ ፤ ፓስወርዱን ለመገመት መሞከር አንዱ ስልት ነው። ካልሆነ ከሰውየው ጋር ጓደኝነት መሥርቶ ፤ ለምሳሌ ፦ ፓስወርድ መስረቂያ ሶፍትዌር የተጫነበት ፍላሽ ዲስክ በሰውየው ኮምፒውተር ላይ መሠካት ፣ ወዘተ ነው።

በአጠቃላይ ማሕበራዊ ምህንድስና (Social Engineering) ፤ በእዚኽ አውድ ፤ የተለያዩ የማታለያ ፣ የማባበያ እና የማስፈራሪያ ስልቶችን በመጠቀም ፤ ከሰዎች የእሚፈልጉትን ምስጢር ወይንም ነገር ማግኘት ነው።

ለምሳሌ ፦ የጥንቆላ ኢኮኖሚው ፤ በጥንቆላው ማወቅ ሲያቅተው ፤ የሰውየውን ስልክ ፣ ስም ፣ ችግር ፣ ወዘተ በማሕበራዊ ምህንድስና አፈላልጎ አግኝቶ ፤ ለሰውየው ስልኩን በመንገር ፣ ያለበትን ችግር በመንገር ፣ ወዘተ ማስደመም እና የጥንቆላው አማኝ ማድረግ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ማሕበራዊ ምህንድስናን የእሚጠቀምበት አንድ መንገድ ነው።

ማሕበራዊ ምህንድስና ለመሰብም ብቻ ሳይሆን ፤ ለማስገደድ ፣ ለማስፈራራት ፣ ለመጉዳት ፣ ለመተንኮስ ፣ ወዘተ ሥራ ላይ ሊውል ይችላል።

ለምሳሌ ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ከአንድ ሰው ቁልፍ መስረቅ ከፈለገ ፤ በሰው መጠጥ ውስጥ ብዥ የእሚያደርግ መድኃኒት ሊጠቀም እና ቁልፍ ሊሰርቅ ይችላል። ሰዎችን በተደራጀ መልኩ ፦ በመስረቅ ፣ መኪና በማጋጨት ፣ በነገር በመተንኮስ ያንንም እኔ ነኝ ያደረኩት በእሚል በስውር በማሳየት ፤ ሰዎችን ሊያስፈራራ ፣ ጫና ሊፈጥር ፣ ሊጎዳ ይችላል።

**<u>ኢመደበኛ አደረጃጀት</u>** ፤ የመንግሥት ሰዎች እና አሠራሮችን በስውር የእሚጠቀም ቢሆንም ፤ በአዋጅ ያልተቋቋመ ፦ በጽሑፍ የሠፈረ እና ግልፅ መዋቅራዊ ቅርፅ ፣ ዓላማ ፣ ተልዕኮ እና ተጠያቂነት የሌለው ፤ ነገር ግን ሰፊ መረብ ኖሮት ፤ የተሰለፈበትን ዓላማ ለማስፈጸም የእሚችልበት ስውር የሰው ኔትዎርክ ማለት ነው።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ይኽን ኢመደበኛ አደረጃጀቱን ተጠቅሞ ነው ፤ የማሕበራዊ ምህንድስናውን ሥራ የእሚሠራው።

ይኽ አደረጃጀት ፦ ምን አልባት በብዙ ሺ ሰዎችን ፣ በብዙ ሺ መኪኖችን ፣ የስልክ መጥለፍያ ሶፍትዌሮችን ፣ ወዘተ ሊጠቀም የእሚችል ፤ ከፍተኛ ገንዘብ እና የሰው ኃብት ማንቀሳቀስ የእሚችል ሊሆን ይችላል።

ስለ እዚኽ ፦ ዘመናዊ ጥንቆላ ምን ይመስላል ካልን ፤ ከእላይ ለመግለጽ የሞከርናቸውን የእሚከተሉት ሶሥት ነገሮች ያካትታል ማለት ነው ፦

1. ጥንቆላ ወይንም ፓራሳይኮሎጂ (Parapsychology)
2. ማሕበራዊ ምህንድስና እና

## 3. ሰፊ ኢመደበኛ ኔትዎርክ

ጥንቆላውን ተጠቅሞ ፤ ፍርኃት ይለቃል ፣ ኃሳብ ሰርቆ ሰው ያጋጫል ፣ ወዘተ። ያ አልሠራም ወይንም አልበቃም ሲል ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀቱ ፤ የማሕበራዊ ምህንድስና ሥራ እንዲሠራ በማድረግ ፤ በተደራጀ መልኩ በስውር የሰበሰበውን መረጅ በመጠቀም ፦ ሰው ያስደምማል ፣ ያስፈራራል ፣ ጫና ያደርጋል ፣ ያታልላል ፣ ወዘተ ፤ በእንደዚኽ ዓይነት መንገድ ነው ዘመናዊው ጥንቆላ የእሚሠራው።

ስለእዚኽ፦ የእኛ ዘመኑ ጥንቆላ ፤ ስሙ ነው እንጂ ጥንቆላ ፤ የጥንቆላ ፣ የማሕበራዊ ምህንድስና እና የኢመደበኛ ኔትወርክ ጥምረት የሆነ ፤ እራሱን ትዩዩ መንግሥት አድርጎ ማቅረብ የእሚፈልግ ፤ ሰነፍ እና አመጸኛ ፤ የትምክህት ኃይል ነው።

ይኽ የስንፍና እና የትምክህት ጥምረት በአምሳያው ኢኮኖሚ እንዴት እንደ እሚገነባ በአንድ ምሳሌ ለማሳየት ልሞክር።

እንበል እና አንድ በግሮሰሪ ንግድ ጥሩ ዕውቀት እና ልምድ ያለው ነገር ግን ፤ ያንን ዕውቀት እና ልምዱን ተጠቅሞ የራሱ ግሬሰሪ የእሚከፍትበት ገንዘብ የሌለው ሰው ይኖራል። ይኽ ሰው ይኽን ችግሩን ለመፍታት ወደ አንዱ ጠንቋይ ቤት ጎራ ይላል።

ያ ጠንቋይ ፤ ይኽን ሰው ፣ እኔ እምልህን አድርግ እንጂ እኔ እዚኽ እና እዚያ ቦታ አንድ ጥሩ ለግሮሰሪ የእሚሆን ቤት እሰጥኀለው ይላል።

ከእዚያም ጠንቋዩ ጠንቁሎ ይኹን ወይንም አስቀድሞ መረጃው ኖሮት ፤ አንድ ክርክር ያለበት እና የተዘጋ ፤ ጥሩ ግሮሰሪ መሆን የእሚችል ፤ የኪራይ ቤት መኖሩን ይጠቁማል ወይንም ይጠነቁላል።

ከእዚያም ፤ በጠንቋዩ ዙሪያ የተሰበሰበው ፤ የኢመደበኛ መረብ ፤ ስለ እዚያ ቤት ፤ የማሕበራዊ ምህንድስናውን በመጠቀም ፤ መረጃ ይሰበስበል ፤ መረጃ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ፤ ያለውን የማሕበራዊ ምህንድስና እና የኢመደበኛ አደረጃጀት አቅም ተጠቅሞ ፤ ያንን ቤት አስከፍቶ ፤ ተከራካሪዎችን አስወግዶ ፤ ያንን ቤት ወደ ጠንቋዩ ጋር ለመጣው ሰው እንዲሰጥ ያደርጋል።

ይኽ ችግር የተፈታለት እና ለግሮሰሪ የእሚሆን ፤ ሰፊ የክራይቤት ቤት በርካሽ ያገኘው ሰው ፤ በእዚያ ቦታ ያለውን ዕውቀት እና ልምድ ተጠቅሞ ግሮሰሪ ከፍቶ ቆንጆ የገቢ ምንጭ ሲያገኝ ፤ ጠንቋዩ እንደ አደረገለት ስለ እሚያስብ ፤ የጠንቋዩ ታዛዥ ባሪያ ይሆናል ፤ ያም ብቻ ሳይሆን ፤ የእዚያ የኢመደብኛው መረብ ምልምል አባልም ይሆናል ፤ በእየ ግዜው ለጠንቋዩ ከእሚያመጣው ስጦታ ጋር።

ወይንም አንድ የተመረቀ ወጣት ሥራ ፈልጎ ቢያጣ እና ወደ አንዱ ጠንቋይ ቢኼድ እና ጠንቋዩ እኔ ሥራ እሰጥኃለኹ ብሎ ፤ በዙሪያው የሰፈረውን የኢመደበኛ አደረጃጀት ተጠቅሞ ፤ ለእዚያ ወጣት ሥራ ቢያስገኝለት ፤ ውጤቱ ተመሳሳይ ይሆናል።

በግዜ ኺደት ደግሞ ፤ ይኽንን ዓይነት ርካሽ የኪራይቤት ቤት ፤ በነጻ ሊባል በእሚችል ዋጋ አግኝቶ ኑሮውን የቀየረው ወይንም ያ ወጣት ሥራ ያገኘው በጠንቋይ አማካኝነት መሆኑ ውስጥ ውስጡን ሲታወቅ

፤ በማሕበረሰቡ ውስጥ በጠንቋይ የማመን ነገር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ስለ እሚደርስ ፤ የጠንቋዩ ተፅዕኖ እና ተዓማኒነት ከፍ ይልና ፤ ሕብረተሰቡ በመንግሥት እና በጥረቱ ከማመን ይልቅ ፤ አትሩጥ ጠንቋይ እገሌ ጋር ኺድ ውስጥ ይገባል።

# 2 ዕንቆቅልሹ: ጥንቆላን ዘመናዊነት ሳይሸረው መቅረቱ

ኋላ ቀር በእሚባሉት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሐገራት እንኳን ፤ የእምንኖርበት ዘመን ድህረ የሳይንስ እና የዕውቀት አብዮት የተደረገበት ዘመን በመሆኑ እና ሰዎች በተማሩ እና በሰለጠኑ ቁጥሩ ፤ ሕይወትን እና ተፈጥሮን በሳይንሳዊ መንገድ ለማብራራት የእሚቀድማቸው በመሆኑ ፤ በአንጻራዊነት ጥንቆላ ደግሞ ከአዕምሮ በላይ በሆነ ኃይል ግላዊ እና ማሕበራዊ ችግርን እፈታለኹ የእሚል በመሆኑ ፤ እንደ እዚኹም በአብዛኛው በጠንቋይነት የእሚታወቁ ሰዎች በስነ ምግባሩም ሆነ በትምሕርት ደረጃቸው እዚኽ ግቡ የእሚባሉ ሰዎች ባለመሆናቸው ፤ ዘመናዊነት በተስፋፋ መጠን ጥንቆላ ይዳከማል ብለን እንድናስብ ያደርገናል።

ተግባራዊ ዕውነታው ግን ፤ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላቀር ሐገራት ዕንቆቅልሽ ነው ።

ምክንያቱም፡- ዘመናዊነት ጥንቆላን ማዳከም ሲኖርበት እንዲያውም ግብዓት በመሆን አጠናክሮት ነው የዕሚታየው።

በርካታ የዕውቀት ማዕድ የሆኑ ዩኒቨርስቲዎች ባሉባቸው ፣ የመንግሥት ምኒስትር መስሪያ ቤቶች ማሕበራዊ ሕይወትን ለማሻሻል ይረዳሉ የእሚሏቸውን የፖሊሲ አማራጮችን በእሚቀርጹባቸው ፣ ዘመናዊ ሕክምና እና የፍርድ ስረዓት ባሉባቸው ከተሞች ፤ ጥግጥጉን እና በስውር ሳይሆን ፤ የእለት ተእለት የማሕበረ ኢኮኖሚ ውሳኔ በእሚደረግባቸው ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ፤ የጥንቆላ አሠራር ተሰግስጎ ይታያል።

ኹሉም ባይባልም ፤ በኹሉም የማሕበረሰብ ደረጃ ያሉ ዜጎች ፤ ከሊቁ እስከ ደቂቁ ፤ ምንም እንኳን የዘረዘርናቸው ዘመናዊ ተቋማት ቢኖሩም ፤ ዛሬም ፡- ጥንቆላ ይጎዳኛል ወይንም ይጠቅመኛል ብለው የእሚቆጥሩት ነገር መሆኑ ፤ ጥንቆላ የዘመኑ እንቆቅልሽ ነው።

በእዚኽ ዕንቆቅልሽ በሆነ መንገድ ፤ ዘመናዊ ዓለም ውስጥ በእሚኖሩ ኋላ ቀር ሕብረተሰቦች ውስጥ ፡- በንግድ ላይ የእሚያጋጥሙ እክሎች ፣ የጤና ችግሮች ወይንም በጠቅላላ ግላዊ እና ማሕበራዊ ክስተቶች በጥንቆላ መነጽር ይታያሉ።

እክሎቹ ፣ የጤና ችግሮቹ ፣ ወዘተ በአንዳች ዓይነት የጥንቆላ አሠራር እንደ መጡ እና መፍትኼያቸውም እዚያ እንደ አለ ይታሰባል። አንድ አንድ ግዜ ከፍተኛ የስልጣን ቦታ ላይ ያሉ እና በውጫዊ አቋማቸው ከእንደ እዚኽ ዓይነት ባሕላዊ ዕምነት ተላቀዋል ተብለው የእሚታሰቡ ሰዎች እራሱ ጥንቆላ አንዳች ዓይነት ኃይል እንደ አለው እና እንደ እሚጠነቀቁት ይታይባቸዋል።

በእርግጥ ይኽ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ብቻ ነው ያለው ማለት አይደለም ፤ ምንም እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት እንደ እሚያደርገው ፤ ከግል ሕይወት አንስቶ እስከ ትላልቅ የማሕበረ ኢኮኖሚ ኹኔታዎች ውስጥ ተፅዕኖ የእሚያደርግ ባይሆንም ፤ በጣም አደጉ በእሚባሉት እንደ አሜርካ ባሉት ሐገራትም ፤ ስሙን ፡- ማንፌስቴሽን (Manifestation) ፣ ኢነርጂ (Energy) ፣ ከኮስሞው ጋር መስማማት (Cosmic Alignment) ፣ ወዘተ በእሚሉ ሳይንሳዊ ቃና ባላቸው ቃላት ተደብቆ ይገኛል።

በአጭሩ ቋንቋው ይቀየራል ፤ አሠራሩ ግን እንደ አለ ይቀጥላል።

ጥንቆላ በእዚኽ መልኩ ፤ የዘመናዊነትን ተፅዕኖ እና ብርታት ተቋቁሞ መቀጠል መቻሉ እና በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ደግሞ እራሱን እንደ ትዩዩ የማሕበረ ኢኮኖሚ ችግር ፈቺ አድርጎ ያቆመበት አግባብ ፤ በአግባቡ መመርመር እና ምላሽ ማግኘት አለበት።

በእዚኽ መሠረትም ፤ ጉዳዩን ጠለቅ ብለን ስንመለከተው ፤ ጥንቆላ በእዚኽ መልኩ የዘመናዊነትን ጫና ተቋቁሞ መቆየት የቻለው ፤ ሰዎች ግንዛቤያቸው ስለ አነሰ እና ዓለምን መረዳት ስለ አልቻሉ ሳይሆን ፤ መፍትኼ ያመጣሉ ተብለው የተቋቋሙ ማሕበራዊ ተቋማት መፍትኼ ማምጣት የእሚሳናቸው በመሆኑ ነው።

ከሞላ ጎደል ጥሩ ግንዛቤ አላቸው የእሚባሉ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማምጣት እና መሳካት ሲኖርባቸው ፤ እስከ እነ ጭራሹም እዚኽ ግባ የእሚባል ዕውቀት የለውም የተባለው ሰው በፈተና ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግብ ፤ የፍርድ ቤት ክርክሮች በሕጉ አግባብ ይበይናሉ ተብለው ሲገመቱ ፤ ህልም እና ብያኔ እንደ ፈቺው ሲሆኑ እና ፍትሕ ሲጓደል ፤ በአጠቃላይ ሰዎች መነሾ እና ውጤትን በአግባቡ ማገናኘት ተስኗቸው ፤ ይኽ የወደቀው በእዚኽ ምክንያት ነው ፤ ያንኛው የተሳካላት በእዚያ ምክንያት ነው ማለት ሲሳናቸው ፤ ሰዎች ከዕማይታየው ዓለም የእሚገኝ ማብራሪያ እና መግለጫ ወደ መፈለግ ይገባሉ።

ይኽም ጥንቆላን ፤ ባልታሰበ መንገድ ወደ ትይዩ የማሕበራዊ ችግር ፈቺ ተቋምነት ያሳድገዋል።

ሰዎች ስለ ማሕበረሰባቸው ግልጸኝነት እና አስተማማኝነት ሲሰማቸው ብቻ ነው አንድ ማሕበረሰብ ጤናማ የእሚሆነው። ዜጎች በማሕበረሰባቸው ውስጥ ፦ ይኽ ለምን ሆነ? ለእዚኽ ማነው ተጠያቂው ? ይኽንን ችግር ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ? የእሚሉ ጥያቄዎችን ሲጠይቁ ፤ በግልጽ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ ሊመልሱት ካልቻሉ ፤ ያ ማሕበረሰብ ብዙ ጥገኛ ችግሮችን ማብቀል ይጀምራል።

የአንድ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት አስተማማኝ እና የተረጋጋ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ፤ ከመድሏዊነት በጸዳ እና ኹሉንም ዜጎች በእኩልነት በዕሚያይ መልኩ ፦ ፍርድ ቤቶች አጥፊውን ቀጥተው አልሚውን ይሸልማሉ ፣ ገበያው አወዳድሮ የተሻለውን አምራች ይሸልማል ፣ የሕክምናው ዘርፍ በሽታን በሳይንስ ያክማል።

በእርግጥ ይኽ ማለት ፦ ፍርድቤቶች ፣ ገበያ ወይንም እንደ ሕክምና ያሉ የሞያ መስኮች ፍጹም እና እንከን አልባ ይሆናሉ ማለት አይደለም ፤ ያም አይጠበቅባቸውም ።

ፍጹምነት ባይቻልም ፤ ለዜጎች መተማመን ሊፈጥር በእሚችል ደረጃ ፤ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኺደቶች በእዚኽ አግባብ ነው የእሚሆኑት የእሚል ተገማችነት እንዲኖራቸው ግን የግድ ነው።

ዜጎች ፦ ስልጣኑን የእማይተላለፉት ነገር ግን ችግሮቻቸውን የእሚፈቱበት እና የመፍትኼው መንገድም ከሞላ ጎደል ለኹሉም አንድ ዓይነት ነው ብለው የእሚተማመኑበት ተቋማዊ አደረጃጀት መኖር አለበት።

የአንድ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ግን ይኽ ዓይነቱ ኢመድሏዊ ወጥነት እና ችግር ፈቺነት ሳይኖራቸው ሲቀር ፤ ያን ግዜ የእሚፈጠረው ክፍተት ለጥንቆላ ኢኮኖሚው በር ይከፍታል።

አንድ አንድ ግዜ የተቋማቱ ኢመድሏዊነት ብቻ በእራሱ በቂ አይደለም ፤ ችግር ፈቺም መሆን አለባቸው። በአንድ ሐገር የእሚገኝ የተቋም አወቃቀር በአንጻራዊነት ፍትኃዊ ሊሆን ይችላል ፤ ሆኖም ችግር ፈቺ ካልሆነ እና ችግር ለመፍታት አቋራጩን እሚጋብዝ ከሆነ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው እሚሆነው።

ምክንያቱም ፦ ፍትሐዊነት ችግር ካልፈታ እና ዜጎች ችግር ለመፍታት ፤ አቋራጭ መንገዶችን እንዲጠቀሙ እሚያስገድድ ከሆነ ፤ በተቋም ግንባታው ፍትሐዊነት ቢተማመኑም በችግር ፈቺነቱ አይተማመኑም ማለት ነው።

ስለ እዚኽ፦ **<u>ከአምባገነንነት ወደ ምርታማነት</u>** በእሚለው መጽሐፍ ውስጥ እንደ አስቀመጥቁት ፤ ሐገራት የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውን ደረጃ ፦ ከግል ንብረት ባለቤትነት ፣ ከንብረት ተንቀሳቃሽነት ፣ ከሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ፣ ከንግድ ክፍትነት እና ከበጀት አስተዳደር አንጻር በማሳደግ ፍትኃዊ ብቻ የኢኮኖሚ ዕድገት አስቻይ የማሕብረ ኢኮኖሚ ተቋም መሆን አለባቸው ፤ ፦ ያን ግዜ ስለ ሆነ ፤ ማሕበረሰባቸው ግልጽ በሆነ መንገድ ፤ አምራችነትን በማበረታት ጥገኛ ጥቅመኝነትን በመግፋት ፤ ትርጉም ያለው ማሕበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የእሚችለው።

ምክንያቱም ፦ ለምሳሌ ፦ እንደ ሶሻሊዝም ያለ ፍጹም አምባገነናዊ ስረዓት በማስፈን ፤ በአንጻራዊነት ድህነትን በእኩልነት ማከፋፈል ይቻል ይሆን ይሆናል እንጂ በሶሻሊስታዊ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ግንባታ ዜጎች የእሚፈልጉትን ዓይነት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አይቻልም።

ዜጎች ደግሞ ፤ በመደበኛው መንገድ ኼደው ፤ የፍላጎታቸውን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ካልቻሉ ፤ በኢመደበኛ መንገድም ቢሆን በመኼድ ይቻላል ወይንም ይገባኛል የእሚሉትን የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት መሥራታቸው አይቀርም ፤ ያን ግዜ ፦ የጥንቆላው አሠራር ፤ ኢመደበኛው የመፍትኼ መንገድ እኔ ነኝ ብሎ ይመጣል።

አብዛኛው ሰው ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ሳይንስ ሊህቅ ስለ አልሆነ እና መሆንም ስለ እማይፈልግ ፦ በጥሩ ውጤት ቢመረቅ እንኳን ሥራ ማጣቱን ፣ በቂ የንግድ ዕውቀት እና ልምድ ቢኖረው እንኳን መነገድ ፈልጎ መሥሪያ ቦታ ማጣቱን ፣ ኹሉን ቢያሟላ እንኳን ኮንትራት ማሸነፍ አለመቻሉን ፣ ወዘተ የማሕበረ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ችግር አድርጎ ሊያየው አይችልም።

ዜጋው እንደ እዚኽ ዓይነት ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ችግሮች ሲፈጠሩበት ፤ ይኽ ችግር ያጋጠመኽ እኮ ፤ ሕገ መንግሥቱ ላይ ያለው ይኽ አንቀጽ ወይንም የመሬት ፖሊሲው ላይ ያለው ይኽ አንቀጽ ፤ ጆን ሎክ (John Locke) እንደ አለው ወይንም ማክስ ዌበር (Max Webber) እንደ አለው ፤ ይኽ እና ያ ችግር ስለ አለበት ነው የእሚል ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ማብራሪያ የእሚሰማበት ጆሮ የለውም።

የእሚፈልገው ፦ ስለ ተመረቀ የሥራ ዕድል ፣ የንግድ ሰው ስለ ሆነ የንግድ ሥራ ዕድል ፣ ኮንትራት ማሸነፍ ፣ ወዘተ ፤ በአጠቃላይ መፍትኼ ነው።

የጥንቆላው አሠራርም ፤ ይኽን ችግር የፈጠሩብኽን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ማስተካከል የእሚችል የማሕበረ ኢኮኖሚ ንድፍ ልስጥኽ አይደለም የእሚለው ፤ ይልቁንም ፦ ተመራቂ ብትሆንም ሥራ ያጣኸው ፣

ለመነገድ መሥሪያ ቦታ ያጣኸው ፣ ወዘተ የእሚያግዝኽ ሚስጥራዊ መንፈሳዊ ኃይል ስለ ሌለ ፣ ሰዎች በአንተ ላይ መተት ስለ አስደረጉብኽ ፣ ወዘተ ነው፤ መፍትሔውም እኔ ጋር ነው ብሎ ነው የእሚመጣው።

ይኽን ብታደርግ ፦ በሬ ብታርድ ፣ ወርቅ ብታስገባ ፣ ወዘተ የችግሩን መፍትኼ አመጣለው ፤ የተደረገብኽን መተት አረክሳለኹ ፣ ወዘተ ብሎ ነው የእሚመጣው።

ዜጎች በመደበኛው አካኼድ ኼደው ሊረዱት ላልቻሉት እና ሊገልጹት ላልቻሉት ችግራቸው ፤ ችግርኽን ልትረዳው እና ልትገልጸው ያልቻልከው ፤ ችግርኽ ሰዋዊ ሳይሆን ስውር ፣ መንፈሳዊ ወይንም ምትኃታዊ ስለ ሆነ ነው በእሚል ፤ ግራ መጋባት በነገሰበት "ዓለም" ውስጥ "እርግጠኝነትን እና መፍትኼን" ይዞ ብቅ ይላል።

በእዚኽም አስፈሪ እና ውግዝ የእሚመስለው ወይንም የነበረው ጥንቆላ ፤ በድንገት የእረፍት እና የአዕምሮ ሠላም ምንጭ ሆኖ ይመጣል።

አንድ ዜጋ ፦ ሞያ እና ልምድ ኖሮት ፦ የሐገሪቱ የማሕበረ ኢኮኖሚ ስረዓት ፤ በተበላሸ የንብረት ሕግ ፤ በቀላሉ መሥሪያ ቦታ እሚያገኝበትን ዕድል ሲያጠብበት ፣ በውርስም በችሮታም ተጣጥሮ መሥሪያ ቦታ ሲያገኝ ፤ በተበላሸ የበጀት አስተዳደር የሐገሪቱን የዋጋ ግሽበት እና የወለድ መጠን ሰማይ አውጥቶበት ፤ ብድር በቀላሉ አግኝቶ ንግዱን ማስፋፋት ሲከብድበት ፣ በተባለሸ የንግድ ክፍትነት ሕግ ወደር አልባ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲፈጥርበት ፣ ወዘተ እና ይኽም ውስብስብ የማክሮ ኢኮኖሚ ስንክሳር ፤ የአዕምሮውን ሠላም እና ደስታውን ሲሰርቀው ፤ መሬት እንድታገኝ አደርግኃለው ፣ ብድር እንድታገኝ አደርጋለኹ ፣ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ አደርግኃለው ፣ ወዘተ የእሚለው እና አንድ አንዴም በጥንቆላ ብቻ ሳይሆን ማሕበራዊ ምህንድስናን ከኢመደበኛ አደረጃጀት ጋር አዳብሎ ተጠቅሞ ፤ ማሕበረሰባዊ አወቃቀር ሊፈታው የእሚገባውን ችግር ፤ በአቋራጭ ሲፈታው ፤ ጥንቆላ እራሱን ከውግዘት ወደ ምስጢራዊ መፍትኼነት ያሽጋግራል።

ለእዚኽም ነው ፤ በስም ጥንቆላ ቢባልም እንኳን በተግባር ግን **የጥንቆላ + ማሕበራዊ ምህንድስና + የኢመደበኛ አደረጃጀት ድምር ውጤት ሆኖ** ፤ ለሰዎች መተዳደሪያ እስከ መስጠት የእሚደርስን አሠራር ፤ ተራ ጥንቆላ ብሎ ማጣጣል ፤ ኹኔታውን አለመረዳት ነው የእሚሆነው።

ስለ እዚኽ ፦ ጥንቆላ የማሕበረ ኢኮኖሚ ችግሮችን በሳይንሳዊ መንገድ እፈታለኹ የእሚለው ዘመናዊነት ሳይፈታው የቀረው ፦

- የዘመናዊ ማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት በተሳሰተ የተቋማ አገነባብ ደካማ እና ውጤት አልባ በመሆናቸው
- እንደ እዚኹም የጥንቆላው ኢኮኖሚ ከዘመኑ ጋር አብሮ በመዘመን የዘመናዊነት ትሩፋት የሆኑትን ማሕበራዊ ምህንድስናን እና ኢመደበኛ አደረጃጀትን ደርቦ በመጠቀሙ

ነው።

በእዚኽ መልኩ ነው እንግዲኽ ፤ ጥንቆላ በኢመደበኛ አደረጃጀት እና በማሕበራዊ ምህንድስና አማካኝነት ፤ የመደበኛ ተቋማት ውድቀት የፈጠረውን ክፍተት ተጠቅሞ ፤ ከመጥፋት ይልቅ ከዘመኑ ጋር አብሮ ዘምኖ የቀጠለው።

# 3 ጥንቆላ እንደ ትዩዩ ተቋም (Witchcraft as a Parallel Institution)

በብሉይ ኪዳን (መጽሐፍ ቅዱስ) ውስጥ ከእሚገኙ ግርምት ከእሚያጭሩ ታሪኮች መካከል አንዱ ፤ የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ ደጋግሞ በጣዖት እና በእንግዳ ዓማልክት አምልኮ ኃጥያት የመውደቁ ታሪክ ነው።

በተለይ ደግሞ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ፤ የእስራኤል ሕዝብ ፤ የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የእሚወጣበት ሕዝብ በመሆኑ ልዩ የእግዚአብሔር ሞገስ እና ጥበቃ የተቸረው ሆኖ ፦ ተደጋጋሚ የሆኑ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በእሚታይበት መልኩ ፤ እግዚአብሔር በእሚመርጣቸው እና በእሚሾማቸው ፦ ነብያት ፣ ነገሥታት እና ካህናት ይመራ የነበረ መሆኑ ሲታሰብ ደግሞ ነገሩ ይበልጥ ግርምት ያጭራል።

በመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪክ ከኤድን ፦ የእስራኤል ሕዝብ በታርኩ ፦ ባሕር ሲከፈል ፣ ጠላቶቹ በሽንፈት ሲበተኑ ፣ ምግብ እና ውኃ ምንም በለሌበት ምድረ በዳ ሲቀርብለት አይቷል። ይኽ ደግሞ ፤ በእስራኤል ታሪክ መጀመሪያ አከባቢ ብቻ ተከስቶ በኋላ የተቋረጠ ሳይሆን ፤ ከታላቁ አብረሐም ጀምሮ በተከታታይ ሚልክያስ እስከ እሚባለው ከክርስቶስ አራት እና አምስት መቶ በፊት እስከ ነበረው ነብዩ ሚልክያስ ድረስ የቀጠለ ነው።

ይኽ ኹሉ ግን ተደጋጋሚ የሆነውን የእስራኤልን ፤ ከእግዚአብሔር ተጨማሪ የሆነ የዋስትና ምንጭ በመፈለግ ወደ ጣዖታት እና ወደ እንግዳ አማልክት የመኼዱን ነገር ሊለውጠው አልቻለም።

ለእዚኽ ምክንያቱ ምንድ ነው ካልን ፤ ሕይወት እና ዘመን ከእሚፈጥርባቸው ስጋት ፤ በእግዚአብሔር በመታመን ብቻ መውጣት አልችልም የእሚል ጥርጣሬ እና ፍርኃት ነው።

ጉዳዩ በእዚኽ ስጋት በሞላበት ዓለም ውስጥ የደህንነት ዋስትና የመፈለግ ጉዳዩ መሆኑን ፤ በአንድ ወቅት እስራኤላዊያን "እንደ ሌሎች አሕዛብ" ንጉሥ አንግሥልን ብለው ሲጠይቁ[1] ፤ ጉዳዩ ተፈጥሯዊ የሆነ የሰዎች ዋስትና የመፈለግ ዝንባሌ ውጤት እንደ ሆነ በእሚገባ ያሳያል ብዬ አስባለኹ።

በ1ኛ ሳሙኤል 8፡5 ላይ በእሚከተለው መልኩ እስራኤላዊያን የመጀመሪያውን ንጉሥ የጠየቁበትን ፦

> *"እነሆ ፥ አንተ ሸምግለኃል ፥ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም ፤ አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድን ንጉሥ አድርግልን አሉት።"*

ታሪክ ካየን ነገሩን ይበልጥ እሚያብራራው ይመስለኛል።

እንግዲኽ እስራኤላዊያን ፤ በእስራኤል ታሪክ ታላቅ ከእሚባሉት ነብያት ፤ ለነብዩ ሳሙኤል ይኽን ጥያቄ ሲጠይቁ ፤ ሙሴ ከሞተ በኋላ እና ከሳሙኤል በፊት ለነበረው ከ300 እስከ 450 ለእሚደርስ ዓመት እንደ

ሌሎች አሕዛብ ወይንም ሌሎች ሕዝቦች የእራሳቸው ንጉሥ ሳይኖራቸው እና ድንገት እግዚአብሔር በእሚያስነሳው መስፍን ሥር የኖሩበት ነበር።

ያ ዘመንም ዘመነ መሳፍንት ተብሎ ይታወቃል።

በእዚኽ ከ300 እስከ 450 በእሚደርስ ዘመን ፤ ብዙ የእግዚአብሔር ተዓምራት ያዩበት ቢሆንም ፤ ቋሚ መንግሥት እና መከላከያ ስለ ሌላቸው ፤ በእየ ግዜው ፡- ዘረፋ ፣ ቃጠሎ ፣ ጦርነት ፣ ወዘተ ሲያሰቃያቸው ነው የኖሩት።

ሳሙኤል በመምጣቱ ይኽ ቢቀየርም ፤ እርሱ ሲያረጅ እና ሊተኩት ያሉት ልጆቹ ግን ፤ እጅግ መረን የሆነ ባለጌዎቹ ነበሩ ፡-

> *1 ሳሙኤል 8፡3 "ልጆቹም (የሳሙኤል) በመንገዱ አልኼዱም ፤ ነገር ግን ረብ ለማግኘት ፈቀቅ አሉ ፤ ጉቦን እየተቀበሉ ፍርድ ያጣምሙ ነበር።"*

ስለ እዚኽ፡- የእስራኤል ሽማግሌዎች ስጋት ገባቸው ፤ አንተ ትሞታለኽ ፤ ልጆችኽ መረን ናቸው ፤ እግዚአብሔር አዲስ መስፍን እስኪያስነሳ ልንሰቃይ ነው እና ንጉሥ አንግሥልን ፤ በዘመናዊ ቋንቋ እናስቀምጠው ካልን ፤ ተቋም ገንባልን አሉት።

መጽሐፍ ቅዱሱም እግዚአብሔር ተቋጣ የእሚል ነገር ቢልም ፤ የተቆጣው በጥያቄው ሳይሆን በአጠያየቁ ነው እሚመስለው። ምክንያቱም ፡- ጥያቄውን ሰምቶ ፤ የመጀመሪያውን ንጉሥ ሳያልን አንግሶላቸዋል ፤ ከእዚያም ዳዊትን እና ቤቱን የዘላለም የእስራኤል ነገሥታት አድርጓል ፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ከዳዊት የንግሥና ዘር ነው የወጣው።

እንደ እኔ ፤ እግዚአብሔር እራሱ ፤ ከነብይ አሠራር ወደ ተቋም አሠራር ማደጋቸውን የወደደው እና የእርሱም ኃሳብ ነው የእሚመስለው።

ይኽ የእስራኤላዊያኑ ጥያቄ እንደ ዕሚያሳየው ፤ ጉዳዩ በእግዚአብሔር ፈጽሞ አናምንም የማለት ሳይሆን ፤ መች እንደ እሚነሳ እማያውቁት እንደ ሳሙኤል ዓይነት ሌላ ብርቱ ነብይ እስኪነሳ ፤ በእራሳቸው ዕምነት በእግዚአብሔር ላይ ተደግፈው መኖር የፈጠረባቸው ስጋት ፤ እንደ እግዚአብሔር በዕምነት የእሚቀርቡት ሳይሆን ፤ እንደ ሌሎቹ አሕዛብ ፡- አጠገባቸው ሆኖ የዕሚያዩት እና የእሚዳሠሡት እና በአንዳች መንገድ ሊቆጣጠሩት የእሚችሉትን እና ስጋታቸውን የእሚያረግብላቸው ተቋማዊ አሠራር የመፈለግን ተፈጥሯዊ የሰውን ዝንባሌ ነው።

ይኽ ዓይነቱ ሰዋዊ ስጋት እና ተጋላጭነት ነበር ፤ የካህናት መንግሥት ሆኖ የተመሠረተውን የእስራኤልን ሕዝብ የመጀመሪያውን ንጉሥ የሰጠው።

ከእዚኽ አንጻር ሲታይ ፡- በእዚኽ መልኩ ወደ ሌሎች ትይዩ ፡- ጣዖት ፣ ነገሥታት ወይንም የተወገዙ ተግባራት የመዘር ነገር ፤ የስጋት መጠን ከቁጥጥር ሲያልፍ ፤ ሰዎች ከመደበኛው (በእዚኽ ግዜ ፤ በእግዚአብሔር

ከመታመን) ወደ ሌሎች አማራጭ የመድህን ዋስትና ምንጮች በመኼድ ስጋቱን ለመቅረፍ ይሞክራሉ የእሚል አንድ ጥልቅ ሰዋዊ ባሕሪን ያሳያል።

ሰዎች የእሚያውቁት አካኼድ መፍትኼ አላመጣ ሲላቸው ፤ አማራጭ ያያሉ።

ይኽ ዓይነቱ ዝንባሌ የእስራኤል ሕዝብ ብቻ አይደለም። በመላው የዓለም ሕዝብ ኹሉ ታሪክ ፤ ተመሳሳይነት ያላቸው የጥንቆላ እና የባዕድ አምልኮ ስረዓቶች ተመሣሣይ ሚና ሲጫወቱ እንደ ነበር ታሪክ ያሳያል።

በጥንታዊ ግሪክ ዴልፋይ (Delphi) በእሚባለው ቦታ የነበሩት ኦራክል (Oracle) ይባሉ የነበሩት ጠንቋዮች መንግሥታትን በሐገር ግንባታ እና በጦርነት ጉዳይ ሲያማክሩ ይታያሉ። በጥንታዊ ግብፅ የነበሩ የጣዖት አምልኮ ቀሳውስት እና በባቢሎን የነበሩ ኮከብ ቆጣሪዎች ፤ የዘመኑን እንቆቅልሽ የመፍታት እና መጪዎን ነገር የማመልከት ሥራ ሲሠሩ ነበር። እንደ ሶቅራጠስ ያሉ ታላላቅ ጠቢባን እንኳን ፤ ለጠቢብነታቸው በጠንቋዮች ምስክርነት ይሰጣቸው ነበር።

በጠቅላላው እነ እዚኽ ፤ የጥንቆላ ሥራዎች ፤ ለእነእዚኽ ጥንታዊ ማሕበረሰቦች ፤ እንደ ዛሬው በምስጢራዊ እና በስውር ሳይሆን ፤ የመደበኛው የማሕብረሰቡ የውሳኔ አሰጣጥ ስረዓት አካል በመሆን ፦ ዘመንን ሲተረጉሙ ፣ መፍትኼ ሲያመላክቱ ፣ ምክር ሲመክሩ ፣ ወዘተ ነበር።

ኹኔትዎች ከሰዎች መረዳት እና ማገናዘብ በላይ በመሆን የሰውን የዕውቀት ወሰን ሲፈትኑ ፤ የልዕለ ተፈጥሮ ማብራሪያ ያቀርባሉ ፣ ሕይወት ስጋት ሲሞላባት እና እርግጠኝነት ሲጠፋ ምሪት ይሰጣሉ ፣ በአጠቃላይ ስጋት እና ውጥረት በሞላባት ዓለም የሰውን ልብ እንዲረጋጋ ለማድረግ ይሞክራሉ።

ይኽን በማድረግ ፤ መደበኛ የሆነውን ለዜጎች መተማመን እና እርጋታ ሊሰጥ የእሚገባውን መንግሥታዊ ተቋም የእሚያግዙ ወይንም የእሚተኩ **<u>ትይዩ ተቋማት</u>** በመሆን ፤ ከአንዳች ዓይነት የዕምነት ስረዓት በላይ ይሆናሉ።

ይኽ ዓይነቱ ሚና ፤ በተራው ዜጋ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ አንድ አንድ የማሕበረሰቡን ሊህቃን እና የፖለቲካ አመራሮችንም ሊነካ እና ሊያሳትፍ ይችላል።

ነገሥታት ፣ ጀነራሎች እና የፖለቲካ አመራሮች ምሪት እና ማረጋገጫ ለማግኘት ሲሉ ወደ ጥንቆላ አሠራር ጎራ ማለታቸውን የእሚዘግቡ እና የእሚመሠክሩ በርካታ ታሪካዊ ማስረጃዎች አሉ።

እንዲያውም በጥንታዊው ዓለም ፤ በመደበኛው መንግሥታዊ አመራር እና የጥንቆላን ድጋፍ የመፈለጉ ነገር ለመለየት በእሚያስቸግር መልኩ የተቀላቀሉ ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ይኽን መሰሉ ታሪካዊ ዕውነታ ተንጸባርቋል። ንጉሥ ሳዖል ትልቅ የፍልስጤም ሠራዊት መጥቶበት ፤ አብሮት ያለው ጦር ተመናምኖ እና ምሪት የእሚሰጠው የእግዚአብሔር ነበይ በጠፋበት ወቅት ፤ እጅግ በጣም ሲጨንቀው ፤ እራሱ በሕግ በሞት ያስቀጣል ብሎ ያጠፋውን የሙታን መንፈስ ሳቢ

የእሚባሉትን ሰዎች አገልግሎት ፍለጋ ወደ ጥንቆላው ዓለም ጎራ ብሏል ፤ ይኽንንም 1ኛ ሳሙኤል 28 ከቁጥር 5 ጀምሮ እናገኘዋለን ፡-

*"5 ሳኦልም የፍልስጥኤማውያንን ጭፍራ ባየ ጊዜ ፈራ፥ ልቡም እጅግ ተንቀጠቀጠ።*

*6 ሳኦልም እግዚአብሔርን ጠየቀ፤ እግዚአብሔርም በሕልም ወይም በኡሪም ወይም በነቢያት አልመለሰለትም።*

*7 ሳኦልም ባሪያዎቹን፦— ወደ እርስዋ ሄጄ እጠይቅ ዘንድ መናፍስትን የምትጠራ ሴት ፈልጉልኝ አላቸው፤ ባሪያዎቹም፦— እነሆ፥ መናፍስትን የምትጠራ አንዲት ሴት በዓይንዶር አለች፡ አሉት።*

*8 ሳኦልም መልኩን ለውጦ ሌላ ልብስም ለብሶ ሄደ፥ ሁለትም ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ በሌሊትም ወደ ሴቲቱ መጡ። እርሱም፦— እባክሽ፥ በመናፍስት አምዋርቺልኝ፥ የምልሽንም አስነሽልኝ፡ አላት።*

*9 ሴቲቱም፦— እነሆ፥ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ከምድር እንዳጠፋ ሳኦል ያደረገውን ታውቃለህ፤ ስለ ምን እኔን ለማስገደል ወጥመድ ለነፍሴ ታደርጋለህ? አለችው።*

*10 ሳኦልም፦— ሕያው እግዚአብሔርን! በዚህ ነገር ቅጣት አያገኝሽም ብሎ በእግዚአብሔር ማለላት።*

*11 ሴቲቱም፦— ማንን ላስነሣልህ? አለች፤ እርሱም፦— ሳሙኤልን አስነሽልኝ፡ አለ።*

*12 ሴቲቱም ሳሙኤልን ባየች ጊዜ በታላቅ ድምፅ ጮኸች፤ ሴቲቱም ሳኦልን፦— አንተ ሳኦል ስትሆን ለምን አታለልኸኝ? ብላ ተናገረችው።*

*13 ንጉሡም፦— አትፍሪ፤ ያየሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም ሳኦልን፦— አማልክት ከምድር ሲወጡ አየሁ አለችው።"*

እነ እዚኽ ተደጋጋሚ ባሕሪያዊ ይዘት ያላቸው ክስተቶች ፤ በታሪክ ውስጥ የገኃዱ ዓለም ዕውነታ የሰዎችን ዕምነት እና ስነ ልቦና ሲፈታተን እና ኑሮ ከሰዎች አቅም በላይ ሲሆን ፤ እንደ ጥንቆላ ያሉ ኢመደበኛ አሠራሮች ፤ **ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሴፍቲ ኔት** (**Metaphysical safety net**) ወይንም የደህንነት ዋስትና ሆነው ማገልገል ይጀምራሉ ፤ የእሚል ድምዳሜን ያስከትላሉ።

እንደ ጥንቆላ ያሉ አሠራሮች ፤ ይኽንን አገልግሎት በመስጠት ተፈላጊነታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ የእሚያስችላቸው ፤ መደበኛው ፡- ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊ ፣ አንድ አንዴ እንዲያውም ኃይማኖታዊው ስረዓት እራሱ ፤ ሕብረተሰቡ የእሚፈልገውን እና የእሚጠብቀውን ዋስትና እና ደህንነት መስጠት ሲያቅታቸው ነው።

ከእዚኽ አንጻር ወሳኝ የእሚሆነው ጥያቄ ፤ ጥንቆላ እንደ እሚለው ወይንም እንደ እሚባልለት ዕውነትም አንዳች ዓይነት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል አለው ወይንስ የለውም የእሚለው አይደለም ። ይልቁንም ፡- ሰዎች

መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ይሰጡኛል ብለው የእምያሱባቸውን አገልግሎቶችን እና ጥቅሞች ጥንቆላ ሊሰጠኝ ይችላል ብለው እንዲያምኑ በማድረግ ፤ ጥንቆላ እራሱን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ትይዩ እና ተፎካካሪ አገልግሎት ሰጪ አድርጎ ማቅረብ ይችላል? የእሚለው ይሆናል።

ሕይወት በጥርጣሬ ስትሞላ ፣ ሰው ምን ባደርግ ይሳካልኛል ብሎ ጠይቆ መልስ ሲያጣ ፣ መደበኛ ማሕበራዊ ተቋማት የኢኮኖሚ ስኬት መንገዱ ይኽ ነው ብለው መነሾ እና ውጤትን በአሳማኝ መልኩ አያይዘው ማቅረብ ሲሳናቸው ፤ እንደ ጥንቆላ ያሉ አማራጭ ኢመደበኛ አሠራሮች ጥንካሬ ያገኛሉ።

የጥንቆላ አሠራሮች ፤ ምንም እንኳን የእሚሰጧቸው ምልሶች አስተማማኝ እና ትክክል ባይሆኑም ፤ የእራሳቸውን እና ከመደበኛው የተለየ መልስ መስጠታቸው ግን ግልጽ ነው። ለምሳሌ ፦ ዓለምን የእሚገዛው የጥንቆላ መንፈስ ስለ ሆነ ፤ ሥራ ያጣኸው ድግምት ተደግሞብኽ ነው ፣ የደገመብኽ ይኽ ወይንም ያኽ ሰው/አካል ነው ፣ እኔ ማርከሻውን እደግምልኃለው ፤ የእሚል ዓይነት መልስ ይዘው ይመጣሉ።

ወይንም ይኽ ዓለም በጥንቆላ ኃይል ስለ እሚገዛ ፤ ከጥንቆላ ውጭ ኃብት ወይንም ዕውቀት ማካበት አትችልም ብለው ይመጣሉ።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ መደበኛው ማሕበራዊ ተቋም ፤ በተደጋጋሚ ፈታኝ ለሆኑ የሕይወት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ሲያቅተው እና ሰዎች የስጋት መጠናቸው ሲጨምር ፤ የጥንቆላ አሠራር ይስፋፋል።

በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ አለመረጋጋት እና ስጋት እየጨመረ ሲኼድ ፤ ተፈጥሯዊው አሠራር ሊመልስ ያልቻለውን ጥያቄ በመመለስ ሰዎችን የእሚያረጋጉ አማራጭ አሠራሮች ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ይኼዳል ማለት ነው።

በመሆኑም ፦ ጥንቆላ እንደ አንዳች ዓይነት አጉል ዕምነት ብቻ መታየት የለበትም ፤ ይልቁንም መደበኛ ተቋማት በመዳከም እና በመውደቅ መደበኛ አገልግሎታቸውን መስጠት ባለመቻላቸው የእሚፈጠረውን ክፍተት ፤ ለመጠቀም የእሚፈጠር አርቴፊሻል ኢመደበኛ ተቋማዊ መልስ እንደ ሆነ ነው መታየት ያለበት።

ስለ እዚኽ ኺደቱ ግልጽ ነው ፦ መጀመሪያ የተቋማት መዳከም እና መውደቅ ማሕበራዊ ጥያቄዎችን የመመለስ እና ማሕበራዊ ችግር የመፍታታ አቅማቸውን ያጠፋል ፤ በእዚያን ግዜ በእሚፈጠረው ክፍተት እንደ ጥንቆላ ያሉ ኢመደበኛ አሠራሮች ፤ ክፍተቱን ተጠቅመው እራሳቸውን አማራጭ የመፍትሔ ተቋም አድርገው ያቀርባሉ።

እንደ እዚኽ ዓይነት ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ብዙ ግዜ ሲጀምሩ ፤ ስውር እና ድብቅ ሆነው ነው ፤ ነገር ግን አንድ ግዜ ፦ የሰዎችን ምርጫ በመወሰን እና እድል በማከፋፈል ፤ በማሕበረ ኢኮኖሚ ውስጥ ውጤታማነታቸው እየጨመረ ሲመጣ ፤ ኢመደበኛነታቸው እና ስውርነታቸው ባይቀይርም ፤ የአደባባይ ምስጢር የሆነ ጠንካራ ኃይል ይሆናሉ።

በኺደትም ፦ በተደራጀ መልኩ የእሚመለምሉ ፣ ማበረታቻ እና ቅጣት የእሚሰጡ ፣ የእራሳቸው አስፈጻሚ ያላቸው ይሆናሉ።

እዚኽ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ፤ በግዜያዊነት ለስረዓት ቀውስ እና ውድቀት ምላሽ ሆነው የተፈጠሩት እነ እዚኽ እንደ ጥንቆላ ያሉት ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ፤ ከጭቃ ጎጆነት ወደ ሕንጻነት ያድጉና ፤ አደረጃጀታቸው እና ቀጣይነታቸውን በማጠናከር ፤ አንዳች ዓይነት **<u>የኢኮኖሚ ስረዓት</u>** ወደ መሆን ያድጋሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር እና የመደበኛ ተቋማት አስተማማኝነት በጣም ዝቅተኛ በሆነባቸው ማሕበረሰባት ፤ እንደ ጥንቆላ ያሉ ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ፤ ከጭቃ ጎጆነት ወደ ሕንጻነት የእሚቀየሩበት አግባብ በውል ይታያል።

እንደ እዚኽ ባሉ ማሕበረሰባት ውስጥ ፤ የስኬት ምንጩ ሥራ እና ጥረት ሳይሆን አንዳች ዓይነት ስውር አሠራር እና ኃይል ነው የእሚለው ትርክት ዝም ብሎ ትርክት ብቻ ሳይሆን ፦ የሽያጭ ኺደቶችን ፣ በሰዎች መካከል ያለ ግንኙነትን እና የሰዎችን ተስፋ ፤ የእሚወስን ነገር ይሆናል።

በእዚኽ ግዜ ፤ በጥንቆላ ጉዳይ ፤ ሰዎች ዝም ብለው በወሬ ደረጃ ብቻ አይወሰኑም ፦ በእዚኽ ዕምነት ላይ ተመስረተው እርምጃ ይወስዳሉ (They take action) ፣ ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋሉ ፣ ውሳኔ ይወስናሉ።

ይኽን ዓይነቱን እንደ ጥንቆላ ያሉ ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ከጭቃ ጎጆነት ወደ ሕንጻነት የእሚሸጋገሩበት እና **<u>የጥንቆላው ኢኮኖሚ</u>** ዓይነት ስረዓት የእሚሆኑበት አግባብ ያለውን ተፅዕኖ ለመረዳት ፤ ጥንቆላ ምንድ ነው ከእሚል ወጥተን ፤ ዘመናዊ ጥንቆላ በእንዴት ያለ አግባብ ነው ፤ የተፅዕኖ እና የግብይይት ስረዓት በመሆን እራሱን ወደ ኢኮኖሚ ስረዓትነት የእሚቀይረው የእሚለውን ዕንመልከት።

# 4 የጥንቆላ ኢኮኖሚ አካላት (The Elements of Witchcraft Economies)

የኢኮኖሚ ስረዓት ምንድ ነው ያልን እንደ ሆን ፤ የኢኮኖሚ ስረዓት ፦ አገልግሎት እና ምርት የእሚመመረቱበት እና የእሚከፋፈሉበት ስረዓት እንደ ሆነ ነው ሳይንሱ የእሚነግረን።

አግልግሎቶች እና ምርቶች ደግሞ የእየራሳቸው አቅራቢ እና አምራች እንዲኹም ተገልጋይ እና ሸማች የሆኑ ሰዎች አሏቸው።

በንድፈ ኃሳብ ደረጃ እያንዳንዱ የኢኮኖሚ ስረዓት (Economic system) ሊመልሳቸው የእሚገቡ የተወሰኑ ጥያቄዎች አሉ።

በኢኮኖሚያዊ ስረዓቱ ውስጥ ፤ ተዋንያን ወይንም ተሳታፊዎች እንዴት እንደ **<u>እሚመለመሉ</u>** እና በስረዓቱ ውስጥ የዕድገት መሰላሉን እንዴት እንደ እሚወጡትም አብሮ መቀመጥ አለበት።

አብሮም ፦ ስረዓቱ **<u>የማበረታቻ አሠራሩ</u>** የትኞቹን ተግባራት እንደ እሚሸልም እና የትኞቹን ደግሞ እንደ እሚቀጣ በግልጽ ማስቀመጥም አለበት።

የአምራችነት ፣ የቅጥር እና የሸማችነት **<u>ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን</u>** እንዴት እንደ እሚያከፋፍልም ማስቀመጥ አለበት።

በተዋንያኖች መካከል ያለው **<u>ግንኙነት</u>** በምን አግባብ እንደ ሆነ እና ችግር ሲፈጠር እንዴት እንደ እሚዳኝም መቀመጥ አለበት።

በስተመጨረሻም ፦ ሰዎች በኢኮኖሚ ስረዓት ውስጥ ምን **<u>መጠበቅ</u>** (**Expectations**) እንደ እሚችሉ በግልጽ ተቀምጦ ፤ ተሳታፊዎቹ ፤ ምን ዓይነት ተግባር ምን ዓይነት ውጤት እንደ እሚያስከትል ማወቅ አለባቸው።

ሆኖም ንድፈ ኃሳብ ብቻውን ፋይዳው ትንሽ ነው። አንድ የኢኮኖሚ ስረዓት በአግባቡ ሠርቶ ውጤት እንዲያመጣ ፤ በንድፍ የተቀመጠውን ኃሳብ ወደ መሬት አውርደው በተግባር የእሚተረጉሙ **<u>አስፈጻሚዎች</u>** ያስፈልጉታል።

ያ ሲሆን ነው አንድ የኢኮኖሚ ስረዓት ፤ በንድፈ ኃሳብ ደረጃ የተቀመጡትን ሕጎች በቋሚነት እንዲተገበሩ በማድረግ ፦ የዕድል ማከፋፈል ፣ የተዋናይ መረጣ ፣ የማበረታቻ እና የግንኙነት መርኾዎች እንደው ዝም ብለው የወረቀት ላይ ሕጎች ሳይሆኑ በተግባር ባሕሪን የእሚቆጣጠሩ ተጨባጭ ሕጎች ሊያደርጋቸው የእሚችለው።

ለምሳሌ ፦ ሶሻሊስታዊውን የዕዝ ኢኮኖሚ በመመልከት ፤ እነ እዚኽ የዘረዘርናቸው የስረዓት አካላት (System elements) በግልጽ ማየት እንችላለን።

በሶሻሊስታዊው የዕዝ ኢኮኖሚ ስረዓት ውስጥ ተሳታፊዎች ወይንም ተዋናዮች የእሚመለመሉት እና ወደ ዕድገት የእሚመጡት ፤ ለሶሻሊዝም ርዕዮት በተለይ ደግሞ ለመደብ ትግል አስተሳሰብ እና የካፒታሊዝምን ስረዓት የማጥፋት አስፈላጊነት ላይ ያለ የእማይናወጥ ወገንተኝነት ኖራቸው በመገኘታቸው ነው።

በእዚኹ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ የማበረታቻ አሠራሩ (The incentive mechanism) ለሶሻሊዝም ርዕዮት ፤ በተለይ ደግሞ ለመደብ ትግል አስተሳሰብ እና የካፒታሊዝምን ስረዓት የማጥፋት ትግል ድጋፍ እና አስተዋፆ ማድረግ ሲሆን ፤ ከእዚኽ ርዕዮት ማፈግፈግ ደግሞ እስከ ሞት የእሚደርስ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

ከእዚኽ የተነሳ በሶሻሊስታዊው የዕዝ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ መሰላሉን ተወጣጥቶ ከፍታው ላይ ለመውጣት ፤ ተዋናዩ ለእዚኽ ርዕየተ ዓለም ያለውን ታማኝነት እና ርዕየተ ዓለማዊ ግቡን ለማሳካት ያለውን አስተዋፆ ማሳየት አለበት።

ስለ እዚኽ ፡- በእዚኽ ስረዓት ውስጥ ተሳታፊ የመሆን ዕድል እና ዕድገት ማግኘት የእሚቻለው በትምሕርት ብስለት እና በሞያ ልቀት መመዘኛ ሳይሆን ፤ ለሶሻሊዝም ዓላማ መሳካት ቁርጠኛ መሆንን እና ዓላማውንም ለማሳካት ለእሚደረገው ትግል ጠቃሚ በመሆን መመዘኛ ነው። ለሶሊስታዊው ዓላማ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያላቸው ይመለመላሉ ፣ ዕድገት ያገኛሉ ፤ ለኃላፊነት ይበቃሉ።

የቅጥር ፣ የአምራችነት ፣ የሽማችነት ዕድሎች ፤ ፖለቲካዊም ሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፤ በተማከለ መልኩ በዕቅድ እና በኮታ ይከፋፈላሉ።

በስረዓቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ፤ እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት ፤ ለአንድ ሶሻሊስታዊ ዓላማ የቆሙ ጓዶች የእሚለው መርኽ ይገዛዋል። የመጡበት መደብ እና ለጭቁኑ መደብ ያላቸው ተቆርቋሪነት በጋራ እንዲቆሙ የእሚያደርጋቸው ፤ ከእዚኽ ማፈንገጥ አለ ተብሎ ሲታሰብ ደግሞ በጥርጣሬ የእሚተያዩበት ነው።

አባላቱ ወይንም ተሳታፊዎቹ ከስረዓቱ ምን እንደ እሚጠብቁ ያውቃሉ። ርዕዮተ ዓለማዊ ወገንተኝነት ፣ ለዓላማው መሳካት ያለ ቁርጠኝነት ፤ ስረዓቱ የእሚፈልጋቸው ነገሮች ናቸው።

በስተመጨረሻ ፤ ይኽን ንድፈ ኃሳባዊ የስረዓት ቅርጽ ፤ ወደ መሬት አውርዶ በተግባር የእሚለውጣቸው ሕጋዊ እና የማስገደጃ አሠራር አለ። በስረዓቱ ንድፍ መሠረት ወጥነት ባለው መልኩ ፡- የምልመላው ሥራ እንዲሠራ ፣ አልሚው እንዲሸለም እና አጥፊው እንዲቀጣ ፣ ዕድሎች እንዲከፋፈሉ እና ግንኙነቶች እንዲመሩ ፤ ስረዓቱ በአስፈጻሚ መንግሥት የማስገደድ አቅም ላይ ይደገፋል።

በእዚኽ አግባብ ፤ የስረዓቱን ንድፈ ኃሳባዊ አሠራር በተግባር እንዲውል ያደርጋል።

በተመሳሳይ የካፒታሊዝም ስረዓትም ውስጥ የስረዓቱን አካሎች (System's Elements) ማየት እንችላለን ፤ ምንም እንኳን የስረዓቱ ንድፈ ኃሳብ ከሶሻሊዝም ቢለይም።

በካፒታሊዝም ስረዓት ውስጥ ፤ በመርኽ ደረጃ ፤ ተሳትፎ ያለምንም መሥፈርት ለኹሉም ክፍት ነው። ተዋንያኖች በስረዓቱ ውስጥ ማምረት እና መሸጥ በእሚችሉበት ልክ እንደ ሠራተኞች ፣ እንደ ነጋዴ ወይንም እንደ ኢንቨስተር ይሳተፋሉ። ምንም እንኳን የተወሰኑ ገደቦች ቢኖሩም ፤ ስረዓቱ በአንጻራዊነት ለኹሉም ክፍት ነው።

በካፒታሊዝም ስረዓት ውስጥ በመሠረታዊነት የኢኮኖሚ ዕድሎች እና ጥቅሞች የእሚከፋፈሉት በፓርቲ ውሳኔ ሳይሆን በገበያ ነው።

ኃብት ፣ ሥራ ፣ እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች የእሚከፋፈሉት ፦ የዋጋ ስረዓት ፣ ውድድር እና በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ግብይይት ፤ በጋራ ሆነው በእሚፈጥሩት አሠራር ነው።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ አዲስ ወይንም ተጨማሪ እሴት (Value) መፍጠር የእሚችሉ ፣ ወጪ መቀነስ የእሚችሉ ፣ እና አዲስ ያልተሟላ የሰው ጥየቃ ያገኙ ሰዎች (Those who identify unmet demand) ከሌሎች ይልቅ የኢኮኖሚ ዕድል የማግኘት ነገራቸው ይጨምራል።

የማበረታቻ ስረዓቶች በአብዛኛው ቁሳዊ ጥቅሞች ናቸው። ትርፍ ፣ ገቢ እና ኃብት ማከማቸት ናቸው በዋናነት የሰዎችን ባሕሪ የእሚቀርጹት። ስኬታማነት የእሚሸለመው ገንዘብ እና ገንዘብ የእሚገኝባቸውን ዕድሎች በማስፋት ነው። ውድቀት የገንዘብ ክስረት ፣ ከገበያ መውጣት ወይንም የተሳትፎ መቀነስ ያስከትላል።

በተዋናዮች መካከል ያለ ግንኙነት በንግድ ውል እና በመገበያየት ሕግ ነው እሚመራው። የንግድ ውሎች እንዲከበሩ ፣ ዋጋዎች ትክክለኛ እንዲሆኑ ፤ ሰዎች እርስ በእርሳቸው መተዋወቅ የለባቸውም ፤ እነ እዚኽ ነገሮች በግል ትውውቅ ወይንም በአንድ ዓይነት የርዕዮተ ዓለም ካድሬነት ወይንም ታማኝነት ላይ ከእሚመሠረቱ ይልቅ ለኹሉም ዕኩል በእሚሠራ ሕግ አማካኝነት ይሠራሉ።

ሰውም ከስረዓቱ ምን እንደ እሚጠብቅ ያውቃል። ምንም እንኳን ኹሉም ውጤቶች አስቀድመው ይታወቃሉ ባይባልም ፤ ነገር ግን ውጤትን የእሚወስኑት እንደ ውድድር ፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ግብይይት እና ይኽም ሕጋዊ ከለላ እንደ አለው ፤ ስለ እሚታወቅ ፤ ሰዎች ፦ ማቀድ ፣ ኢንቨስት እና ስፔሻላይዝ ሊያደርጉ በእሚችሉበት ደረጃ በአንጻራዊነት እርግጠኝነት አለው።

በስተመጨረሻም ፦ በካፒታሊዝም ስረዓት ውስጥ ንድፉ ወደ መሬት የእሚወርድበት እና ተፈጻሚነት የእሚያገኘው ፦ ውሎች መከበራቸውን ፣ የንብረት ባለቤትነት መከበሩን ፣ እና አለመግባባቶች መፈታታቸውን በእሚያረጋግጡ ፦ በፍርድ ቤቶች ፣ በመንግሥታዊ ተቆጣጣሪ አካላት (Regulatory bodies) ፣ እና እንደ ባንክ ባሉ የገንዘብ ስረዓቶች (Financial systems) ነው።

በእዚኽ መልኩ ነው ካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ገለልተኛ በሆነ እና በሰዎች ትውውቅ ወይንም መቀራረብ ላይ ባልተመሠረተ መልኩ የእሚያካኺደው።

በካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሲስተም ውስጥ ሰዎች ሲሳተፉ ፤ ውጤታቸው ሊለያይ ይችላል ፤ ሆኖም ኹሉም ሰው ፤ ምስጥራዊ ሳይሆን ግልጽ በሆነ መንገድ በተቀመጠ እና ሊመረመር በእሚችል መልኩ ፤ ውጤቶች የመጡበትን መንገድ ያውቃሉ።

እነ እዚኽ ለማነጻጸሪያነት ያቀረብናቸው ፦ ሶሻሊስት ሆኑ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ስረዓቶች አንድ የጋራ መርኽ አላቸው እርሱም ፦ የኢኮኖሚ ሲስተሞች ምንም እንኳን የፍልስፍና ልዩነት ቢኖራቸውም ፦ የምልመላ እና የዕድገት መርኾች ፣ የኢኮኖሚ ዕድሎች ማከፋፈያ መርኾች ፣ የማበረታቻ ስረዓቶች ፣ ግንኙነቶች የእሚመሩበት መርኽ እና እነ እዚኽ የሲስተሙ ሕጎች በእንዴት ባለ አግባብ እና በማን እንደ እሚተገበሩ ማስቀመጥ አለባቸው።

ስለ እዚኽ፦ ለምሳሌ ፦ የካፒታሊዝም እና የሶሻሊዝም ሲስተሞች ከተለያዩ የተለያዩት ፤ በሲስተሙ ውስጥ ፤ እንደ ማበረታቻ ስረዓት ፣ እንደ ዕድል ማከፋፈያ ሕግ ፣ ወዘተ ያሉ የተለያዩት የሲስተሙ ንዑስ ክፍሎች በመኖራቸው እና በአለመኖራቸው (Existence or absence of certain Systemic elements) ሳይሆን ፤ እነ እዚኽ ንዑስ ክፍሎች በአቀናጁበት መንገድ ነው።

የእሚታወቁትን እና መደበኛዎቹን እንደ ሶሻሊዝም እና ካፒታሊዝም ያሉ የኢኮኖሚ ሲስተሞቹን በእዚኽ መልኩ ከተረዳናቸው ፤ በአንጻራዊነት ስውር እና ኢመደበኛ የሆኑትን ለመረዳት ይቀላል።

እንግዲኽ ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ በአንድ አንድ ኋላ ቀር ሊባሉ በእሚችሉ ማሕበረሰቦች ውስጥ ፤ መደበኛ የእሚባሉት ተቋማት ቢኖሩም ፤ በተጨባጭ ግን ኹል ግዜ እነርሱ ብቻ አይሆኑም ኢኮኖሚያዊ ውጤቶችን የእሚወስኑት ፤ ምክንያቱም ፦ ተቋሞቹ ደካሞች እና ወጥነት የእሚጎድላቸው በመሆኑ።

እንደ እዚያ በእሚሆንበት ግዜ ፦ ከመደበኛው ሲስተም ትይዩ ሌላ ኢመደበኛ ኢኮኖሚያዊ ውጤቶችን ለመወሰን የእሚፈልግ ሌላ ሲስተም ብቅ ይላል።

እነ እዚኽ ሲስተሞች በአዋጅ የተቋቋሙ እና በመንግሥት አካል የጸደቀ የእሚታወቅ መመሥረቻ ደንብ የላቸውም ፤ ሆኖም በአዋጅ የተቋቋሙትን መደበኛ ተቋማት ሚና በትይዩነት ወይንም በመተካት ለመጫወት ይፈልጋሉ።

ተዋናይ ይመለምላሉ ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች ያከፋፍላሉ ፣ የእራሳቸው የማበረታቻ አሠራር ያመጣሉ ፣ ብዙ ግዜ ስውር በሆነ መንገድ ፤ የሲስተማቸውን መርኽ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣሉ።

የጥንቆላው ኢኮኖሚም ይኽን ዓይነት ባሕሪ ያለው እና እነ እዚኽ ኢመደበኛ ሲስተሞች በእሚመጡበት መንገድ የእሚመጣ ነው።

የጥንቆላ ኢኮኖሚ መደበኛ ዕውቅና ያለው የኢኮኖሚ ስረዓት አይደለም። በሕገመንግሥት ፣ በፖሊሲ ሰነዶች ወይንም በኢኮኖሚክ ሳይንስ ጥናት ውስጥ ውክልና የለውም። በተግባር ግን ፦ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች የእሚከፋፈሉበትን አግባብ ፣ ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች የእሚወሰኑበትን አግባብ ፣ እና ማሕበረሰብ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ምን ሊጠብቅ (Defines Expectations) እንደ እሚገባ ፤ ይወስናል።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ ልክ ካፒታሊስታዊ እና ሶሻሊስታዊ የኢኮኖሚ ስረዓቶችን በእምንረዳበት አግባብ ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚም ልንረዳው እንችላለን።

**ተዋንያን/ተሳታፊዎች**

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ለኹሉም ክፍት አይደለም ፤ ሆኖም በከፍተኛ ደረጃ የጥቂቶች ነው ማለት ግን አይደለም። ተሳታፊዎቹ ፡- ጠንቋዮች ፣ ጠንቋይ አገናኝ ደላሎች ፣ የኢመደበኛ አደረጃጀቱ ተሳታፊዎች ፣ የጥንቆላ አገልግሎት ፈላጊዎች እና በጥንቆላ ኢኮኖሚ አሠራር ተጎጅዎች ናቸው። ተሳታፊዎቹ የእሚመረጡት በአብዛኛው በጥንቆላ በማመናቸው ፣ ለጥንቆላው ኔትወርክ ባላቸው ቅርበት ፣ ባለባቸው ችግር ወይንም ደግሞ አንድ በጥንቆላ ኃይል ሊያሳኩት የእሚፈልጉት ነገር በመኖር ፤ መመዘኛ ነው።

አንዳንዶች ፡- ንግዳቸው ገበያ ስለ አጣ ፣ ሥራ መቀጠር ስለ እሚፈልጉ ፣ የጤና ችግር ስለ አጋጠማቸው ወይንም አንዳች ዓይነት እክል በግል ሕይወታቸው ስለ አጋጠማቸው ፤ ለእዚያ እርዳታ በመፈለግ ነው ወደ ጥንቆላው ኢኮኖሚ የእሚመጡት። ሌሎች ደግሞ የጥንቆላ አገልግሎት ለእሚፈልጉ ሰዎች የጥንቆላ አገልግሎት በመስጠት ነው ፤ እንደገና ሌሎች ደግሞ የጥንቆላ አገልግሎት ፈላጊዎችን እና የጥንቆላ አገልግሎት አቅራቢዎችን በማገናኘት እና የጥንቆላው ኢኮኖሚ አስፈጻሚ በመሆን ነው ወደ ጥንቆላ ኢኮኖሚ ውስጥ የእሚገቡት።

**የኢኮኖሚያዊ ዕድል ድልደላ**

በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ ዕድሎች በግልጽ በእሚታወቅ ሕግ ወይንም በነጻ ገበያ ውድድር አይደለም የእሚደለደሉት ፤ ይልቁንም ኢመደበኛ እና ምስጢራዊነት በበዛበት መንገድ ነው የእሚደለደሉት።

የሥራ ዕድል ፣ የንግድ ፈቃድ ፣ ኮንትራት ወይንም ሌሎች የኢኮኖሚ ጥቅሞች የእሚገኙት ፤ በጥንቆላው ተፅዕኖ ፣ በጥንቆላ ደላሎች ድጋፍ ወይንም በስውሩ የጥንቆላ መረብ ውስጥ ባለ አሠራር ነው። በአብዛኛው በጥንቆላው መንፈሳዊ ኃይል የተገኘ ስኬት ተብሎ የእሚነገረው ስኬት ምን አልባት ፤ ድርብርብ የጥንቆላው መረብ ተሳታፊዎች ብዙ የተቀናጀ እንቅስቃሴ አድርገው ያመጡት ሊሆን ይችላል።

**ማበረታቻው**

የጥንቆላው ኢኮኖሚ የማበረታቻ አሠራር ከመደበኛው ኢኮኖሚ የማበረታቻ አሠራር በእጅጉ ይለያል።

ሰዎች የጥንቆላ ኢኮኖሚ ተሳታፊ የእሚሆኑት ፡- ፍርኃት ፣ ተስፋ እና አንዳች ዓይነት ልዩ ጥቅም አገኛለኹ የእሚሉ እሳቤዎች ተዳምረው በእሚፈጥሩት ግፊት ነው። ተሳታፊዎቹ ፡- አንድ ከእሚያሰጋቸው ነገር ጥበቃ ይፈልጉ ይሆናል ፣ ከደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ይፈልጉ ይሆናል ወይንም ተፎካካሪያቸውን ማሸነፍ ይፈልጉ ይሆናል። ምንም እንኳን ውጤቱ አስተማማኝ ላይሆን ቢችልም ፤ የአጋንንቱ ዓለም በእነ እዚኽ ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ ፈጥሮ እነርሱ የእሚፈልጉትን ነገር እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል የእሚለው ዕምነት ትልቅ ማበረታቻ ነው።

በተመሳሳይ የጥንቆላ አገልግሎት የእሚሰጡት ሰዎች ፡- ኃይለኛ ጠንቋይ መባል የእሚሰጠው ዝና ፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ የመሆን ጉጉት እና የገንዘብ ጥቅም ነው የእሚያማልላቸው። እነርሱ ጋር መጥቶ ፡- ከሕመም

ተፈወሰ ፣ ገንዘብ አገኘ ፣ ትዳር አገኘ ፣ ወዘተ የእሚሉ ምስክርነቶች ፤ ዕውነት ሆኑ ድራማ ፤ እንደ ማስታወቂያ ሌሎችን በመሳብ ፤ ጠንቋዮቹን ይበልጥ ያጠናክራቸዋል።

**የተሳታፊዎች ግንኙነት (Relationships)**

በጥንቆላው ኢኮነሚ ውስጥ ግንኙነቶች በከፍተኛ ደረጃ ፤ በግል ቅርርብ እና ትውውቅ ላይ የተመሠረተ ነው። ከትውውቅ የእሚመጣ መተማመን ፣ ምስጢረኝነት እና ታማኝነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

በገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ኹለት ሰዎች ከእዚኽ በፊት ምንም መተዋወቅ ሳይኖራቸው መገበያየት ይችላሉ ፤ በጥንቆላ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ ማን በማን በኩል መጣ ፣ ማን ታማኝ ነው ፣ ማን በጥንቆላ ኢኮኖሚ ኔትወርክ ውስጥ ምን ማድረግ ይችላል ፣ ወዘተ የእሚሉት ነገሮች ወሳኝ ናቸው።

ዝም ብሎ መጠንቆል እና ማስጠንቆል እሚባል ነገር የለም።

በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ የመረጃ ፍሰት የእሚደረገው በኢመደበኛ ኔትወርኩ አማካኝነት በተመረጠ እና በተመጠነ መንገድ ነው ፤ ግንኙነት የእሚመሠረተው እና የእሚጸናው ፤ ተደጋግሞ በመገናኘት እና በተደጋጋፊነት (Mutual Dependence) ላይ ነው።

**መጠበቅ (Expectations)**

ሰዎች በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ ደጋግመው መሳተፋቸው ፤ ከስረዓቱ ምን መጠበቅ እንደ እሚችሉ ያሳውቃቸዋል።

ተሳታፊዎች በእሚኖሩበት ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ ስኬት ይኹን ውድቀት ፦ በጥረት ፣ በክህሎት ወይንም በመደበኛ ሕጎች ሳይሆን ፤ በስውር ኃይሎች ተፅዕኖ እንደ እሚመጣ ቀስ በቀስ እያወቁ ይኼዳሉ። ይኽም ውሳኔ የእሚወስኑበትን መንገድ ሙሉ በሙሉ ይቀይርባቸዋል። አንድ ግዜ ይኽን ከተረዱ በኋላ ፤ ገንዘባቸውን እራሳቸውን በሞያ ለማሳደግ ወይንም የድርጅታቸውን አቅም ለማሳደግ ከማዋል ይልቅ ፦ ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ፦ ጥበቃን ፣ ተፅዕኖን ወይንም ሌላ ልዩ ጥቅምን ለመግዛትም ይጠቀሙበት ወይንም ኢንቨስት ያደርጉት ይጀምራሉ።

**ማስፈጸም (Enforcement)**

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ምን አልባት እንደ ካፒታሊዝም እና ሶሻሊዝም ካሉት የገኃድ ኢኮኖሚዎች ይልቅ ለጥቂት ተገልጋዮቹ ብቻ ቢሆንም ውጤት የእሚያመጣው ፤ የእራሱን ቀጣይነት የእሚያረጋግጠው ከጥንቆላው በላይ በኢመደበኛ አደረጃጀቱ እና በማሕበራዊ ምህንድስና አቅሙ ነው።

የእሚያስፈጽምበት መንገድም ኹል ግዜ ግልጽ እና የተማከለ አይደለም። የእሚጠቀምባቸው መንገዶች ፦ ማሕበራዊ ጫና በመፍጠር ፣ ስም እና ዝና በማጥፋት ፣ ከኔትወርክ በማስወጣት ወይንም ደግሞ ኔትዎርኩ በእሚያደርገው የተቀናጀ አሠራር ሊሆን ይችላል።

እንዲያውም ፡- አንድ አንድ ግዜ ፤ ተሳታፊዎች የጥንቆላው ኢኮኖሚ የእሚያዛቸውን ነገር የእሚያደርጉት ፤ አስገኝላችኋለው ያለውን ጥቅም ስለ አስገኘላቸው ሳይሆን ፤ ትዕዛዝ እሚቢ ማለት የእሚያስከትለውን ቅጣት ወይንም የእሚያስከፍለውን ዋጋ ፈርተው ሊሆን ይችላል።

በእዚኽ መልኩ ነው ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ተዓማኝነቱን እና ቀጣይነቱን የእሚያረጋግጠው።

**የጥንቆላው ኢኮኖሚ በጠቅላላው**

ስለ እዚኽ ፡- እንደ ምልመላ ስረዓት ፣ ዕድል ማከፋፈያ መርኽ ፣ ማስፈጸሚያ መንገድ ፣ ወዘተ ያሉትን የጥንቆላ ኢኮኖሚ አካላት (System Elements) ስንመለከት ፤ የጥንቆላ ኢኮኖሚ አንዳች ዓይነት ባሕላዊ ዕምነት ብቻ ሳይሆን ፤ ተቋማዊ አደረጃጀትም እንደ ሆነ ዕናያለን።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፡- አንድ መደበኛ የኢኮኖሚ ስረዓት እንደ እሚያደርገው ፡- ዕድል ይደለድላል ፣ ማበረታቻዎችን ምን እንደ ሆኑ ይወስናል ፣ ውጤትችን ይወስናል።

የእዚኽ ውጤትም እጅግ ጉልኽ ነው። ሲስተሙ በእዚኽ መልኩ እየሰፋ ሲኼድ ፤ ግለሰቦች ስኬትን ሆነ ውድቀትን ፤ በጥንቆላው መነጽር የማየታቸው ነገርም አብሮ እየሰፋ ይኼዳል።

መደበኛ ተቋማት ፍትኃዊ እና ገለልተኛ አሠራር እና ሕግ መተማመን ይሸረሸራል ፤ በአንጻሩ በኢመደበኛ ኔትዎርክ እና በስውር አሠራሮች የመደገፍ ነገር እየጨመረ ይኼዳል።

በእንደ እዚኽ ዓይነት ኹኔታ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ስጋት ይበዛዋል ፣ ግልጽነት ይጎድለዋል ፣ ከእዚያ በተጨማሪም በግልጽ በእማይታወቁ እና ተጠያቂነት በሌላቸው እና ሊመረመሩ በእማይችሉ ስውር ኃይሎች ላይ ይደገፋል።

ስለ እዚኽ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ በእዚኽ መልኩ መረዳት ያስፈልጋል ፡- በሰዎች ላይ ለመፍረድ እና ለማጣጣል ሳይሆን ፤ ይልቁንም የጥንቆላው ኢኮኖሚ እራሱን እንዴት ትይዩ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋም አድርጎ እንደ አቀረበ ለመረዳት።

# 5 የጥንቆላ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ምንጭ

አንድ የኢኮኖሚ ሲስተም ፤ ዘመናዊዎቹን ጨምሮ ፤ ያለ አንዳች አስቻይ እና መነሻ ምክንያት ከባዶ አይመነጭም። ኢኮኖሚያዊ ሲስተሞች ብዙ ግዜ ፡- ከእነርሱ በፊት የነበሩ ኢኮኖሚያዊ ስረዓቶች በዝግመታዊ ለውጥ ወይንም በውድቀታቸውም ምክንያት ያመጡዋቸው ፤ ታሪካዊ ውጤቶች ናቸው።

የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ በዩናይትድ ኪንግደም ወይንም በዩናይትድ ስቴትስ የመጣበት አግባብ ይኽን ያሰየናል።

በታላቋ ብሪታንያ የፊውዳል የኢኮኖሚ ስረዓት እንደ ፊውዳሊዝም የጉልበት እና የእህል ግብር ሳይሆን ቀጥታ የገንዘብ ግብር ሰብሳቢ ወታደራዊ (fiscal-military) መንግሥት ወደ መሆን የተለወጠው ፤ በፊውዳሊዝም ስረዓት ሲበዘበዝ የነበረው ገበሬ ሆ ብሎ በአመጽ በመነሳቱ ሳይሆን የወቅቱ የሐገሪቱ ባለኃብቶች እና ሊህቃን የፖሊሲ ለውጥ በማድረጋቸው የመጣ ነው።

ለምሳሌ ፡- በእንግሊዝ የኢንክሎዠር አክት (Enclosure Act) ወይንም ኹሉም ሰው በጋራ የእሚጠቀምባቸውን መሬት በማጠር ለግል የማቅረብ አካኼድ ፤ ጭሰኞች ፡- ከብት እሚያስግጡበት ፣ ውኃ የእሚያገኙበት ፣ እንጨት የእሚያገኙበትን ፣ አንድ አንዴም ደርበው የእሚያርሱትን መሬት ፣ ወዘተ ዕድል በማጥበብ ግብርና ለንግድ (Commercialization) ሲሠራ እንጂ ለእለት ተእለት ጉርሥ ሲሠራ እንደ አያዋጣ ማድረጉ ፤ በእንግሊዝ ዘመነ ፊውዳሊዝም አብቅቶ ዘመነ ኢንደስትራላይዜሽን እንዲጀምር አንድ ምክንያት ነበር።

እንደዛውም ፡- የዘውዳዊውን ስረዓት ስልጣን የእሚገድቡ ፤ የፓርላማ አሠራር እና እንደ ባንክ ኦፍ ኢንግላንድ (Bank of England) ዓይነት በዓለም የብሔራዊ ባንክ ታሪክ ከሲውድኑ በመቀጠል ኹለተኛ የሆነው የእንግሊዝ ብሔራዊ ባንክ መቋቋሙ ፤ በሐገረ እንግሊዝ የግል ንብረት የበለጠ ዋስትና እያገኘ እና የብድር አገልግሎት እየተስፋፋ መምጣቱም ሌላው ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም የተደረገውን ሽግግር ያገዘ ተቋማዊ ለውጥ ነበር።

ከእዚኽም የተነሳ ፡- ለምሳሌ ፡- የእንግሊዝ መንግሥት ብድር ከተበደረ አበዳሪው ብድሩ እንደ እሚከፈለው እርግጠኛ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡- ፓርላማው ንጉሡ ብድር አልከፍልም እንደ አይል ስለ እሚያደርገው። ያም የንብረት (ያበደሩት ብድር) ዋስትና እንዲያገኝ ያደርጋል። ብሔራዊ ባንክ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆኖ ፤ ብር እንደ አሻው እሚያትም ከሆነ ፤ በዋጋ ግሽበት የዜጎች ገንዘብ ዋጋው እንዲያጣ በማድረግ በግል ንብረት ላይ ስጋት ይፈጥራል ፤ በእንግሊዝ ግን ባንኩ ገለልተኛ ስለ ሆነ ፤ ረጅም ማቀድ ፣ መበደር ፣ ወዘተ ተቻለ።

ይኽ ወደ ካፒታሊዝም የተደረገ ለውጥ ግን በጭሰኞች አብዮት አልመጣም ፤ እንዲያውም ጭሰኞች በለወጡ ኺደት ከመሬታቸው ተፈናቅለው በወቅቱ በማቆጥቆጥ ላይ ወደ ነበሩት ኢንደስትሪዎች ውስጥ በሠራተኝነት እንዲቀጠሩ ነው የሆነው።

ስለ እዚኽ ፦ ከእንግሊዝ አንጻር ከአየነው ፤ ካፒታሊዝም ከታች ወደ ላይ በተደረገ ግፊት ሳይሆን ፤ ይልቁንም በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በወሰዱት የፖሊሲ ምርጫ የመጣ ሆኖ ነው የእምናገኘው።

በአንጻሩ ፤ ካፒታሊዝም በአሜሪካ የመጣበትን መንገድ ካየን ፤ ውጫዊ የሆነ ኃይል የፈጠረውን ኢኮኖሚያዊ ገደብ መቃወም ያመጣው እንደ ሆነ ነው የእምናየው።

በአሜርካን ሐገር በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ሆነው የነበሩ አሜሪካዊ ሊህቃን እና የተወሰኑ ንዑስ ከበርቴዎች (Middle Class) የእንግሊዙ ዘውዳዊ ስረዓት በእሚከተለው የግብር እና የመርከንታሊስት (Mercantalist) ፖሊሲ ምክንያት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እየገደበ እንደ ሆነ ተሰማቸው።

የአሜሪካው አብዮት ፤ በተወሰነ መልኩ ፤ ይኽንን ገዳቢ መዋቅር ለማፈራረስ መሞከር ነበር። ምክንያቱም ፦ አብዮቱ ከተካኼደ እና አሜሪካ ከእንግሊዝ ቀኝ ግዛት ነጻ ከወጣች በኋላ ፤ አሜርካን በጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ብቻ ገድቧት የነበረውን የእንግሊዙን የቀኝ ስረዓት ገደብ በማንሳት ፤ የአሜርካን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የእሚያረጋግጡ ፦ አሜርካዊ ፋብሪካዎችን መክፈት ፣ ከሌሎች ሐገራት ጋር እነርሱን በእሚጠቅማቸው መንገድ መነገድ ፣ ወዘተ በመቻል ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥቅም አግኝተዋል።

የቀድሞው የእንግሊዙ መንግሥት ይጠቀምበት የነበረው ገዳቢ የኢኮኖሚ አሠራር ተመልሶ እንደ አይመጣም ፤ በሕገመንግሥታቸው ውስጥ የአዕምሮ ንብረት እንደ ቁሳዊ ንብረት የእሚያከበር አንቀጽ በመጨመር ፤ ነጋዴዎች አይደለም ለቁሳዊ ኃብታቸው ለአዕምሯዊ ፈጠራቸው ራሱ ዋስትና እንዲያገኙ በማድረግ ፤ ለካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ግንባታ አመቺ ኹኔታ ፈጠሩ።

ከነጻነት በኋላ የነበረችው አሜሪካ የኢኮኖሚ ዕድሎችን ለኹሉም ዜጋ በእኩልነት እምታከፋፍል ነበረች ባይባልም ፤ ምንም በእማያጠራጥር መልኩ ግን አሜርካ በእንግሊዝ ቀኝ ግዛት ሥር ከነበረችበት ግዜ አንጻር ሲታይ ፤ በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል ነበር።

ይኽም በአሜርካ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ እንዲያድግ የተመቻቸ ኹኔታ ፈጠረ።

ተመሳሳይነት ያለው ኺደትም በራሺያ ታሪክ ይታያል።

የራሺያው አብዮት የራማኖቭ ዘውዳዊ እና አምባገነናዊ ስረዓት (Romanov autocracy) በግትር እና በዝባዥ አካኼዱ በሕዝብ ዘንድ የፈጠረው ቅሬታ ውጤት ነበር።

በራሻም ልክ እንደ አሜርካ ኹሉ ፤ አንድ ከተደላደለ እና ሰፊ የብዝበዛ መዋቅር በመዘረጋት በግለሰብም ሆነ በማሕበረሰብ ደረጃ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከገደበ ስረዓት ለመላቀቅ መፈለግ ነበር ፤ አብዮቱን ያስከተለው።

ሆኖም በራሻም እንደ አሜርካው ኹሉ ፤ ነባራዊው ስልጣን የፈጠረውን ኢኮኖሚያዊ ገደብ ለማንሳት ለውጥ ቢቀሰቀስም ፤ ችግሩን ለመፍታት ግን የተለየ እና ፍጹም ተቃራኒ ሊባል የእሚችል መንገድ ነበር የመረጡት።

ምክንያቱም ፦ አሜርካኖች የኢኮኖሚ ብዝበዛን ለማስቆም መፍትኼው የግል ንብረት ባለቤትነት መብትን እና የግብይይት ውልን ማክበር ነው ሲሉ ፤ በራሺያ ደግሞ የግል ንብረት ባለቤትነት መኖር ነው ለኢኮኖሚ ብዝበዛ የእሚያጋልጠው በማለት ፤ ኢኮኖሚያዊ ጭቆና እና ብዝበዛ እንዲጠፋ የግል ንብረት ባለቤትነት ይታገድ የእሚለውን የሶሻሊዝም መስመር ነበር የመረጡት።

ውጤቱም በራሺያ የዕዝ ኢኮኖሚን ማስከተል ነበር ፤ እርሱም ኼዶ ኼዶ እንደ ቀድሞው የዘውዳዊ የብዝበዛ ስረዓት የእራሱ የሆነ ግግርነት እና ቆሞ ቀርነት አስከተለ።

በካፒታሊዝም እና በሶሻሊዝም መካከል ልዩነት መኖሩ ግልጽ ቢሆንም ፤ ኹሉተም ግን ፦ እንደ ፊውዳሊዝም ፣ ዘውዳዊ እና የቀኝ ግዛት ያሉ ስረዓቶች ለእሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ችግሮች የተሰጡ ምላሾች ነበሩ።

ኹለቱም በእየራሳቸው መንገድ ፤ ከእላይ የተዘረዘሩት ዓይነት ስረዓቶች ለፈጠሩት ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች የተሰጡ ምላሾች ነበሩ።

የእዚኽ አካኼድ ፋይዳው ደግሞ ግልጽ ነው ፤ ልክ መደበኛ የሆኑ የኢኮኖሚ ሲስተሞች ከእነርሱ በፊት ለነበረ መዋቅራዊ ውድቀት ምላሽ ሆነው እንደ እሚመጡት ኹሉ ፤ ኢመደበኛ የሆኑ የኢኮኖሚ ሲስተሞችም ፤ መደበኛው የኢኮኖሚ ሲስተም በአግባቡ ማገልገል ሲያቅተው የእሚፈጠሩ ናቸው።

የጥንቆላው ኢኮኖሚም እንደው ዝም ብሎ ሳይሆን የእራሱ አስቻይ ኹኔታ የእሚያመጣው ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ፤ መደበኛዎች የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት በንድፈ ኃሳብ ደረጃ ሊገኙ ይችላሉ ፤ በተግባር ግን በንድፍ እንደ አስቀመጡት አይሆኑም ።

ያን ግዜ ፤ ሰዎች ከእሚሰሙት ተነስተው ከመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸው በእሚጠብቁት አገልግሎት እና በተግባር በእሚያገኙት አገልግሎት መካከል ልዩነት ይፈጠራል።

ሕጉ ለኹሉም ዜጋ እኩል የመብት ጥበቃ እና ዋስትና አለ ብሎ ተስፋ ሊሰጥ ይችላል ፤ በተግባር ግን ፦ ሕጉ የእማይገዛቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ፣ በተመሳሳይ ፖሊሲው ፤ የኢኮኖሚ ስኬቶች ኹሉም ጋር በጥረት እና በክህሎት መመዘኛ ይደርሳሉ ሊል ይችላል በተግባር ግን ተፈጻሚነት ላይኖረው ይችላል ፣ በጠቅላላው ተቋማቱ በኃሳብ ደረጃ ለኹሉም በእኩልነት የእሚያገለግሉ ናቸው ይባላል ፤ በተግባር ግን ፤ መድሎ በብዙ መልክ ይኖራል ፤ ከእዚኽም የተነሳ ዜጎች ፦ ሕጉን አክብሬ ብጥር እና ብሠራ ፤ የኢኮኖሚ ስኬት ይኖረኛል ብለው የማመናቸው ነገር ይሸረሸራል።

ለምሳሌ ፦ ሕጉ የንብረት ባለቤትነት መብት ለኹሉም በእኩልነት ይከበራል ሊል ይችላል ፤ በተግባር ግን ፤ የእርሶ መሬት ለሕዝብ አገልግሎት ስለ ተፈለገ ተብሎ ፤ ከገበያ ዋጋ እጅግ ያነሰ ዋጋ በካሳነት ተሰጥቶ ፤ ያ አከባቢ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ላለው እና አልሚ ለተባለ ባለኃብት በጣም በርካሽ ሊሰጥ ይችላል።

በሕግ ኹሉም ነጋዴ በገበያ ተወዳድሮ ይነግዳል ሊባል ይችላል ፤ አንድ አንድ ንግዶች ግን ፤ ልማታዊ ስለ ሆኑ ወይንም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስለ ሆኑ በእሚል ፦ የግብር እፎይታ ፣ ዝቅተኛ ቀረጥ ፣ ርካሽ

እና ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር ፣ ወዘተ እንዲያገኙ ሊደረግ እና ከሌላው ነጋዴ አንጻር ያጋደለ የመወዳደሪያ መስክ ሊመቻችላቸው እና በእዚኽም ከፍተኛ የኃብት ዕድገት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

የሐገሪቱ ገበያ ለኹሉም ክፍት ነው ሊባል ይችላል ፤ በተግባር ግን የሐገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ውድድር ለመከላከል በእሚል ፤ ከውጭ ዕቃ የእሚያስገቡ ነጋዴዎች ከፍተኛ የቀረጥ መጠን ሊጣልባቸው ይችላል።

የእንደ እዚኽ ዓይነት አሠራሮች ድምር ውጤትም ፤ መደበኛው የሐገሪቱ የማሕበረ ኢኮኖሚ ስረዓት ፤ ኹሉንም ዜጎች በእኩልነት ከማገልገል ይልቅ ፤ እንደ አሻው ለሐገር ይጠቅማሉ ያላቸውን ንግዶች በመደገፍ ስም የመወዳደሪያ ሕጉን በመቀያየር ፤ የሐገሪቱን የንግድ ስረዓት ከግምት ውጭ (Unpredictable) በማድረግ ፤ የዜጎችን ስጋት እና የመድሎ ሰለባነት ስሜት ማግነን ይሆናል ።

ከእዚኽም የተነሳ በማሕበረሰቡ ውስጥ የኢኮኖሚ ስኬት ፦ የታታሪነት እና የምርታማነት ውጤት ሳይሆን ይልቁንም ከአንድ ስውር የተፅዕኖ ኃይል ጋር በእሚደረግ ግንኙነት እና ስምምነት የእሚመጣ ነው የእሚል ዕምነት እንዲያይል ያደርጋል።

አንድ ግዜ ይኽ ኹኔታ ከተፈጠረ ፤ ለኢኮኖሚያዊ ስኬት አማራጭ ማብራሪያ እና ስልት የእሚያቀርቡ ማናቸውም ስረዓቶች ተፈላጊነታቸው ይጨምራል።

መደበኛው አሠራር እንደ እሚለው በፍትኃዊነት ኢኮኖሚያዊ ስኬትን ማከፋፈል ካልቻለ ፤ ሰው ሌላ አማራጭ መፈለግ ውስጥ ይገባል።

በተለይ ደግሞ ከእዚኽ በፊት ተሞክረው የወደቁ መደበኛ ስረዓቶች ካሉ ፤ ይኽን አማራጭ የመፈለግ ነገር ይበልጥ ያጠናክረዋል።

ለምሳሌ ፦ ሶሻሊዝም በዘመኑ ፦ ሕብረተሰባዊነትን በመስበክ ፤ ኹሉም በሥራው እና በላቡ ልክ ብቻ የእሚኖርበትን እና የብዝበዛ ኃይሎች የጠፉበትን ሐገር እንደ እሚፈጥር ማስታወቂያ ሠርቶ ነበር።

በተግባር ግን ፦ በአብዮተኝነት ስም ፤ ሕዝቡን ከጭቆና እናድናለን ያሉት አብዮተኞች እራሳቸው አዲስ የገዢ መደብ የሆኑበትን እና ከሌላው ዜጋ ይልቅ ለኃብት እና ለስልጣን የተሻለ የቀረቡበትን እና የተጠቀሙበትን ኹኔታ ነበር የፈጠረው።

ይኽ ዓይነቱ በሶሻሊስታዊ ፕሮፖጋንዳ እና በተግባር መካከል የተፈጠረው ልዩነት ፤ በሕበረተሰቡ ዘንድ ተስፋ መቁረጥን እና ግራ መጋባትን አስከትሏል።

አንድ ማሕበረሰብ ደግሞ ፤ ዘመናዊ እና ሳይንሳዊ የእሚባሉ ስረዓቶች ፤ ኹሉንም በእኩልነት እሚያገለግል ስረዓት እናመጣለን ብለው ሰብከው ሲያበቁ በተግባር ግን ከአንድ ጨቋኝ እና በዝባዥ ስረዓት ምንም የእማይለዩ ሲሆኑ ፤ በመደበኛ ስረዓቶች ተስፋ መቁረጥ እና ግራ መጋባት ብቻ አይደለም የእሚፈጠርበት ፤ አንድ አንድ ግዜ ፤ ሳይንሳዊ ነኝ የእሚሉ ዘመናዊ ስረዓቶች በሙሉ ፤ አጉል ተስፋ ብቻ

ከመስበክ ያለፈ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ፍትሕ ማስፈን የእማይችሉ ናቸው የእሚል ፤ ጸረ ዘመናዊ ስረዓት ግንዛቤም ሊፈጥሩበት ይችላሉ።

ይኽ ሲሆን ፤ የሕብረተሰብ የአስተሳሰብ ውቅር በመሠረታዊነት ተናግቷል ማለት ነው።

ይኽም ሕብረተሰባዊ የሆነ የአስተሳሰብ ስረዓት መናጋት ፤ ትክክለኛ ኃይል በመደበኛ እና ሳይንሳዊ በእሚባሉ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ ሳይሆን ፤ በስውር እና ኢመደበኛ አሠራር ውስጥ ነው የእሚገኘው የእሚል ፤ የተንጋደደ ሕብረተሰባዊ አስተሳሰብን ይፈጥራል።

ይኽ ዓይነቱ አስተሳሰብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ሲደላደል ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ በጥገኝነት እራሱን የእሚያበቅልበት የቆሻሻ ክምር አገኘ ማለት ነው።

ስለ እዚኽ፡- የጥንቆላው ኢኮኖሚ ከባዶ ወይንም ከባሕላዊ አስተሳሰብ ብቻ አይመጣም። በዘመናዊው ዓለም የጥንቆላው ኢኮኖሚ የእሚያቆጠቁጠው ፤ በአብዛኛው ፡- መደበኛ ተቋማቱ ፡- መዋዠቅ ሲበዛባቸው ፣ ሲዳከሙ እና የእሚጠበቅባቸውን ውጤት በተደጋጋሚ ማስገኘት ሲያቅታቸው ነው።

መደበኛ ተቋማቱ አስተማማኝነታቸው እየቀነሰ ሲመጣ ፤ ዜጎች አማራጭ ፡- ማብራሪያ ፣ ከለላ እና ዕድገት ማግኛ መንገድ መፈለግ ውስጥ ይገባሉ።

ከእዚኽ አንጻር ካየነው ፤ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ መዋቅራዊ መንስኤ ኖሮት ነው የእምናገኘው። እንደው ከባዕድ አምልኮ ወይንም ከባሕላዊ ዕምነት አይመነጩም ፤ ይልቁንም ነባራዊ መደበኛ ተቋማት ተዓማኒነታቸው ሲሸረሸር እና ሲዳከም ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ አማራጭ ሆኖ ይመጣል።

መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት እንሰጣለን በእሚሉት እና በተግባር በእሚሰጡት አገልግሎት መካከል ልዩነቱ በሰፋ ቁጥር ፤ እንደ ጥንቆላ ኢኮኖሚ ያሉት ኢመደበኛ እና ትይዩ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት እራሳቸውን ለማሳደግ እና ለማስፋፋት የእሚችሉበት ኹኔታም በእዚያው መጠን ያድጋል።

# 6 የጥንቆላው ኢኮኖሚ እራሱን የእሚያጠናክርበት ዑደት (The Self-Reinforcing Loop)

አንድ ግዜ ፤ መደበኛ ተቋማት ዋዥቀው እና ተዳክመው የእሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት በመሳናቸው ምክንያት የጥንቆላው ኢኮኖሚ ካቆጠቆጠ እና እራሱን እንደ ትይዩ አገልጋይ ማቅረብ ከጀመረ ፤ እራሱን የእሚያጠናክርበት ዋነኛውም መንገድ ፦

> *መደበኛው አሠራር ኹሉንም በእኩልነት አገለግላለኹ ይላል ነገር ግን ማንንም በአግባቡ አያገለግልም ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ግን ፤ የእርሱ መረብ ውስጥ ለእሚገቡት አስተማማኝ ውጤት የእሚያመጣ አገልግሎት መስጠት ይችላል የእሚለው ትርክት ነው።*

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ዝግ እና ለአባላቱ ብቻ የእሚያገለግል ውስን ክበብ በመሆኑ ፤ ለትልቁ ማሕበረሰብ ጎጂ ቢሆንም ፤ ውስን ለሆኑት አባላቱ ግን ውጤታማ አገልግሎት ይሰጣል።

ለምልምል አባላት ፦ በተለይ አገልግሎቱን ፈልገው ለእሚመጡት ፤ መደበኛው ስረዓት ከእሚሰጠው በላይ ፦ አፍጣኝ ፣ በልዩ ኹኔታ ለተገልጋዩ የእሚሰጡ (Tailored) እና አስተማማኝ የሆኑ ውጤቶችን ይሰጣል።

ይኽን ደግሞ ኹሉንም ዜጎች እኩሌ ከእኩሌ ሳልል አገግላለኹ ከእሚሉት እና በተግባር ግን በጣም ደካማ እና መድሎ የበዛበት አገልግሎት ከእሚሰጡ መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት አንጻር ሲታይ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፦ ለተመረጡ ሰዎች በልዩ ኹኔታ የእሚሰጡ እና በአንጻራዊነት ፈጣን አገልግሎት ይሰጣል ማለትን ያስከትላል።

የእዚኽ ልዩ ጥቅም ተቀባዮች ክበብ አባል የመሆን ተስፋ ፤ አንድ ትልቁ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ራሱን የእሚያጠናክርበት መንገድ ነው።

በተለይ ደግሞ ዜጎች ፦ በጥንቆላ ኢኮኖሚው ምክንያት ፤ ከግርግር ወጥተው ፤ የልዩ ጥቅም ተጠቃሚ ሆነው እራሳቸውን ማየታቸው ፤ ራሳቸውን እንደ ልዩ ሰው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።

ሐገር ዓለሙ በሙሉ ያላወቀው አንድ ታላቅ ምስጢር እንደ አወቁ እና እንደ አላቸው ማሰብ ይጀምራሉ።

የነፍስ አድን ሩጫ ሆኖ የተጀመረው የጥንቆላ ኢኮኖሚ ተሳታፊነት እንደ አንዳች ታላቅ የስኬት ምስጢር ባለቤትነት መቆጠር ይጀምራል።

እንዲኽ ዓይነቱ የምርጦች ምርጥነት ስሜት ግን በአንድ ሰው ብቻ አይወሰንም ፤ ቀስ እያለ ይስፋፋል።

በግዜ ኺደትም ይኽ ስሜት ሲዛመት ፦ መደበኛ ተቋማት ለኹሉም ዜጋ በእኩልነት ፍትሕ እና ዕድል እናቀርባለን ይላሉ ፤ በተግባር ግን በጣም ብዙ ጉድለት አለባቸው ፤ በአንጻሩ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ለኹሉም

ሳይሆን ፤ በጥቅም ኔትወርክ ውስጥ ላሉ ለታደሉ ለጥቂቶች ብቻ ፤ እንደ መደበኛ ተቋማቱ ተስፋ ሳይሆን ተጨባጭ ውጤት ይሰጣል የእሚለው ጉዳይ ፤ ጠንካራ በተግባር የተደገፈ ትርክት እየሆነ ይኼዳል።

ግልጸኝነት የለውም ግን በስውር አባላቱን ይጠቅማል። በሕግ እና በአሠራር ላይ ተሞርኩዞ ሳይሆን የጥቅም መረብ ውስጥ ላሉት ብቻ ይሠራል።

ከእዚኽ አንጻር ካየነው ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ የኪራይ አከፋፋይ ኢኮኖሚ ይመስላል።

ምክንያቱም ፦ እንደ ማንኛውም የኪራይ ሰብሳቢ እና ጥገኛ ስረዓት ፤ በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ የኢኮኖሚ ስኬት ፦ በምርታማነት ፣ በክህሎት እና በሕግ አክባሪነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ፤ ከአንድ ስውር የኃይል ቡድን ጋር ባለ ቅርበት እና ትሥሥር ላይ የተመሠረተ ነው።

ከእዚኽም የተነሳ በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ነገር ፦ በጥንቆላ ኢኮኖሚው መረብ ውስጥ ግንኙነት ሊመሰረቱ የእሚችሉት የእሚያውቁት በመኖሩ እና በእዚያ የጥንቆላ መረብ ውስጥ የራስን ስፍራ በማግኘት ላይ ነው።

አንድ ግዜ ይኽ አስተሳሰብ ስር ከያዘ ፤ የጥንቅላው ኢኮኖሚ እራሱን የእሚያጠናክርበትን ኹለተኛውን ሞተር ያገኛል ፦ ጉጉት።

ለጥቂት ምርጦች ብቻ የእሚሠራ እና ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የእሚያስገኝ ዝግ ቡድን አባል መሆን ፤ ቀላል የእማይባሉ ሰዎች ላይ ጉግት ይፈጥራል። እንደ እዚኽ ዓይነቱ ቡድን የመኖሩ ነገር ፤ በጣም የተጋነነ ወይንም ከፊል ዕውነታ ያለው ብቻ ቢሆን እንኳን ፤ ወሬው ብቻ በጣም ተፅዕኖ ይፈጥራል።

ግለሰቦች በሌሎች ነገር ላይ ገንዘባቸውን እና ግዜያቸውን ከማባከን ይልቅ ፤ ገንዘባቸውን እና ግዜያቸውን የእዚኽ ዓይነቱ ቡድን አባል ለመሆን በእሚደረግ ጥረት ላይ ያደርጉታል።

እዚኽ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፤ በኃሜት ደረጃ የእሚነገሩ ፤ ታሪኮች ትልቅ ቦታ ይኖራቸዋል።

በኢመደበኛው የኃሜት መረብ ውስጥ ፤ ዕውነተኝነታቸው ያልተጣራ ወይንም በተዛባ መልኩ የቀረቡ ፤ የስኬት ታሪኮች በጣም ይስፋፋሉ።

እነ እዚኽ የስኬት ታሪኮች የግድ በእርግጠኝነት ዕውነት መሆን አይጠበቅባቸውም ፤ የተወሰነ ዕውነትነት ካላቸው እና ከተደጋገሙ በቂ ነው። እያንዳንዱ ታሪክ የእሚያስፈልገው ፤ የሲስተሙን ታማኝነት በመጨመር ሌሎች ሰዎችን መሳብ እንዲችል ፤ ሲስተሙ ይሠራል ለማስባል ነው ።

የአብዛኛውን ሰው ልብ የእሚገዛው ፤ በባሕሪያቸው ውስብስብ ከሆኑ ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ማብራሪያዎች ይልቅ እንደ እዚኽ ዓይነት የውጤት ታሪክ ነው ።

አብዛኛው ሰው ፤ በግል የእሚያጋጥመውን የኢኮኖሚ ትግል ፤ የሞኒተሪ ፖሊሲ (Monetary Policy) ወይንም የተቋማት አገነባብ (Institutional Design) ወይንም የሕግ ስረዓቱ ችግር ያስከተለው ነው ብሎ ማብራራት አይሆንለትም።

ለአብዛኛው ዜጋ ትርጉም የእሚሰጠው ፤ ስለ አሠራሩ ማብራሪያ አይደለም ፡- መሳካት እና መውደቅ ፣ ዕድል ማግኘት እና ማጣት ፤ ያ ነው ትርጉም የእሚሰጠው።

በባሕሪያቸው ውስብስ ገለጻ ያላቸው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ የእሚሉትን አገልግሎት መስጠት ሲያቅታቸው ፤ ሕብረተሰቡ እሚፈልገው ማብራሪያ ሳይሆን ተግባራዊ ውጤት የእሚያመጣለትን ነገር ይሆናል።

በእንደ እዚኽ ዓይነት ኹኔታ ውስጥ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ የእራሱ የሆነ አማራጭ ማብራሪያ ያለው ስረዓት ብቻ ሳይሆን ፤ ውጤት ማስመዝገቢያ ስልትም ይሆናል።

በግዜ ኺደትም ፤ ስኬት በቀዳሚነት ፤ የትጋት ፣ የክህሎት ፣ የችሎታ እና የፈጠራ ውጤት ሳይሆን ፤ ውጤት ማስመዝገበ የእሚችል የአንድ ዓይነት ስውር የተፅዕኖ ኃይል ጋር የሚያያዝ ነገር ይሆናል።

ሥራ ማግኘት ፣ የንግድ ዕድል ፣ ብድር ማግኘት ፣ ወይንም የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት ማግኘት ፤ በጥንቆላ ኢኮኖሚ መነጽር እና መነጽር ብቻ መታየት ይጀምራሉ።

ይኽ ግንዛቤ እየሰፋ እና የተመልማዮች ቁጥሩ እየበዛ ሲኼድ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚም አቅሙ እየጨመረ ይኼዳል።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ከዘመናዊ መደበኛ ኢኮኖሚዎች በፊት የነበረ መሆኑን ልብ ማለትም ይገባል። አንድ አንድ ግዜ ይኽ አንጋፋነት ፡- እራሱን በማሕበረሰብ ውስጥ ለመቅበር እና ለማስተዋወቅ በር ይከፍትለታል።

በግዜ ኺደትም በእሚዘረጋው ኔትወርክ አማካኝነት ፤ በአንድ ሐገር ውስጥ የተለያዩ ፡- ኢኮኖሚያዊ ፣ ማሕበረሰባዊ አንዳንዴም ፖለቲካዊ ክፍሎችን ሰርስሮ ለመግባት ያስችሉታል።

እያንዳንዱ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ተገልጋይ ኢኮኖሚውን ያጠናክረዋል። ተገልጋዮች ውጤት ሲያገኙ መዋጮ ያመጣሉ ፤ መዋጮ በማምጣት ሲቆዩ ሌላ ተገልጋይ ያመጣሉ። በእዚኽ መንገድ ኔትወርኩ በተፈጥሯዊ መንገድ ፤ አንዱ ሌላውን እየመለመለ እና እየሳበ ፤ እራሱን እና ተቀባዩነቱን ያሳድጋል።

የኔትወርክ መጠን ሲሰፋ ደግሞ ተፅዕኖ አብሮ ይሠፋል።

በእዚያም ኔትወርኩ ባደገ ቁጥር ፤ ኔትወርኩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ፤ ውጤት ላይ ያለው ተፅዕኖ አብሮ ያድጋል። ይኽም መልሶ ፤ የጥንቆላው ኔትዎርክ ውጤታማ ነው የእሚለውን ትርክት ይበልጥ በማስፋፋት ፤ አዳዲስ ምልምሎችን ስቦ በማምጣት ኔትወርኩን ይበልጥ ያሰፋዋል ፥ ያጠናክረዋል።

አንድ አንድ ግዜ እንዲያውም ይኽ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ኔትዎርክ ድንበር ተሻጋሪ በመሆን ዓለም ዓቀፋዊነትም ሊላበስ ይችላል። በማሕበራዊ ትሥሥር ፣ በስደት ፣ በንግድ ትሥሥር ፣ የተወሰኑ የኔትዎርኩ አካላት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሊሠራጩ ይችላሉ።

ይኸም ፡- የሥራ እና የኢኮኖሚ ዕድል በሐገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሐገርም ማቅረብ እንችላለን እንዲሉ ያደርጋቸዋል ፤ በተለይ ወደ ምዕራቡ ሐገር ለመኼድ ቪዛ የማግኘት ዕድሉ ጠባብ በሆነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሐገራት ፤ የውጭ ሐገር ቪዛ አስገኛለኹ ካለ ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ተቀባይነት እና አጓጊነት ይበልጥ ያጎላዋል።

እዚኽ ደረጃ ላይ ሲደርስ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ እራሱ የእራሱ የጥንካሬ ምንጭ (Acquires momentum) የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው።

ከእዚኽ በኋላ ራሱን የእሚያስቀጥለው እራሱ ይሆናል (It becomes self-sustaining)።

አዲስ ምልመላው ገቢ ይጨምራል ፣ አዲሱ ምልምል እና የእሚያመጣው ገቢ ኔትወርኩን ያጠናክረዋል ፣ የኔትወርኩ መጠናከር ውጤታማነቱን ከፍ ያደርገዋል ፣ ውጤታማነት ሲያድግ ዝና እና ስም አብሮ ያድጋል ፣ ዝና እና ስም ሌሎች አዲስ ተገልጋዮችን የመልመል አቅምን ያሳድጋል። በእዚኽ አግባብ ፤ እያንዳንዱ የሲስተሙ አካል እርስ በእርሱ እየተመጋገበ ጠቅላላ ኔትወርኩን ወደ እሚቀጥለው ደረጃ ያሳድገዋል።

አንድ ስረዓት ደግሞ ይኸን ዓይነት የዑደት ደረጃ ላይ ከደረሰ ፤ ዑደቱን በመስበር ሲስተሙን ማዳከም ይከብዳል ፤ ምክንያቱም ፡- እዚኽ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ፤ እራሱን ከተለዋዋጭ ኹኔታዎች ጋር አጣጥሞ ለማስቀጠል በእሚያስችለው መልኩ ሕብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ ይዞታ ስለ እሚኖረው።

ውጤቱም ፡- የመደበኛ ተቋማቱ ደካማነት እና አጠራጣሪነት እስከ አለ ድረስ የእሚቀጥል ፤ አንዳች ዓይነት ኢመደበኛ የሆነ ትይዩ ተቋም መሆን ይሆናል።

# 7 ተቀጥላ ዋጋ እና የዋጋ ስረዓት ማዛባት - የጥንቆላ ኢኮኖሚ ችግሮች (Costs and Distortions -Problems of Witchcraft Economy)

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ እንደ የተደራጁ የወንጀል ቡዶኖች እና የቀኝ ግዛት ዓይነት ስረዓቶች ጋር ፤ የእሚጋራቸው እና የእሚመሳሰልባቸው ባሕሪያት አሉት። ምክንያቱም ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ልክ እንደ ተደራጁ የወንጀል ቡድኖች እና የቅኝ ግዛቶች ፤ የሲስተሙ አካል ለሆኑ ተሳታፊዎች ልዩ ጥቅም እና አገልግሎት ይሰጣል ፤ ሆኖም ያን በማድረግ ኺደት ውስጥ በሰፊው ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ውጭ ባለው ማሕበረሰብ ላይ ሰፊ እና ስውር ተጨማሪ ዋጋዎችን ይጭናል።

ስለ እዚኽ ፦ ምንም እንኳን በእርሱ የአሠራር መረብ ውስጥ ላሉ አባላቱ ወይንም ተሳታፊዎቹ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ልዩ እና "አስተማማኝ" አገልግሎት ቢሰጥም ፤ ከኢኮኖሚ ሳይንስ አንጻር ሲታይ ውጤታማ (Effective) የእሚባል አይደለም ፤ ይልቁንም ተደራቢ ዋጋ ስለ እሚጨምር ፤ የ100 ብርን አገልግሎት በ1000 ሺ ብር የእሚያቀርብ ዓይነት ብኩን (Inefficient) ስረዓት ነው።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ በሳይንሳዊ የኢኮኖሚ መርኽ መሠረት ሲመዘን ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ እጅግ ብኩን ከእሚባሉት መካከል ነው የእሚመደበው። የግብይይት እና የአገልግሎት ዋጋ (Transaction costs) አላግባብ ያንራል ፣ በእዚኽም ዋጋ ያዛባል ፣ ኃብት በውጤታማነት እና በምርታማነት ስለ እማያከፋፍል የኃብት ክፍፍልን ያዛባል ፣ ከእዚኽ የተነሳ በአንድ ሐገር ውስጥ ምርታማነት እንዲላሽቅ ያደርጋል።

የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ብኩንነት ይበልጥ ለማሳየት ፤ ንፅፅራዊ ምሳሌን እንጠቀም።

የተደራጁ የወንጀል ቡድን በተንሰራፉባቸው ማሕበረሰቦች ውስጥ ፤ እነ እዚኽ የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች ፦ ለተሳታፊዎቻቸው ፦ የጥበቃ ፣ የማስፈጸም ወይንም ጉዳይ የማቅለል (Protection, enforcement, or access) "አገልግሎት" ይሰጣሉ።

ለምሳሌ ፦ ሲሲሊ በእሚባለው በጣሊያን አውራጃ (ደሴት) ውስጥ ባሉ እንደ ፓሌርሞ (Palermo) ዓይነት ከተሞች ፤ እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ 80% የእሚሆነው ነጋዴ ለማፊያው (The Mafia) የጥበቃ ገንዘብ ካልከፈለ መነገድ አይችልም። አንድ ነጋዴ አልከፍልም ቢል ፤ ሱቁ ይቃጠላል ፣ ንብረቱ ይሰበራል ፣ ወዘተ ፤ ወደ ሕግ አካል ቢኼድ እንኳን መፍትኼ ማግኘት አይችልም ፤ ምክንያትም ፦ የማፍያው ቡድን ፖሊስን ጨምሮ በተለያዩ የመንግሥት መዋቅሮች የራሱ ሰዎች ስለ አሉት እና የእሚቃወሙትን የመንግሥት ሰዎች እንኳን እስከ መግደል ድረስ ስለ እሚኼድ።

ከእዚኽ የተነሳ የአትክልት ነጋዴ እንኳን ለማፍያው ቡድን “የጥበቃ” ገንዘብ የእሚከፍል በመሆኑ እና ለማፍያ የጥበቃ እንደ እሚከፍል መናገር ብዙ ችግር ስለ እሚያመጣበት ፤ ነጋዴው የሸቀጥ ዋጋ ውስጥ የመንግሥትን ግብር ብቻ አይደለም ከግምት የእሚያስገባው ለማፍያው የእሚከፍለውንም ተጨማሪ ክፍያ ስለ ሆነ የሸቀጦች ዋጋ ይጨምራል።

የማፍያው ቡድን ሲጠናከርም ፦ ጨረታ ማሸነፍ ፣ ኮንትራት ማግኘት ፣ የግንባታ መሬት ማግኘት ፣ ወዘተ በሙሉ ከእርሱ ጋር በመሥራት ካልሆነ ሊሳካ የእማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርስና ፤ ከእያንዳንዱ ግዙፍ ግብይት በስተጀርባ የእራሱን የአገልግሎት ክፍያ ስለ እሚያስጨምር ፤ አርተፊሻል የዋጋ ንረት እና የዋጋ ስረዓት መዛባት በማስከተል ፤ የሐገራዊ ኢኮኖሚ ብቁ አምራች ሳይሆን ከዋጋ በላይ የእሚከፍል ብኩን እንዲሆን ያደርገዋል።

ይኽም ማለት ፤ የማፍያው ቡድን በአየለበት ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ የአገልግሎቶች እና የሸቀጦች ዋጋ ፤ ተወዳዳሪ የማምረቻ ዋጋ ሳይሆን ለማፍያው ቡድን የእሚከፈለው ስውር ግብር የተካተተበት እና ይኽም ዓይነቱ ድባብ በእሚፈጥረው ስጋት የትክክለኛ ተወዳዳሪዎች መሸሽ ስውር ዋጋ የተጨመረበት ነው እሚሆነው።

ድምር ውጤቱም ፦ የዋጋ ውድነት ፣ የጥራት መቀነስ እና የአቅርቦት ውስንነት ብሎም ተለዋዋጭነት ነው ፤ ተያይዞም ኋላ ቀርነት ነው የእሚሆነው።

ምንም እንኳን ኹለቱም አንድ ሐገር ቢሆኑም ፤ ደቡባዊ ጣሊያን ከሰሜናዊ ጣልያን ይልቅ ድኃ ፣ ኢዴሞክራሲያዊ እና ኋላ ቀር የሆነው ፤ በደቡባዊ ጣሊያን የማፍያው አደረጃጀት ተስፋፍቶ ፤ በመላው ኢኮኖሚ ላይ የፍርኃት ፣ የተቀጥላ ዋጋ እና የዋጋ ስረዓት መዛባት ስለ እሚያስከትል ነው።

የቀኝ ግዛት ሲስተሞችም ተመሳሳይ አሠራር እና ውጤት ነው ያላቸው። ምክንያቱም ፦ የቀኝ ግዛት ስረዓቶች ፤ ከፍተኛ የተፈጥሮ ኃብት ብዝበዛ በማድረግ እራሳቸውን የእሚጠቅሙ ቢመስሉም ፤ በተፈጥሮ ብዝበዛ ላይ የእሚገነባ ኃብት ፤ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ (It is not competitive and efficient economic system) የምርታማነት ስረዓት ባለመሆኑ ፤ በግዜ ኺደት ብኩንነቱ የእራሱ ጠላት ይሆናል።

ለምሳሌ ፦ የእንግሊዙን የቀኝ ግዛት ኢኮኖሚ ብንመለከት ፤ የቀኝ ግዛት ስረዓቱ አገልጋይ የሆኑ ሰዎችን በልዩ ኹኔታ የእሚጠቅመው ፤ ለምሳሌ ፦ ቀኝ በሚገዛቸው እና እንደ ጥጥ ያሉ የተፈጥሮ ኃብቶችን በእሚመዘብርባቸው ቦታዎች ፋብሪካ እንደ አይገነባ በመከልከል ፣ የብቸኛ አስመጪ/ላኪነት መብት (Monopolies) ለተወሰኑ ንግዶች በመስጠት እና አምባገነናዊነት በማስፈን ነው።

ለምሳሌ ፦ በአሜርካ ጥጥ እንዲታረስ እንጂ ጥጡን ተጠቅሞ ጨርቅ የእሚያመርት ፋብሪካ እንደ አይከፈት ሲያግድ ፤ ኃሳቡ ለንደን የእሚገኙ የቀኝ ገዢው አካል የሆኑ ፋብሪካዎችን ለመጥቀም ነው። ይኽ ዓይነቱ አካኼድ ግን ፤ በለንደን ላሉ የጨርቅ ፋብሪካዎች እና ከለላ ለእሚሰጣቸው ዘውዳዊ ስረዓት ግዜያዊ ጥቅም ቢያመጣም ፤ የተፈጥሮ ኃብት የእሚበዘበዝባቸውን ቦታዎች በማቆርቆዝ እና የጨርቅ ምርት ኺደት በውድድር ሳይሆን በልዩ ጥቅም ስለ እሚገዛ የጥራት እና የዋጋ ጉድለት እንዲኖረው ያደርጋል። እነ እዚኽም ኺደቶች በግዜ ፤ ማሕበራዊ ቅራኔ እና ኢኮኖሚያዊ ድህነት በማስፋፋት ፤ ትልቅ ቀውስ ይፈጥራሉ።

የብቸኛ ነጋዴነት (Monopoly) ፈቃድም ሲሰጥ ፤ ምንም እንኳን ሌሎች እንደ የሐገር ውስጥ ድርጅትን ከውጭ ድርጅት ለመከላከል ነው ወዘተ የእሚባሉ ዓይነት ምክንያት ቢቀርቡበትም ፤ ውጤቱ ግን ብቸኛ ነጋዴው የውድድር ግዴታን አስወግዶ እና የሌሎችን የመሳተፍ መብት ገድቦ ፤ የጥራት ችግር ያለበትን ምርት በውድ ዋጋ እየሸጠ ኢኮኖሚያዊ ብኩንነት ስለ እሚያስከትል ፤ የቀኝ ግዛት መንግሥት ፤ ቀኝ በእሚገዛቸው ሐገራት ብቻ ሳይሆን በእራሱ ማሕበረሰብም ውስጥ ፤ የቀኝ ግዛቱ መንግሥት አገልጋይ የሆኑትን ጥቂቶች ሲጠቅም ፤ ሰፊውን ሕብረተሰብ በድህነት እና በጭቆና ውስጥ ነው እሚተወው።

የእዚያም ውጤት ልክ እንደ ተደራጀው የወንጀል ቡድን ፤ እንደ ማፍያው ፤ ውጤቱ ፦ ማሕበራዊ አለመረጋጋት እና ድህነት ነው።

ይኽም ዓይነቱ የቀኝ ግዛት ኢኮኖሚ አካኼድ የፈጠረው ማሕበራዊ አለመረጋጋት እና የኢኮኖሚ ድህነት ነበር ፤ በአሜሪካ የጸረ ቀኝ ግዛት ትግልን አስጀምሮ ፤ የአሜሪካን ከእንግሊዝ ነጻ መውጣት ያስከተለው።

በተመሳሳይም ፦ በፈረንሳይ እጅግ ደም አፋሰሽ አብዮት የጋበዘው ፤ የቀኝ መንግሥቱ የፈረንሳይ መንግሥት ፤ ቀኝ ለእሚገዛቸው ሐገራት ብቻ ሳይሆን ፤ ለገዛ ሕዝቡም የማሕበራዊ አለመረጋጋት እና የድህነት ምንጭ በመሆኑ ነበር።

በነገራችን ላይ በመላው ዓለም ቀኝ ግዛት የወደቀው ፤ የነጻነት ትግል አሸንፎት ብቻ ሳይሆን ፤ የእራሱ ኢሰባዊ እና ብኩን አካኼድ ከፍተኛ ኪሳራ እና ውርደት ስለ አደረሰበትም ነው።

ስለ እዚኽ ፦ የቀኝ ግዛት ኢኮኖሚ ፤ ምንም እንኳን በግዜያዊነት ፤ ለሲስተሙ አካላት ፤ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያስገኝ ቢመስልም ፤ ኢፍትኃዊ እና ብኩን ስለ ሆነ ፤ በግዜ ኺደት ውጤቱ ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ቀውስ እና የቀኝ ግዛት ኢኮኖሚ ውድቀት ነበር።

የጥንቆላው ኢኮኖሚም ተመሳሳይ አካኼድ እና አሠራር ነው ያለው።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ለተገልጋዮቹ ፦ ሥራ ቢፈጥርም ፣ ብድር ቢያመቻችም ወይንም የዕድል በሮች ቢከፍትም ፤ እነ እዚኽን የእሚያደርገው ግን ፤ በተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ዋጋ ሳይሆን ፤ ስውር እና ተጨማሪ ዋጋ በማስከፈል ነው። የጥንቆላ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ፤ አገልግሎቱን የእሚያገኙት ፦ ከመደበኛው ውጭ የሆኑ ክፍያዎችን በመፈጸም እና ግዴታዎች ውስጥ በመግባት ነው።

መጀመሪያ ላይ እገዛ መስሎ የእሚቀርበው የጥንቆላ ኢኮኖሚ አገልግሎት ፤ በግዜ ኺደት ወደ ብዝበዛነት የእሚቀየር የክፍያ ግዴታ አብሮት አለ።

የጥንቆላን አገልግሎት ተጠቅሞ አንድ ሥራ ያገኘ ሰው ፤ ግዜውን እና ግብር የእሚሰጠው ለሥራው እና ለመንግሥት ብቻ አይደለም ፤ ይልቁንም ሥራውን ላስገኘለት ለጥንቆላው ኢኮኖሚም ጭምር ነው። ይኽ ግን ለተቀጣሪ ብቻ አይደለም ፦ ኮንትራት ለማግኘት ፣ ብድር ለማግኘት ፣ ጉዳይ ለማስፈጸም ፣ ወዘተ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ አገልግሎት ለተጠቀመ በሙሉ ነው።

ይኽም ለጥንቆላው ኢኮኖሚ ተገልጋዮች ተጨማሪ የግዜ ጫና እና የገንዘብ ወጪ ስለ እሚያስከትልባቸው ፤ እነርሱም ያን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን ፦ ጉቦ ይበላሉ ፣ ዋጋ ይጨምራሉ ፣ ነገር ያጓትታሉ ፣ ወዘተ ፤ ይኽም ሲደማመር በኢኮኖሚው ውስጥ የዋጋ መዛባት ያስከትላል።

ውጤቱም ፦ ማሕበራዊ ቀውስ እና ኢኮኖሚያዊ ድህነት ነው የእሚሆነው ፤ ልክ በማፍያዎቹ ወይንም በቀኝ ገዢዎቹ እንደ ሆነው።

መጀመሪያ ፦ **<u>የተዛባ የኃብት ድልድል</u>** ይፈጥራል። ምክንያቱም ፦ በኢኮኖሚው ውስጥ ኃብት እና ዕድል ፦ በምርታማነት ፣ በተወዳዳሪነት እና በክህሎት መመዘኛ ሳይሆን በትውውቅ መመዘኛ ስለ እሚደለደሉ ፤ የኃብቱ ድልድሉ የተዛባ ይሆናል። የእዚኽ ውጤቱ ደግሞ የጠቅላላውን የኢኮኖሚ ብቃት ማድከም ይሆናል ፤ ምክንያቱም ብቃት ያላቸው ሰዎች ወደ ጎን እየተገፉ ፤ ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋር ቅርርብ እና ትውውቅ ያላቸው ሰዎች ፤ ያለ ምንም ብቃት የኢኮኖሚያዊ ኃብት ስለ እሚያገኙ።

በመቀጠል ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ **<u>ዋጋ ያዛባል</u>**። በግብይይት ፣ በልውውጥ እና በውሎች ውስጥ ስውር ተጨማሪ ዋጋዎችን ስለ እሚጨምር ፤ ዋጋው በነጻ ውድድር ሊገኝ ከእሚችለው ዋጋ በላይ ይሆናል። ከእዚኽም የተነሳ ሸማቾች ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ላለው አገልግሎት/ምርት የበለጠ ዋጋ ይከፍላሉ ፤ አምራቾችም በነጻ ገበያ ከእሚገጥማቸው በላይ ከፍ ያለ የግብዓት ዋጋ ተጠቅመው ለማምረት ይገደዳሉ።

በሶስተኝነት ፦ የጥንቅላው ኢኮኖሚ **<u>የስጋት መጠንን ይጨምራል</u>**። በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ በአንድ ጉዳይ ውጤት ለማግኘት በግልጽ እና መደበኛ ተቋማት ላይ ከመመሥረት ይልቅ ፤ በስውር የተፅዕኖ አሠራር ላይ መደገፍ ሲኖር ፤ ግለሰቦች ውጤት ለማምጣት በእሚያውቁት እና በእሚቆጣጠሩት በእራሳቸው ጥረት እና ኢንቨስትመንት ላይ መደገፍ ሲሳናቸው የስጋት መጠናቸው ይጨምራል። በእዚኽ መልኩ ስጋት ሲነግሥ ደግሞ ግለሰቦች የረጅም ግዜ ዕቅድ ለማውጣት እና ነገን ተስፋ አድርገው ሰፊ ምርታማነትን የእሚያሳድግ ኢንቨስትመንት ለማድረግ መስጋት እና መሸሽ ይጀምራሉ።

አራተኛ ፦ የጥንቆላው **ኢኮኖሚያ እኩልነት እየቀነሰ እንዲኼድ** ያደርጋል። በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ ከኔትወርኩ ግንኙነት ያላቸው ልዩ ጥቅም ሲያገኙ ፤ ከኔትወርኩ ውጭ ያሉት ኢኮኖሚያዊ ስኬት ለማስመዝገብ ብዙ መሰናክል እየበዛባቸው ይኼዳል። በግዜ ኺደት ፤ ይኽ ዓይነቱ አሠራር ሥር እየሰደደ ሲኼድ ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ኹለት ትይዩ ሲስተሞች ይፈጠራሉ ፤ አንድ ፊት ለፊት የእሚታይ እና ግልጸኝነት ያለበት ፤ ሌላው ደግሞ ስውር የሆነ እና የስውር ኔትወርኩ አካል በመሆን የእሚነዳ።

የእዚኽም ድምር ውጤቱ ፦ በአደባባይ በሕግ ታውጀው በእሚቋቋሙ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት የአገልግሎት አሠጣጥ እና በተግባር ሕዝቡ የእሚኖረው ኑሮ የተለያየ ይሆናል።

የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ ኢኮኖሚያዊ ብኩንነት (Economic inefficiency) ብቻ አይደለም የእሚያስከትለው ፤ ይልቁንም አብሮ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትልም ይችላል።

ምክንያቱም ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ በስውር እና በድንግዝግዝ ስለ እሚሠራ ፤ በጣም ውስን ተጠያቂነት ነው ያለበት። ተገልጋዮች ቢመዘበሩ ወይንም በደል ቢደርስባቸው ፤ ወደ ሕግ ኼደው የጉዳት ካሳ

ሊጠይቁ አይችሉም። የጥንቆላው አሠራር ፤ ንግድ ፈቃድ አውጥቶ ፤ ውል ፈርሞ እና አስፈርሞ ስለ እማይሠራ ፤ ተበዝብዣለኹ ወይንም ተበድያለኹ ያለ አንድ ተገልጋይ ፤ በቂ ማስረጃ ኖሮት ወደ ፍርድ ቤት ሊኼድ አይችልም።

ይኽም የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ያለ በቂ ተጠያቂነት ፦ የማስገደድ ፣ የማባበል ፣ የማታለል እና አማራጭ የማሳጣት ሥራ እንዲሠራ ያስችለዋል። በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ አንድ ግዜ የተያዙ ሰዎች ፤ ከፍተኛ ዋጋ በመክፈል ካልሆነ ከእዚያ መረብ መውጣት እማይችሉበት ኹኔታ ይፈጠራል ፤ በእዚኽ ረገድ መደበኛ የማሕብረ ኢኮኖሚ ተቋማት ምንም ሊረዷቸው አይችሉም።

ይኽ በግዜ ኺደት ፤ ኹሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው የእሚለውን ነገር ትርጉም አልባ ያደርገዋል። ሙብት ኹኔታዊ ይሆናል ፣ የኢኮኖሚ ዕድሎች በእሚታወቁ ሐገራዊ ሕግ እና ፖሊሲዎች መሠረት ሳይሆን በኢመደኛ እና ስውር ኃይላት የእሚዘወሩ ይሆናሉ።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ እየተስፋፋ ሲኼድም ፤ ይኽን መሠሉ አሉታዊ ማሕበራዊ ተፅዕኖው አብሮ ያድጋል።

የዋጋ መናር ፣ የዋጋ መዛባት ፣ በመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት አለመተማመን እርስ በእርስ እየተመጋገቡ ፤ አንዱ አንዱን እያባሰው ይኼዳል።

ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ውጭ የሆኑ ግለሰቦች ፤ የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ሰቆቃቸው እየበዛ ፤ በአንጻሩ ተሳታፊዎቹ ይበልጥ ወደ ኢኮኖሚው ስረዓት ውስጥ ጠልቀው የእሚገቡበት ኹኔታ ይፈጠራል። ደጋግመን እንደ አልነው ፤ የእዚኽ ውጤቱ ኢኮኖሚያዊ ችግር ብቻ አይሆንም ፤ ይልቁንም ማሕበራዊ ውጥረት እና አለመረጋጋትም ይሆናል።

ይኽም ስለ ጥንቆላ ኢኮኖሚ ኹለት ነገር ማለት እንድንችል ያደርገናል ፤ እርሱም ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ በአንድ በኩል የመደበኛ ተቋማት ውድቀት የእሚፈጥረውን ክፍተት የእሚሞላ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ማሕበረሰብን የእሚበላ ብል ( Corrosive) ነው።

አመጣጡ የመደበኛ ተቋማት ድክመት የፈጠረውን ክፍተት እሞላለኹ በእሚል ቢሆንም ፤ በኺደት ግን ያኑን መጀመሪያ ያመጣውን የተቋማት ክፍተት ይብስኑ ማክፋት እና ማባባስ ይሆናል ውጤቱ ነው።

ስለ እዚኽ፦ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ ውስን ከሆኑት ተገልጋዮቹ አንጻር የፈለገውን ያኽል ውጤታማ ቢሆንም ፤ የዋጋ ንረት በማስከተል ፣ ሰዎች በውድድር ሳይሆን በትውውቅ እንዲያምኑ አድርጎ ኢኮኖሚያዊ ባሕሪዎችን በማበላሸት ፣ በእዚያም የሐገራዊ ኢኮኖሚ ርጋታ እና አስተማማኝነት እንደ አይኖረውም በማድረግ ፤ ለሰፊው ማሕበረሰብ ማሕበራዊ ብል (Social Corrosion) መሆኑ በእማያወላዳ መልኩ ግልጽ ነው ።

# 8 ሊህቃን ለምን የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ማፍረስ ያቅታቸዋል

ሊህቃን የፈለጉትን ያኽል ጠንካራ እና ባለስልጣን ቢሆኑ ፤ ትልቁን ማሕበረሰብ ከእሚገዛው ስረዓት በላይ መሆን አይችሉም።

ምንም ሊህቅ ቢሆኑም እንኳን ፤ የእሚኖሩበት ማሕበረሰብን የእሚገዛው ኹኔታ ፣ ገደብ እና የአስተሳሰብ ሰረዓት እነርሱንም ይገዛቸዋል።

የደኃ ሐገር ፕሬዝደንት የደኃ ሐገር ፕሬዝደንት ነው።

በእዚያኽ ላይ ደግሞ ፤ በግዜ ኺደት የማሕበረሰባቸው ሊህቃን እና አለቃ ቢሆኑም ፤ አብዛኛዎቹ ሊህቃን ሲጀምሩ ጀምሮ ሊህቅ እና አለቃ ሆነው አይደለም የጀመሩት ፤ ይልቁንም ሌላው የማሕበረሰቡ ክፍል በእሚኖርበት ኹኔታ ፣ ባለበት ገደብ እና የአስተሳሰብ ዘውግ ውስጥ ፤ መደበኛ እና ኢመደበኛ ተቋሞች የእሚያስቀምጡባቸውን ፈተናዎች አልፈው ነው ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሱት።

ይኽ ደግሞ ፤ በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ ትይዩ ወይንም ምትክ አሠራር ሆኖ በእሚገኝበት ግዜ ፤ ልዩ እንደምታ ይኖረዋል።

ምክንያቱም ፦ እንደ ጥንቆላው ኢኮኖሚ ዓይነት ፤ ኢመደበኛ የሆነ ትይዩ ተቋም ከመደበኛዎቹ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ጎን ለጎን በእሚቆምበት ግዜ ፤ አንድ የዛሬ ሊህቅ ፤ ከነበረበት የተራ ዜግነት ደረጃ ተነስቶ ፤ የዛሬው ሊህቅነት ደረጃው ላይ በክህሎቱ እና በችሎታው ብቻ ይደርሳል ብሎ ማለት ትንሽ ይከብዳል።

ምክንያቱም ፦ በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ በእዚኽ መልኩ መደበኛ እና ኢመደበኛ የሆነ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ በትይዩነት እና በተፎካካሪነት አብረው በእሚዓዙበት ግዜ ፤ አንድ ሰው በእድገት መሰላሉ ወደ ላይ ለመውጣት ፤ መደበኛ እና ግልጽ የሆኑትን ተቋማት ብቻ ሳይሆን የስውሮቹን የኢመደበኛ ተቋማትም አገልግሎት መጠቀምም ግድ ይሆናል።

ይኽም ማለት ፦ በእንደ እዚኽ ዓይነት ባለኹለት መልክ ማሕበረሰብ ውስጥ ፤ ችሎታ እና ክህሎት ብቻ ሳይሆን ፤ ከኢመደበኛው ኔትወርክ ጋር አብሮ መሥራትም ይፈልጋል።

በተለይ ለታዳጊ አመራሮች ይኽ ትልቅ ግራ መጋባት የእሚፈጥር ነው። ምክንያቱም ፦ ብዙ ዋጋ ከፍለውም ቢሆን ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋር አለመነካካት አለባቸው ወይንም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተወሰነ ደረጃ መተባበር ይኖርባቸዋል ፤ እድገት ማግኘት ከፈለጉ። እንዲያውም የጥንቆላው ኢኮኖሚ በማሕበረሰቡ ውስጥ በጣም ከሰረጸ ፤ ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋር ሳይተባበሩ በፍጹም ወደ ላይ ከፍ ማለት የእማይችልበት ኹኔታ ይፈጠራል።

ይኽ በእሚሆንበት ግዜ ፤ የማሕበረሰቡ ሊህቃን እና አመራሮች ፤ ስልታዊ ይሆናሉ ፦ በአደባባይ የመደበኛውን ተቋም አገልግሎት በእኩልነት ለኹሉም ዜጋ ለማቅረብ እሠራለኹ እያሉ ፤ በስውር ግን ከኢመደበኛው የጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋር አብረው የእሚሠሩ በመሆን።

የጥንቆላ ኢኮኖሚ ጠንካራ በእሚሆንበት ግዜ ፤ በእዚያ ማሕበረሰብ ውስጥ አንድ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የእሚደርሱ ሰዎች ፤ መደበኛውንም ኢመደበኛውንም አሠራር በማጣቀስ ስለ እሚሆን ወደ ላይ የእሚወጡት ፤ በአፋቸው ሳይሆን በተግባራቸው ፤ ስኬት የጥረት እና የችሎታ ውጤት ሳይሆን ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋርም የመተሰሳሰር ጉዳይነው ብለው የእሚሰብኩ ይሆናሉ።

ይኽ አንድ ግለሰብ ወይንም ጥቂቶች የእሚይዙት መንገድ ሳይሆን ፤ ከሞላ ጎደል ማሕበረሰባዊ መንገድ የመሆን እድሉም በጣም ይጨምራል።

በእዚኽ መልኩ ወደ ላይ የእሚወጡ ሰዎች በበዙ ቁጥር ፤ አካኼዱ ይበልጥ ሥር እየሰደደ ይኼዳል።

ይኽም ፦ የማሕበረሰቡ ሊህቃን እና ሙህራን ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ የእሚቃወሙ እና ለማፍረስ የእሚሠሩ ሳይሆን ፤ በውድም ይኹን በግድ ተባባሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

ምክንያቱም ፦ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፤ ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ላይ ያደረሳቸውን አደረጃጀት ለማፍረስ መሞከር ፤ በግልም ሆነ በፖለቲካዊ መልኩ ከፍተኛ ዋጋ የእሚያስከፍላቸው ስለ እሚሆን።

እንዲያውም የጥንቆላው ኢኮኖሚ ተፅዕኖ እጅግ ሲያይል እና መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ለይስሙላ ባለጉዳይ ለመቀበል እንጂ ባለ ጉዳይ ለማገልገል ያልተቋቋሙ በእሚሆንበት ግዜ (When formal institutions function largely as a façade) ፤ ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ተሳትፎ ውጭ መሆን እማይታሰብ ነው የእሚሆነው።

በእዚኽን ግዜ እድገት እና ከፍታ በቀዳሚነት ከእዚኽ ከስውሩ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ጋር ባለ ግንኙነት የእሚወሰን ይሆናል።

የጥንቆላ ኢኮኖሚው የእድገት ደረጃ እዚኽ ላይ ከደረሰ ፤ የማሕበረሰብ ሊህቃን እና አመራሮች ፤ ለእድገት የጥንቆላውን ኢኮኖሚ የእሚጠቀሙ ሳይሆን እስከ እነ ጭራሹም የጥንቆላው ኢኮኖሚ ውጤት ነው የእሚሆኑት።

የማሕበረሰብ ሊህቃን እና አመራሮች የጥንቆላ ኢኮኖሚ ውጤት በእሚሆኑበት ግዜ ፤ የእሚከተሉት ባሕሪያት ይስተዋልባቸዋል።

አንድ አንድ የማሕበረሰብ ሊህቃን እና አመራሮች (Elites) ዝምታን ይመርጣሉ። በፊትለፊት ከመቃወም ወይንም ከመደገፍ ይልቅ ፤ ውስንነታቸውን አውቀው በዝምታ በኢኮኖሚው ውስጥ ለመሥራት ይወስናሉ።

ሌሎቹ በእዚኽ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀቱን ተጠቅመው ፤ ስልጣንን ለማስጠበቅ ፣ ተፎካካሪን ልክ ለማስገባት ወይንም ታማኝ ተከታይ ለማግኘት ይጠቀሙበታል።

ነግሩ ትንሽ ጫን ሲልም ፤ በአደባባይ እራሱ ፤ የእሚያግዘኝ ስውር ኃይል አለ ማለትም ሊጀመር ይችላል።

በተለያዩ የአፍሪካ ሐገራት እንደ ታየው ፤ በቃለ መጠይቅ ወቅት ወይንም ንግግር ሲደረግ ፤ የጥንቆላ አቅም ሊነሳ ይችላል።

ለምሳሌ ፦ የደቡብ ሱዳኑ ሬክ ማቻር (Reik Machar) ወደ ስልጣን የመጡት የጎሳቸው ነብያት ተንብየውለት እንደ ሆነ ይናገራል ፣ የደቡብ አፍሪካው ጃኮብ ዙማ (Jacob Zuma) በጸረ አፓርታይድ ትግሉ ወቅት በነጮ ጠላቶቻቸው ላይ ጠንቆላ እንደ ተጠቀመ በ2016 ተናግሯል።

እንደ እዚኽ ዓይነቱ ነገር ብዙ ያልተለመደ እና በይዘቱም አንዱ ከአንዱ የእሚለይ ይሆናል ፤ ሆኖም የጥንቆላው ኢኮኖሚ በኋላ ቀር ማሕበረሰባት ውስጥ በምን ያኽል ደረጃ ከመደበኛው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋም ጋር ተቀላቅሎ እንደ እሚገኝ ያሳያል።

በአንድ አንዶች ዘንድ ፤ ከእዚኽ የማለፍ እና ጥንቆላን የባሕል እና የማንነት ጉዳይ አድርጎ የማቅረብ ነገርም ይታያል። በባሕል ሕዳሴ ስም የጥንቆላውን ባሕል እንደገና ማንሰራራት ወደ አደባባይ ማውጣት ፤ እንደ ክርስትና ባሉ የውጭ ኃይማኖቶች የደረሰብንን የባሕል ደፈቃ ማስወገድ ነው ተብሎ የመቅረብ ነገርም ተጀምሯል።

እንደ እዚኽ ዓይነት እንቅስቃሴዎች የተለያዩ እና አንድ የጋራ መነሻ አላቸው ባይባልም ፤ ተደማምረው ግን ጥንቆላውን በማጠናከር ፤ የመደበኛ ተቋማት ተላዋጭ አድርጎ የማቅረቡን ነገር ግን ያግዛሉ።

የእዚኽም ውጤቱ ፦ ጥገኛውን የጥንቆላ ኢኮኖሚ ታግሎ ለማሸነፍ የማሕበረሰብ ሊህቃን እና አመራሮች ተደራራቢ ጫና እንዲ ገጥማቸው በማድረግ ትግሉን ውስብስብ ያደርግባቸዋል።

በአንዱ በኩል ብቁ አመራር ለመስጠት ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ በነጻ እና ገለልተኛ ሕግ ኹሉንም የማሕበረሰብ ክፍል በእኩልነት በማገልገል ዕድልን በእኩልነት የእሚያከፋፍሉ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለመኖር ፣ ውድድርን ለማሸነፍ እና አጋር ለማግኘት ከኢመደበኛው የጥንቆላ ኢኮኖሚ ጋር አብሮ መሥራት ሊፈልግ ይችላል።

ምርጫውን ማሕበረሰብን በመለወጥ እና በግል ህልውና መካከል ያደርግባቸዋል።

በመሆኑም ፦ ሊህቃን እና አመራሮች ፤ በጣም የጎለበት ስነምግባር ፣ ላቅ ያለ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ግንባታ ዕውቀት ፣ እንዲኹም ሰፊ መሠረት ያለው ማሕበራዊ እገዛ ከሌላቸው በስተቀር ፤ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የተንሰራፋ ኢመደበኛ አደረጃጀት ያለውን የጥንቆላ ኢኮኖሚ ሊታገሉት አይችሉም።

ብቻቸውን ከሞከሩት ፤ ከፍ ያለ ፤ ኢመደበኛም ቢሆን ተቋማዊ ተቃውሞ እና በግልም ከፍተኛ ስጋት ይጋረጥባቸዋል።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ መልካም ልብ ያላቸው መሪዎች እንኳን ፤ ይኽን ስውር አሠራር ከመታገል ይልቅ ፤ ማቻቻልን እንዲመርጡ ይሆናሉ።

አንድ አንድ ግዜ ፤ የማቻቻሉ ሙከራ ፤ በግዜ ኺደት ወደ ማፅደቅ እና መደገፍ ሊሸጋገር ይችላል።

እነ እዚኽ ናቸው እንግዲኽ የማሕበረሰብ ሊህቃን እና መሪዎች ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ፤ ሙሉ በሙሉ እንደ አይዙትም እንደ አይተውትም ፤ ይልቁንም ስልታዊ በሆነ መንገድ አብረውት እንዲሰሩ የእሚያደርጋቸው።

የእዚኽም ውጤቱ ፡- ምንም እንኳን የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ገለተኛ የሆኑ እና ኹሉንም የማሕበረሰብ ክፍል በፍትኃዊነት የእሚያገለግሉ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን እሚያዳክም ቢሆንም እንኳን ፤ ሊህቃኑ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ከማስወገድ ይልቅ አብረው እንዲሠሩ ይሆናል።

በእዚኽ መልኩ ካየነው ፤ መባል ያለበት ሊህቃን እንዴት የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ማፍረስ ያቅታቸዋል? ሳይሆን ፤ የጥንቅላው ኢኮኖሚ እራሱን የእሚያጠናክርበት አንድ መንገድ የማሕበረሰቡን ሊህቃን እና አመራሮችን እንኳን በመረቡ ውስጥ ሊያስገባ የእሚችል በመሆኑ ነው።

# 9 መፍትሔው : ተቋማዊ እንጂ የባሕል አብዮት ወይንም መንፈሳዊ አይደለም

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ለማሳየት እንደ ተሞከረው ፤ የጥንቁልናው ኢኮኖሚ ፤ በተለምዶ ከእሚሰጠው ግምት በላይ ወሰብሰብ ያለ ስለ ሆነ ፤ ሰዎች በትክክል አይረዱትም።

ጥንቆላ ማለት ለብዙዎች፡- መጠንቆል (የተሰወረ ማወቅ ፣ የወደፊት መናገር ፣ ወዘተ) ፣ ድግምት መድገም ወይንም ባሕላዊ ሕክምና መስጠት ብቻ አድርገው ይወስዱታል። ለማስቀመጥ እንደ ተሞከረው ግን ፤ በዘመናዊው ቋመናው ጥንቆላ ከእዚያ ወሰብሰብ ይላል።

ዘመናዊው ጥንቆላ ወይንም የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፡- የጥንቁልና መንፈስ ወይንም በሳይንሱ ፓራሳይኮሎጂ (Parapsychology) ብቻ አይደለም ፤ ይልቁንም ከጥንቁልና አሠራሩ ጋር አብሮ ፣ ኢመደበኛ አደረጃጀት እና ማሕበራዊ ምህንድስና (Social Engineering) አንድ ላይ ተጣምረው የእሚፈጥሩት እና ተቋማዊ ውጤት ለማምጣት የእሚሠራ አደረጃጀት ነው።

ይኽም ማለት ፡- የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ ከተራ ወይንም መደበኛ ፤ ክፉ መናፍስትን ከማናገር እና መጠቀም ወይንም በሳይንሱ ፓራሳኮሎጂካል (purely parapsychological or cultural phenomenon) ከመሆን ያለፈ ነው።

አኹን ባለበት ደረጃ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ክፍተት እመላለኹ ፤ ሲከፋም እነርሱን እተካለኹ የእሚል ተፎካካሪ ነው። የኢኮኖሚ ዕድሎችን በማከፋፈል ፣ የኢኮኖሚ ውጤቶችን በመወሰን እና በኢኮኖሚ ተዋናዮች መካከል የእሚገኝ ግንኙነትን በመምራትም ተፎካካሪነቱን ያሳያል።

የዘመኑ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ትክክለኛ መልኩ ይኽ ነው ካልን ፤ ለጥንቆላ ችግር የተለመደውን መልስ ፤ ማለትም ፡- ጎጂ ባሕል ነው ብሎ የባሕል መታደስ እንቅስቃሴ ወይንም መንፈሳዊ ብቻ ነው ብሎ አስበ መንፈሳዊ ውጊያ ብቻ ማወጅ ፤ የተሳሳተ መፍትኼ ነው የእሚሆነው ፤ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ፤ መደበኛዎቹ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ደካማ በሆኑበት ማሕበረሰብ ውስጥ።

እኔ በግሌ ፤ እንደ ክርስቲያን አማኝ ፤ ጥንቆላው ብቻውን ቢሆን ኖሮ ፤ በክርስትና ሕይወት ማደግ እና መጎልበት ፤ ጥንቆላውን በግል አንድ አንዴም በማሕበረሰብ ደረጃ ለማሸነፍ ያግዛል ብዬ አምናለኹ ፤ አሁን በእሚገኝበት የተደራጀ እና ማሕበራዊ ምህንድስናን በእሚጠቀምበት ደረጃ ግን ፤ ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ባለው ሰው እንኳን ቢደረግ ፤ ብቻውን ድል ለማስመዝገብ ያዳግተዋል ብዬ አስባለኹ።

ምክንያቱም ፡- አሁን በእሚገኝበት ደረጃ የጥንቆላው ኢኮኖሚ እንዲኽ ተንሰራፍቶ እና ተጠናክሮ ያለው ፤ በጥንቆላው ኃይል ብቻ ሳይሆን ፤ በኢመደበኛ አደረጃጀቱ እና በማሕበራዊ ምህንድስናው ታግዞ ፤ ተጨባጭ ውጤት የእሚያመጣ አገልግሎት በመስጠት በመሆኑ።

ጥንቆላው በራሱ ስህተት እና ግምት ስለ እሚበዛበት ፤ ሰዎች ትክክለኛነቱን ጥያቄ ውስጥ ቢያስገቡ እንኳን ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀቱን እና ማሕበራዊ ምህንድስናውን ተጠቅሞ መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ክፍተት በመጠቀም ፦ እድል ስለ እሚሰጥ ፣ የማስተባበር ሥራ ስለ እሚሠራ ፣ ተፅዕኖ ስለ እሚያደርግ ፤ ለማጣጣል እና ለመናቅ አዳጋች ያደርገዋል።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ ጥንቆላው እንደ አንዳች ዓይነት ፤ ልዩ እና ስውር ፤ ከሰው አቅም በላይ የሆነ ምትኃታዊ ኃይልን እንደ ሆነ ተደርጎ ሰውን ለማማለል ይቀርባል እንጂ ፤ በጥንቆላው ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ ሰው እና ኃብት በማንቀሳቀስ ፤ መረጃ የማሰራጨት ፣ ሰዎች የማስተባበር እና ጫና የመፍጠር ሥራ በመሥራት ፤ ውጤታማ የእሚያደርገው ፤ በዋናነት ኢመደበኛ አደረጃጀቱ እና የማሕበረሰባዊ ምህንድስና አቅሙ ነው።

በእርግጥ ፦ እንደ እኔ እምነት ፤ ጠንቋዩ በሳይንሱ ቴሌፓቲ (Telepathy) በእሚባለው መንገድ ፤ በሰዎች ላይ ፍርኃት ፣ ጭንቀት ፣ በጠቅላላ ኃሳብ የመልቀቅ ሥራ ሊሠራ አይችልም አይደለም ፤ ነገር ግን ፤ ያ በእሚሆንበት ግዜ እንኳን ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀቱ እና ማሕበራዊው ምህንድስና ፤ ነገሩን ጉልበት ካልሰጠው ፤ ብዙ ግዜ ውጤቱ ኢምንት ነው።

ስለ እዚኽ፦ ዘመናዊውን የጥንቆላ ኢኮኖሚ ፤ የባሕል አብዮት በማድረግ ወይንም መንፈሳዊ ውጊያ በማድረግ ብቻ ለማሸነፍ መሞከር ፤ በጣም ውስን ስኬት ነው የእሚኖረው።

ቢበዛ ፤ እራሱን ይበልጥ እንዲደብቅ ሊያደርጉት ነው የእሚችሉት።

የእሚፈለገው ግን ፤ እራሱን እንዲሰውር ማድረግ ሳይሆን ፤ ማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ችግር ሊፈጥር በእማይችል መልኩ ማሳነስ እና ማድቀቅ ነው።

ለእዚኽ ብቸኛ መፍትኼ ፤ እንደ አረም ሆኖ እንዲብቅል የእሚያደርገውን ብስባሽ ቆሻሻ እርሱም የመደበኛ ማሕብረ ኢኮኖሚ ተቋማት ድካም በማስወገድ ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ መብቀያ አረንቋ (ገበያ) ማሳጣት ነው።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ተፈላጊ የእሚያደርገው ምክንያት ሲጠፋ እንጂ ውግዝ ከማርዮስ ሲባል አይደለም የእሚጠፋው።

መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፦ በቃላቸው መሠረት ሲገኙ ፣ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት ሲኖራቸው ፣ አብረውም የተቋቋሙለትን ዓላማ በተጨባች በማሳካት ሕብረተሰብን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ሲያረጋግጡ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ተፈላጊነት እየቀነሰ ይኼድና ማሕበራዊ እንደምታው ይመናመናል።

በእዚኽ መልኩ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ትንሳኤ መስጠት የእሚቻለው ፤ በዋናነት በኹለት መንገድ ነው ፡-

1. ኹሉንም በእኩልነት የእሚያገለግሉ ገለልተኛ እንዲሆኑ በማድረግ እና
2. ፈጣን እና ተደራሽ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዘገብ የእሚችሉ በማድረግ

ነው።

የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት በሕግ ፊት እኩልነትን ማረጋገጥ የእሚችሉ ቢሆኑ ነገር ግን ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት የእማይመቹ ከሆነ ፤ የግዜ ጉዳይ ነው እንጂ ፤ የኢኮኖሚ ዕድገት የእሚፈልጉ ሰዎች ፤ ያችን በድህነት የነበረችውን ፍትኃዊነት ወደ ኢፍትኃዊነት ይቀይሯታል ፤ በተደራጀ የወንጀል ቡድን አሠራር ይኹን በጥንቆላ ኢኮኖሚ።

ስለ እዚኽ ፡- እንደ እኔ እምነት ፤ **<u>ከአምባገነንነት ወደ ምርታማነት</u>** በእሚለው መጽሐፍ ላይ እንደ አስቀመጥቁት ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ አረንቋ ማድረቅ የእሚቻለው ፡- አምስቱን ተቋማዊ ኹኔታዎች በማሳደግ ነው።

እነርሱም ፡-

1. የንብረት ባለቤትነት መብትን ማረጋገጥ
2. የንብረት ተንቀሳቃሽነትን ማረጋገጥ
3. በኢኮኖሚ ጉዳዮች ሕጉ በገለልተኛነት እና በእኩልነት ለኹሉም እንዲሠራ በማድረግ
4. የሐገር ኢኮኖሚ ከዓለም ዓቀፍ ንግድ ጋር በንግድ ክፍትነት በማስተሳሰር እና
5. ጠንቃቃ የበጀት አስተዳደር ስረዓት በማዳበር

ነው።

የአንድ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ እነ እዚኽን አምስት መርኾች ባከበረ መልኩ ሲዋቀሩ ፤ የኢኮኖሚ ጥቅም በጥረት እና በችሎታ እንጂ ከፖለቲካ ባለስልጣናት ወይንም ከአንድ ስውር የጥንቆላ ኢኮኖሚ ጋር ባለ ትብብር አይመጣም ፤ ያም ብቻ ሳይሆን ፤ የኢኮኖሚ ጥረቶች ውጤታቸው ደካማ አይሆንም።

የአንድ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት እነ እዚክን አምስት ኹኔታዎች ባከበረ መልክ ሲዋቀሩ ፡- ሰዎች ሥራ ቢቀጠሩ የእሚያገኙት ደሞዝ በምግብ የእሚያልቅ ሳይሆን ለቤትም ለመኪናም (በብድርም ቢሆን) የእሚተርፍ ይሆናል ፣ የንግድ ዕንቅስቃሴዎች ፡- በዋጋ ግሽበት ፣ በውድ የብድር ወለድ ፣ በውጭ ምንዛሪ እጥረት እና ገበያ በማጣት ከእሚሰቃዩ ይልቁ ፤ ጥራት እና ዋጋን ለማሻሻል የእሚወዳደሩ ይሆናሉ ፣ ወዘተ።

በእዚኽ መልኩ የአንድ ማሕበረሰብ ኢኮኖሚ ፤ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት ከኢኮኖሚያዊ ምርታማነት እና ዕድገት ጋር በእሚኖረው ግዜ ፤ የጥንቅላው ኢኮኖሚ ተፈላጊነቱ መቀነስ ብቻ ሳይሆን በማሕበረ ኢኮኖሚ ውስጥ በጥገኝነት ተለጥፎ ውጤት የማምጣት አቅሙ እየቀነሰ ስለ እሚኼድ ፤ የተቋማቱ በእዚኽ መልክ መጠናከር እስከ አለ ድረስ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ እየተዳከመ እና እየተመናመነ ኼዶ ፤ በዛር ላይ ፡- መዳፍ

አነባለኹ ፣ መሐረብ እርግብ አደርጋለኹ ፣ በካርታ ጥንቆላ ሚስጥር ኢገልጣለኹ የእሚል ፤ የሰርከስ ታዳሚ ነው የእሚሆነው።

እንደምታው ግልጽ ነው ፡- የጥንቆላው ኢኮኖሚ እንደ አጉል ዕምነት ብቻ ታይቶ አይደለም መፍትኼ ሊፈለግለት የእሚገባው ይልቁንም እንደ አንዳች መዋቅራዊ አሠራር ነው።

ስለ እዚኽ ፡- እንደ ኢትዮጵያ ባለ ኋላ ቀር ሐገር ፤ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ተንሠራፍቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ከተባለ ፤ መፍትኼው ፤ ውግዝ ከማርዮስ ማለት ሳይሆን ፤ ከአጉል ወንዝ የእማያሻግር የርዕዮተ ዓለም ክርክር ወጥቶ ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻችንን ፤ ኢኮኖሚያዊ አምራችነትን በእሚሸልሙ እና ጥገኝነቱን በእሚገፉ መንገድ ማዋቀር ነው።

ያን ማድረግ የእሚቻልበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ ፡- ከላይ በተዘረዘሩት አምስቱ ተቋማዊ ኹኔታዎች አንጻር ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ተቋሞቻችንን በማሳደግ ነው።

የተከበራችኹ ኢትዮጵያዊያን ፡- የንብረት ባለቤትነት መብትን እና የንብረት ተንቀሳቃሽነት መብት በማክብር የኢኮኖሚ ጥቅሞች ያለ ፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በምርታማነት እና በተወዳዳሪነት በነጻ ገበያ እንዲከፋፈሉ ካላደርግን ፣ የሕግ ስረዓታችንን ለኹሉም በእኩልነት የእሚሠሩ እና የንግድ ክፍትነትን በማረጋገጥ ፤ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሕጎች ለኢትዮጵያዊን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰተፍ ለእሚፈልገው የውጭ ዜጋም በእኩልነት እንዲሠራ በማድረግ ፡- ብድር ፣ መሬት ፣ ቀረጥ ፣ ግብር ፣ ወዘተ ለኹሉም ዜጋ በገበያ ሕግ እንዲደርሰው ካላደርግን ፣ የመንግሥት የበጀት አጠቃቀም ገቢ እና ወጪን ያመጣጠነ በማድረግ የመንግሥት በጀት አጠቃቀም የዋጋ ግሽበት እንደ አያስከትል ፣ የወለድ መጠን መናር እንደ አይስከትል ፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዳይፈጥር እና የዕዳ ጫና እንደ አያበዛ ፤ ካላደረግን የሕዝባችንን የኢኮኖሚ ጥያቄ ልንመልስ እና እንደ የጥንቆላ ኢኮኖሚ ያሉ ጥገኛ ስረዓቶችንም ልንዋጋ አንችልም።

ሙስናን በጸረ ሙስና ብቻ ለመዋጋት መሞከር ፤ ውቂያንስን በጭልፋ ዘግኖ ለመጨረስ እንደ መሞከር ነው። ኢምፖርት ሰብስቲቲውሽን እያሉ እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እያሉ ፤ የመንግሥትን ስልጣን ለኢኮኖሚያዊ ስረዓት አልበኝነት ማጋለጥ ፤ ርኃብን ለመዋጋት ፤ ምርትን ከመጨመር ይልቅ ሰዎችን በቀን አንዴ ብሉ ብሎ እንደ መምከር ፋይዳ ቢስ ነው።

ማሕበረሰብ ይኽን ተረድቶ ፡- የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማቱን አምስቱን ኹኔታዎችን እንዲያሟላ በማድረግ ፤ የሕዝብን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ ግልጸኝነት እና ምርታማነት ያላቸው ማድረግ ካልቻለ ፤ እንደ ጥንቆላ ኢኮኖሚ ያሉ ፤ ጥገኛ የኢኮኖሚ ስረዓቶችን በሌላ በማንኛውም መንገድ ለመታገል መሞከር ውጤት አልባ ነው እሚሆነው።

# 10 መደምደሚያ : ከአጋንንት ወደ ተቋም ግንባታ

ምን አልባት በእዚኽ ዘመን የሰው ሳይንሳዊ ዕውቀት እና የቴክኖሎጂ አቅሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረስ ፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት ሰዎች ሊያሷኳቸው ሳይሆን ሊያስቧቸው እንኳን የእማይችሏቸውን ነገሮች ፡- ከጤና ጉዳይ አንስቶ እስከ ግብርና ምርት ፣ ከግብርና ምርት አንስቶ ለሰው አስፈላጊ የሆነ ዘርፈ ብዙ ቁሳቁሶችን እስከ ማምረት ፣ ከቁሳቁስ ምርት አንስቶ እስከ እጅግ የረቀቁ የመገናኛ እና የትራንስፖርት መንገዶች የመጠቀም ደረጃ ላይ በመድረሱ እና የሰውን ቁሳዊ ችግር በብዙ መልኩ መፍታት የተቻለበት በመሆኑ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ ከሳይንስ ባሻገር ምትኃታዊ ኃይልን እየሰበከ ፤ ተንሠራፍቶ እዚኽ ደረጃ የደረሰበት አግባብ ትንሽ ግርምት እና ጥያቄ ሊያጭር ይችላል።

እንደ እሚታወቀው ፡- የሕክምናው ሳይንስ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የዘረ መል ምህንድስና ላይ ነው ፣ የትራንስፖርቱ መስክ እጅግ ተራቆ ከአንድ የዓለም ጫፍ ወደ ሌላ የዓለም ጫፍ በሰዓታት ግዜ ውስጥ ካለሆነ ከኹለት ቀን ባነሰ ግዜ ውስጥ መድረስ ተችሏል ፣ አንድ አንድ የመኪና ፋብሪካዎች እጅግ ዘመናዊ የሆነ መኪና በአንድ ደቂቃ ማምረት እሚችሉበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና የአልባሳት ፋብሪካዎች ልብስ እንደ ቅጠል ማርገፍ ችለዋል ፣ ወዘተ።

በእዚያ ላይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር ሐገራት እንኳን ሳይቀር ፡- ከእለት ወደ እለት ዩኒቨርስቲዎች በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፉ ነው ፣ የእውቀትን አድማስ በመደበኛው እና በዲጅታል መንገድ ለማስፋት ያለው እድል ከእለት እለት ጨምሮ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሷል ፣ የቴክኖሎጂ አክሰስ በእየግዜው እየጨመረ ነው ፣ ወዘተ ፤ በእዚኽ ኹኔታ የጥንቆላው ኢኮኖሚ እያፈገፈገ እና እያነሰ ይኼዳል ተብሎ ሲጠበቅ እስከ እነጭራሹም ድንበር እያሰፋ እራሱን ትይዩ ተቋም ደረጃ ለማድረስ እየተቃረበ መምጣቱ ትንሽ ጥያቄ ያጭራል።

ይኽ ጥያቄ ሲነሳባቸው ሰዎች በአብዛኛው ፡- ቴክኖሎጂው ፣ ሳይንሱ ፣ ወዘተ ቢኖርም ፤ ሕብረተሰቡ ግን ገና መኃይም ነው ፣ ባሕላዊ ነው ፤ ለእዚያ ነው ጥንቆላው የበረታው የእሚል መልስ ነው የእሚሰጡት።

በእዚኽ አጭር መጣጥፍ ውስጥ ለማሳየት እንደ ተሞከረው ግን ፤ መኃይምነትን እና ባሕላዊነትን የጥንቆላ ኢኮኖሚ መነሻ ምክንያት አድርጎ ማቅረብ ኹኔታውን በአግባቡ አለመረዳት ነው የእሚሆነው።

አኹን በደረሰበት ደረጃ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ የማሕበረሰብ ባሕላዊነት ውጤት አይደለም ፤ ማሕበራዊ ማሕይምነቱ የዘመናዊ ተቋማት ግንባታ እንዳይኖር አድርጓል ካልተባለ በስተቀር።

በአብዛኛው ግን ፤ የማሕበረሰቡ ማኃይምነት ነው ጥንቆላውን ያስፋፋው የእሚባለው ፤ ሕብረተሰቡ የስኬታማ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት የመገንቢያው ዕውቀት ያንሰዋል በእሚል ሳይሆን ይልቁንም መጀመሪያውንም በጥንቆላው መፍትኼ አገኛለኹ ብሎ ማሰቡ መኃይም ስለ ሆነ ነው በእሚል ነው።

የዘመናዊ ጥንቆላን ኢኮኖሚ መነሻ የእሚሰጠው የተቋማት መዳከም በመሆኑ ይኽ ዓይነቱ መልስ ትክክል አይደለም።

በእዚኽ አጭር መጣጥፍም ለማለት የተፈለገው ፤ ዘመናዊው እና የተደራጀው የጥንቆላ ኢኮኖሚ ምንጩ ፤ የመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት መዳከም እንጂ ፤ አንድ ሕብረተሰብ ማኃይማዊ የአጉል ዕምነት ተከታይነት በመሆኑ አይደለም።

ምክንያቱም ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ የባዕድ ዓምልኮ ዓይነት የሆነው ጥንቆላውን ብቻ የያዘ አይደለም ፤ ይልቁንም አንድ የኢኮኖሚ ስረዓት ፦ ተሳታፊ የእሚመለምልበት ፣ ማበረታቻ የእሚሰጥበት ፣ ግንኙነት የእሚያዳኝበት ፣ ጥቅም የእሚያከፋፍልበት እና ሕጉን የእሚያስፈጽምበት እንደ አለው ኹሉ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚም በእራሱ መንገድ እነ እዚኽ የአንድ ኢኮኖሚያዊ ስረዓት አካላት አሟልቶ የያዘ ነው ፤ በኢመደኛ አደረጃጀቱ እና በማሕበራዊ ምህንድስና ስልቱ።

ስለ እዚኽ ፦ በመደበኛው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፍትኽ እና ኢኮኖሚያዊ ስኬት ማግኘት ያልቻሉ ወደ እኔ ኑ የእሚል እና መርጦ ወደ እራሱ የእሚያስገባቸውን በእራሱ መንገድ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የእሚሰጥ ወይንም ሰጣለኹ የእሚል ከጥንቆላ ጋር አብሮ እና ባሻገር ሰፋ ያለ ኢመደበኛ አደረጃጀት እና ተቋማዊ ቅርጽ ያለው ነው።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ እራሱን ለመደበኛዎቹ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ እንደ ትይዩ ወይንም እንደ ተፎካካሪ የእሚያቀርብ ኢመደበኛ አደረጃጀት ነው።

የዘመናዊው የጥንቆላ ኢኮኖሚ ዋና ጥንካሬው ፤ ጠንቋዮቹ ስበው በእሚያመጡዋቸው ወይንም በእሚልኳቸው አጋንንት አይደለም ።

እነርሱ አቀሳሳሪ ናቸው ፤ ይልቁንም የጥንቆላው ኢኮኖሚ ትልቅ ጥንካሬ ፤ የተቋማት መዳከም በእሚፈጥረው የስጋት ድባብ ውስጥ ፤ ኢመደበኛ አደረጃጀቱን እና ማሕበራዊ ምህንድስናውን ተጠቅሞ ፤ የሰዎችን ባሕሪ መግራት እና መቆጣጠር የእሚችል በመሆኑ ነው።

መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ተዳክመው ፤ ተግባራዊ ውጤት አልባ ቀፎ በመሆናቸው ምክንያት ፤ ሐገሬው የኢኮኖሚ ውጤቶች ከሥራ ፣ ከትጋት እና ከችሎታ ጋር ከመገናኘት ይልቅ ዘፈቀደ በእሚመስል መልኩ ታታሪው ቆሞ ሲቀር ወንዝ አመጣሹ እላይ ሲወጣ ሲያዩ ፤ የሕይወት ምስጢር ወይንም የኢኮኖሚ ስኬት በአንዳች ልዩ ኃይል ነው የእሚመራው እና ያ ነገር ምንድ ነው ብለው መጠየቅ ውስጥ ይገባሉ።

ያን ግዜ ፦ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ፤ እስከ ዛሬ ታውረኽ ነበር ዛሬ ዓይንህ በራ ፤ ስውር ኃይልን ተጠቅሜ ፦ ሥራ እምሰጥኽ ፣ ጉዳይ እማስፈጽምልኽ ፣ ኮንትራት የእማሰጥኽ ፣ ወዘተ እኔ ነኝ ብሎ ይመጣል።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ በእዚኽ መልኩ እራሱን መመስረት ከጀመረ በኋላ ፦ በጥንቆላ ኃብት አፈራኹ ፣ ትልቅ ሥራ ያዝኩ ፣ ኮንትራት አሸነፍኩ ፣ ወዘተ የእሚሉ የዕውነት ይኹን የውሸት ምስክርነቶች ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ሌሎችን አማሎ እየሳበ ኔትወርኩን እንዲያሰፋ ያደርገዋል።

አንድ አንድ ግዜ ፤ ሰዎች ስለ እሚያምኑበትም ላይሆን ይችላል የእሚሳትፉት ፤ ይልቁንም እኔስ ለምን ይቅርብኝም ስቦ ሊያስገባቸው ይችላል።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ አንድ ግዜ ፡- በማባበልም ፣ በማታለልም ፣ በማስቀናትም ፣ ወዘተ ኔትወርኩን ካሰፋ በኋላ ፤ የማስፈጸም አቅሙ እና ተደራሽነቱ አብሮ ስለ እሚያድግ ፤ በሐገር ደረጃ የሰዎችን በሐሪ የእሚወስንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል ፤ ውስጥ ውስጡን ቢሆንም ፤ ጥንቆላ የእሚባል እና ሰዎች እራሳቸውን ለመጥቀም እና ሌሎችን ለመጉዳት የእሚጠቀሙበት ፤ ስውር እና ምስጥራዊ ኃይልን የእሚጠቀም አሠራር አለ የእሚለው ዜና ፤ ሰዎችን ጥንቆላን እንዲፈሩ እና እንዲሸሹ ካልሆነም ፤ ጥንቆላን መጠቀም እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል።

ይኽ ሲሆን ፤ ሰዎች ፡- በችሎታ እና በምርታማነት ለመወዳደር እየተዳከሙ ፤ ጥንቆላውን ለመጠቀም ይነሳሉ ።

የሮጠው ሳይሆን ያስጠነቆለው ከሆነ ዕድገት የእሚያገኘው ፣ ኮንትራት የእሚያገኘው ፣ ወዘተ መሮጥ ዋጋ ያጣል ፤ ማስጠንቆል ዋጋው ከፍ ይላል።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ የእሚላበሰውን ይኽን ዓይነቱ መኃበራዊ ጉልበት ፤ የማሕበረሰቡ ሊሂቃን እና መሪዎች እንኳን ሰለባ ሊያደርግ ይችላል። ምክንያቱም ፡- የማሕበረሰቡ መሪዎች እራሳቸው ከማሕበረሰቡ ውስጥ የእሚወጡ በመሆኑ ፤ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉት የመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት የእሚፈጥሩትን ችግር እና መሰናክል አልፈው ስለ ሆነ አሁን የደረሱበት ደረጃ የእሚደርሱት ፤ ከጥንቆላው ኢኮኖሚ ጋር ወይ አልነካህም አትንካኝ ካልሆነም በስውር የመተባበር ነገር ይኖራቸዋል።

ልቋቋመው አልችልም ብለው ሲሸሹት ወይንም አይተው እንደ አላዩ ሲልፉትም ሆነ የእድገት መሰላሉን ለመወጣት ጥንቆላውን ሲጠቀሙ ፤ እነርሱም እንደ ሌላው የጥንቆላው መረብ ውስጥ እንደ ገባው ዜጋ ፤ በእራሳቸው መንገድ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ያጠናክሩታል።

እንዲኽ በእሚሆንበት ግዜ ፤ መደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማቱ ፤ በአዋጅ እና በመተዳደሪያ ደንብ ተዋቅረው ይኖራሉ ፤ በስውር ግን የጥንቆላው ኢኮኖሚ በትይዩነት ወይንም በምትክነት የእነርሱን አገልግሎት በውድ ዋጋ ያቀርባል።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ በእዚኽ መልኩ በትይዩነት ወይንም በምትክነት መቆሙ ፡- የኢኮኖሚውን ብቃት በመቀነስ እና ብኩንነት በመጨመር ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድልን እና ኃብትን በምርታማነት ሳይሆን በጥንቆላ ደንበኛነት መሥፈርት በማከፋፈል የሐገርን ምርታማነት በመግደል ፣ በጥገኝነት በስውር የእሚሰበስበው ክፍያ በአንድም በሌላም መንገድ በተለያየ መልኩ ኢኮኖሚው ውስጥ በመዝለቅ የአገልግሎት እና የምርት ዋጋዎችን በማናር ፣ ወዘተ ፤ ዳፋው ብዙ ነው።

የጥንቆላው ኢኮኖሚ እንደ እዚኽ የተንሰራፋ እና መሠሪ ከሆነ ፤ ምን ተስፋ አለን በእሚል ጭንቀት ሊገባን አይገባም ፤ የመጣጥፉ ዓላማ የችግሩን ጥልቀት ማሳየት ብቻ ሳይሆን መፍትሔውንም ማሳየት ነውና።

የችግሩ ጥልቀት ለገባው እና ለመፍትሔው ለተዘጋጀ ማሕበረሰብ ፤ የጥንቆላው ኢኮኖሚ መፍትኼ ቀላል ነው ፡- የጥንቆላው ኢኮኖሚ መሠረት የመደበኛ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት መዳከም ከሆነ ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ማጠናከር የጥንቆላውን ኢኮኖሚ መሠረት ይንደዋል።

የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ሲጠናከሩ ማለት ፡- የከተማ አስተዳደሮች መሬት (ወይንም የመሬት ሊዝ) ፤ የገጠርም የከተማም ፤ በገበያ እንዲገዛ እና እንዲሸጥ በፖሊሲ ሲፈቅዱ ፣ ባንኮች ብድር በገበያ መሠረት ያዋጣል ላሉት ሲያበድሩ ፣ የሐገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲ የውጭ ምንዛሪ እንደ ማንኛውም ሸቀጥ በገበያ እንዲገዛ እና እንዲሸጥ ሲፈቅድ ፣ የሐገሪቱ ባንክ ከመንግሥት የፖሊሲ መሣሪያነት ወጥቶ በኢኮኖሚ ሳይንስ መሠረት የዋጋ ግሽበት ፣ የወለድ መጠንን እና የሥራ አጥነትን ችግር ለመዋጋት ሲሠራ ፣ መንግሥት የበጀት ጉድለት ሞላለው በእሚል ገንዘብ ማተም ሲያቆም ፣ በማበረታቻ ስም የግብር እፎይታ ፣ የማበረታቻ ብድር ፣ የቀረጥ ቅነሳ ፣ ወዘተ በተወዳዳሪነት ሳይሆን ስትራቴጂ ለተባሉ መስኮች መሰጠት ሲያቆም ፣ ፍርድ ቤቶች ቀልጣፋ እና ፈጣን ፍትኃዊ አገልግሎት ሲሰጡ ፣ ሕጎች አቦ ሰጥ እና ግብታዊ ከመሆን ይልቅ ግልጽ ፣ ሳይንሳዊ እና በቂ ሕዝባዊ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆኑ ፣ ወዘተ ማለት ነው።

ያን ግዜ ፡- በማሕበረሰቡ ውስጥ የኢኮኖሚ ጥቅም በፖሊሲ እና በመንግሥት ምርጫ ሳይሆን በዜጎች አምራችነት መመዘኛ መሠረት ስለ እሚከፋፈል እና ምህዳሩም ለኹሉም አምራች ዜጋ ከሞላ ጎደል በእኩልነት የእሚያገለግል ስለ እሚሆን እና አብሮም ኢንደስትራላይዜሽን አኹን በኢትዮጵያ እንደ ሆነ ከ52 ዓመት በኋላ እንኳን ያልተሳካበት ሳይሆን ከ20 እስከ 40 ባለ ዓመታት ውስጥ ስለ እሚሳካ እና ዜጋውም የመሳካቱን ተስፋ ሊክደው በእማይችል መልኩ ስለ እሚያየው ፤ ምን ጎደለኝ ብሎ ፤ ተጨማሪ ቀረጥ ወደ እሚያስከፍለው እና ተገቢው ተጠያቂነት እና አስተማማኝነት ወደ ሌለው ወደ ስውሩ የጥንቆላው ኢኮኖሚ ይኼዳል ?

በእዚኽ መልኩ በተቋማት መጠናከር የጥንቆላው ገበያ እየቀነሰ ሲኼድ ፤ ከግዜ ወደ ግዜ አላስፈላጊ ይሆናል።

እንደ ዕምታዩት ፤ የጥንቆላውን ኢኮኖሚ ማፍረስ ፤ ሰዎች በጥንቆላ እንዲያምኑ ወይንም እንደ አያምኑ ከማድረግ ጋር የተያያዘ አይደለም ፤ ይልቁንም በማሕበረሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ ስጋትን የመቀነስ ጉዳይ ነው።

የኢኮኖሚው አስተማማኝነት ሲጨምር የጥንቆላው አስፈላጊነት ይቀንሳል።

ከእዚኽ አንጻር እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር እና ደካማ ተቋማት ባሉባቸው ሐገራት ፤ ጠንካራ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን የመገንባትን ነገር ፈታኝ ያደረገው ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ጥንካሬ የእምንመዝንበት መንገድ ፤ ከ20 እስከ 40 ዓመት ባለ ግዜ ውስጥ ኢንደስትሪያሌዝሽን ማምጣት ይችላሉ ወይንስ አይችሉም በእሚል ሳይሆን ከሞላ ጎድል ከምኞታችን ሊባል በእሚችል ደረጃ ፤ ከምኞታችን አንጻር ጥንካሬያቸውን ስለ እምንመዝን ነው።

የሕገ መንግሥቱ ዓይነት ሳይሆን ሕገ መንግሥት ስለ አለን ፤ የመሬት ፖሊሲው ዓይነት ሳይሆን የመሬት ፖሊሲ ስለ አለን ፣ የገንዘብ ፖሊሲው ዓይነት ሳይሆን የገንዘብ ፖሊሲ ስለ አለን ፣ ወዘተ በአጠቃላይ የይስሙላም ይኹኑ አይሆኑ መዝገብ ቤት የእሚሞሉ የተቋም መመሥረቻ ሰነድ እና ፖሊሲ ስለ አለን እና በእዚያም መሠረተ የተቋቋሙ ፡- ፓርላማ ፣ ምኒስትር መሥሪያ ቤቶች ፣ የፖሊሲ ሰነዶች ፣ ፍርድ ስረዓት ፣ ክልል ፣ የአከባቢ መንግሥት ፣ ወዘተ ስለ አለን ብቻ ፤ ጠንካራ ተቋም ያለን አድርገን የእምንወስድ መሆኑ አንድ ትልቅ ደንቃራ ሆኗል።

እነ እዚኽ ተቋማት አያስፈልጉም አይደለም ፤ ነገር ግን ፤ እነ እዚኽ ተቋማት መመዘን ያለባቸው ፤ አኹን በተዋቀሩበት መንገድ ፤ የዛሬ 20 ቢበዛ ደግሞ 40 ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ ፤ ኢንደስትራላይዜሽን የእሚያመጣ መዋቅራዊ ሽግግር ያስችላሉ ? በእሚለው ነው።

ያ ደግሞ ፤ እንደ ኢሕአዴግ ዓለም ባያምንበትም እኛ ግን እያደግን ነው በእሚል ፤ የተንሻፈፈ ዕድገት በማደግ መሸቀጥም የለበትም።

አካኼዳችን ፡- መላው ዓለም ፡- IMF, World Bank, African Development Bank, World Class Economist, etc. ፤ የኢትዮጵያ አካኼድ ፤ በእሚቅጥለው ከ20 እስከ 40 ዓመት ፤ ኢትዮጵያን ኢንደስትራላይዝ ያደርጋታል ብሎ መስማማት አለባቸው።

የእሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንደ እሚባለው ፤ አካኼዳችን መመስከር አለበት ፤ መላው ዓለም እየኮነን እኛ ሐገር በቀል ቀመር አለን የእምንል በመሆናችን ግን ፤ ይኸው 52 ዓመት ሆኖናል ከበሬ እና ከዶማ ሳንላቀቅ።

እንደገናም ፤ አካኼዳችውን የዛሬ 20 ዓመት ቢበዛ የዛሬ 40 ዓመት ኢንደስትራላይዝ ሊያደርገን ይገባል ሲባል ፤ ለምሳሌ ፡-የዛሬው አያያዛችን ከ5 ዓመት በኋላ የኢትዮጵያን የነፍስ ወከፍ ገቢ ቢያንስ በ700 ዶላር እንደ እሚጨመር ያሳያል ማለት ነው።

20 እና 40 ዓመት ተኻቶ ፤ ድንገት ልክ በ20ኛው እና በ40ኛው ዓመት ፤ ኢንደስትራላይዝድ መሆን የእሚባል ነገር ስለ ሌለ።

የዛሬ የኢቶጵያን የተቋማት ኹኔታ ይዛችኹ ግን የትኛውንም ኢኮኖሚስት እና የኢኮኖሚ ትንበያ መሣሪያ ፤ የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ የዛሬ አምስት አመት ስንት ይሆናል ብትሉት ፤ በ700 ዶላር ይጨምራል ሊል አይችልም።

መንግሥት እንደ አሻው በትክክለኛው ጎዳና ላይ ነኝ ሊል ይችላል ፤ መሬት ላይ ያለው ተጨባጭ ኹኔታ እና ዓለም ዓቀፉ የኢኮኖሚ ሳይንስ ዕውቀት ግን ፤ የለም በደካማ የተቋማዊ ጎዳና ላይ ነው ያለኸው ነው የእሚለው።

ስንደመድመው ፡- አጋንንቱን አባረን ተቋም መገንባት ካለብን ፤ በተቋም ግንባታ ጉዳይ ውበት እንደ ተመልካቹ ነው ዓይነት ድርቅና ይዘን የትም ልንደርስ አንችልም።

የተቋም ግንባታ መርሐችን እኛን ሳይሆን ውጤትን እና ዓለምን ማሳመን አለበት።

ያን ግዜ ፤ ጥንቆላ ጎጂ ባሕል ሆኖ ይቀራል !

ስለ እዚኽ ፡- ግባችንን ፡- መናፍስትን ከመዋጋቱ ጎን ለጎን እና በአሻገር ፤ ጠንካራ ተቋም በመገንባት ላይ ማተኮር አለበት። ስለ ተቋሞቻችን ጥንካሬ ደግሞ ሳይንስ እና የእሚያስመዘግቡት ውጤት ይመስክር እንጂ ፤ እኛው በልማዳዊ ድርቅናችን ፤ ዓለም ባይረዳንም ፣ ውጤት ባይደግፈንም ወይንም ውጤታችንን ዓለም

ቢንቀውም ፣ የእኛ አካኼድ ሐገራዊ ነው ፣ ወዘተ በእሚል ፤ ተቋማዊ ጥንካሬን ሳይንሳዊ ሳይሆን ግለሰባዊ (Subjective) ልናደርገው አይገባም ፤ እንደ እዚያ ደርቀን የትም ስለ አልደረስን።